# የወልድያ ዩኒቨርሲቲ የአምስት ዓመታት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ

## ከ2013 እስከ 2017ዓ.ም

**ጥር 2013ዓ.ም**

**ወልድያ ዩኒቨርሲቲ**

ማውጫ

መግቢያ ....4
1.1 የወልድያ ዩኒቨርሲቲ አጭር ታሪክ ....5
1.2 የስትራቴጂዊ ዕቅዱ ግንባታ ሂደት ....Error! Bookmark not defined.
1.3 የሚዛናዊ ውጤት-ተኮር ስርዓት ምንነትና ጠቀሜታ ....Error! Bookmark not defined.
2. አገራዊና ተቋማዊ/ስትራቴጂያዊ ዳሰሳ ....18
2.1 የአገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ትንተና ....Error! Bookmark not defined.
2.1.1. የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ Error!
2.1.2. የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ Error!
2.1.3. የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ Error!
2.1.4. የከተማና ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ Error!
2.1.5. የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ Error!
2.2 ተገልጋዮችንና ባለድርሻ አካላትን መለየትና ፍላጎታቸውን መተንተን ....15
2.2.1 ተገልጋዮችንና ባለድርሻ አካላትን መለየት 16
2.2.2 የተቋሙና የተገልጋይ/ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት ማነፃፀሪያ 12
2.2.3. የተገልጋይ/ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት ትንተና 16
2.3 የውስጣዊና ውጫዊ /ጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚና ስጋት/ ዳሰሳ ....Error! Bookmark not defined.
2.3.1 ውስጣዊ ዳሰሳ Error!
2.3.2. ውጫዊ ዳሰሳ 18
2.4. አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች....Error! Bookmark not defined.
2.4.1. አስቻይ ሁኔታዎች /ጥንካሬ + መልካም አጋጣሚ/ 20
2.4.2. ፈታኝ ሁኔታዎች /ድክመት + ስጋት/ 21
2.5. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች....Error! Bookmark not defined.
2.6. የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ ዕሴቶች እና መሪ ቃል....Error! Bookmark not defined.
3. ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች እና ዕይታዎች ....Error! Bookmark not defined.
3.1 የትኩረት መስኮች ....Error! Bookmark not defined.
3.2 ዕይታዎች ....Error! Bookmark not defined.

4.ስትራቴጂያዊ ግቦች እና የግቦች መግለጫ ..... Error! Bookmark not defined.
5. ስትራቴጂክ ማፕ ..... Error! Bookmark not defined.
5.1 የላቀ የትምህርት አሰጣጥ ..... Error! Bookmark not defined.
5.2 ችግር ፈች ጥናትና ምርምር ..... Error! Bookmark not defined.
5.3 የማህበረሰብ አገልግሎት ..... Error! Bookmark not defined.
5.4 የቴክኖሎጂ ልማት ..... Error! Bookmark not defined.
6. ተቋማዊ ግቦች፣መግለጫዎች እና ዉጤቶች ..... Error! Bookmark not defined.
7. መለኪያዎችና ዒላማዎች ..... Error! Bookmark not defined.
8. ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች ..... 52
9. የክትትልና ግምገማ ስርዓት ..... 82
9.1 የክትትል ስርዓት ..... 82
9.2 የሪፖርት ፍሰትና ወቅት ..... 83
9.3 የሪፖርትና ግብረ-መልስ የጊዜ ሰሌዳ ..... 84
9.4 ግምገማ ..... 85
9.5 የውድድርና የሽልማት አፈጻጸም ..... 86
9.6 ስትራቴጂ ፍተሻና ማስተካከያ ..... 87
9.7 የቅሬታ አቀራረብ ..... 87

## 1.መግቢያ

ትምህርት የሰው ልጆችን የኑሮ ሁኔታ የተመቻቸ ለማድረግና ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማረጋገጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወት የእድገት መሳሪያ ነው፡፡ የአንድ ሃገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና የቴክኖሎጂእድገት ቀጣይነት እንዲኖረው ትምህርት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ በመሆኑም ሀገራት ዜጎቻቸው የትምህርት እድል እንዲያገኙና በቀሰሙት እውቀት፣ ክህሎትና የአመለካከት ለውጥ ለራሳቸውም ሆነ ለሀገራቸው እድገት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ለማስቻል የማያቋርጥ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

ሀገራችንምመንግስት ህብረተሰቡን በልማት ተጠቃሚ እንዲሆን፣ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍንና ዲሞክራሲያዊነት እንዲያብብ ሀገራዊ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመንደፍ በየደረጃው ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በትምህርት ዘርፍ ልማት እቅዶቹም በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የትምህርት ተሳትፎን፣ ፍትሃዊነትን፣ ጥራትንና አግባብነትን የሚያሳድጉ ግቦችና አቅጣጫዎች በማስቀመጥና በመተግበር ከፍተኛ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

የወልዲያ ዩኒቨርሲቲም መንግስት በነደፈው ከፍተኛ ትምህርትን የማስፋፋት እቅድ መሰረት በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ ለመክፈት በእቅድ ይዞ ከካከናወናቸው ተግባራት ውስጥ አንዱ ሲሆን ስራውን በ2004ዓ.ም 600 የመደበኛ ፕሮግራም ተማሪዎች ከትምህርት ሚኒስቴር ተመድበው ከነዚህ ውስጥ በዩኒቨርስቲው ቀርበው የተመዘገቡ 573 ተማሪዎችን በመያዝ ነበር፡፡ ከዚህ በመነሳት በ2012ዓ.ም የተቀበላቸውን አዲስ መደበኛ ተማሪዎች ቁጥር ወደ 4221 ከፍ በማድረግ የአጠቃላይ መደበኛ ተማሪዎች ቁጥር 12,003 ደርሷል፡፡ በትምህርት ፕሮግራሞች ደረጃም በ2004ዓ.ም ከነበሩት 12 የትምህርት ክፍሎች ወደ 45 ከፍ ለማድረግ ተችሏል፡፡

በጥናትና ምርምር ዘርፍም የጥናትና ምርምር ፖሊሲ በመንደፍና የምርምር የትኩረት ዘርፎችን በመለየት እንዲሁም የተመራማሪዎችን አቅም በማጎልበት ቁጥራቸውን ከማሳደግ ባለፈ ተደራሽ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ተቋማዊ ሰሚናሮችን የማዘጋጀት፣ የጥናትና ምርምር ፕሮሲዲንግ የማሳተም፣ተመራማሪዎች የጥናትና ምርምር ውጤቶቻቸውን በአገር ውስጥና በውጪ አገር ታዋቂ ጆርናሎች ላይ እንዲያሳትሙ የማበረታታት እንዲሁም በየዓመቱ አገራዊ ሲምፖዚየም እንዲካሄድ የማድረግ ተግባራትን አከናውኗል፡፡

በሌላ በኩል የሚሰጣቸው ማህበረሰብ አገልግሎት ተግባራት ህበረተሰቡን ያሳተፉና ችግሮችን በዘላቂነት ሊፈቱ የሚችሉ ለማድረግ የሚያስችል ጭብጦችን የመለየትና ቅደም ተከተል የመስጠት ስራ የተሰራ ሲሆን የቀጥተኛ ተጠቃሚዎችን ቁጥርም 14,000 ለማድረስ ችሏል፡፡

በአጠቃላይ ዩኒቨርስቲው ባለፉት ዓመታት የነበረው ከዓመት ዓመት እየተሻሻለ የመጠ አፈጻጸም የአጠናክሮ ለማስቀጠልና  የነበሩበትን ክፍተቶች በመለየትና በቀጣዩ አምስት ዓመታት የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል የአስር ዓመት መሪ እቅድ በማቀድ ይህንን ከመሪ እቅዱ የተቀዳ እቅድ አዘጋጅቷል፡፡ እቅዱ የዩኒቨርስቲውን አመሰራረት፣ የበለፉ ዓመታት አፋጻጸም፣ ግቦችና ዓላማዎችና የትኩረት አቅጣጫዎች፣ ወሳኝ የሆኑ የሰብዓዊና ቁሳዊ ሃብቶች፣ የማስፈጸሚያ ተቋማዊ አቅም ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች፣ የፋይናነስ ፍላጎትና ምንጭ፣ የስትራቴጂክ ግቦች፣ዓላማዎችና አመላካቾች፣ ዒላማና የድርጊት መርሃ ግብር እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ሥርዓትን አካቶ በመያዝ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 2. የወልድያ ዩኒቨርስቲ አመሰራረት፣ አፈጻጸምና ነባራዊ ሁኔታ ግምገማ

## 2.1 የወልድያ ዩኒቨርሲቲ አጭር ታሪክ

ወልድያ ዩኒቨርሲቲ የኢፌዴሪ መንግስት በነደፈው ከፍተኛ ትምህርትን የማስፋፋት ዕቅድ መሰረት ከከፈታቸው የሦስተኛ ትውልድ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ሲሆን በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 220/2003 መሰረት የመሰረት ድንጋዩ ጥቅምት 26 2001ዓ.ም ተጥሎ ህዳር 18 2004 ዓ.ም መደበኛ የመማር ማስተማር ተግባሩን በይፋ ጀምሯል፡፡ ዩኒቨርሲቲው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በሰሜን ወሎ ዞን፣ በወልድያ ከተማ 201 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ዋና ግቢ፣ መርሳ ላይ የግብርና ኮሌጅ እና ላሊበላ ላይ የቅርስ ጥበቃና ጥናት ኢንስትተዩት አለዉ፡፡ ዋናዉ ግቢ የሚገኝባት ወልድያ ከተማ ከኢትዮጵያ ዋና ከተማ አዲስ አበባ በሰሜናዊ አቅጣጫ በ521 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡

ዩኒቨርሲቲው በ2004ዓ.ም የመማር ማስተማር ስራውን ሀ-ብሎ ሲጀምር በመደበኛው ፕሮግራም በመጀመሪያ ዲግሪ 573 ተማሪዎችን  በአራት ፋካልቲዎችና በአስራ ሁለት ትምህርት ክፍሎች እንዲሁም በቅዳሜና እሁድ የትምህርት መርሃ-ግብር በሁለት ትምህርት ክፍሎች 156 ተማሪዎችን በድምሩ  729 ተማሪዎችን የተቀበለ  ሲሆን በወቅቱ

115 መምህራንና 117 የአስተዳደር ሠራተኞች ነበሩት፡፡ ዩኒቨርሲቲዉ አሁን በዘጠኝ ዓመታት ቆይታዉ በ2012 ዓ.ም ሁለት ኢንስቲትዩት፣ ሁለት ኮሌጅ፣ አራት ፋካልቲ፣ ስድስት ትምህርት ቤቶች ያሉት ሲሆን በአጠቃላይ በመጀመሪያ ዲግሪ 48 የትምህርት መስኮችን በ44 ትምህርት ክፍሎች በሁለተኛ ዲግሪ 9 የትምህርት መስኮችን በመክፈት ዓመታዊ የቅበላ አቅሙን ወደ 12,003 ተማሪ ከፍ ያደረገ ሲሆን በጥናትና ምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፎችም ሰፊና የተጠናከረ ስራ በመሰራት ላይ የሚገኝ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት 1,285 መምህራንና ቴክኒካል አሲስታንት እንዲሁም 958 ቋሚ የአስተዳደር ሰራተኞችና 983 በማህበራት የተደራጁ አገልግሎት ሰጭ ሰራተኞች አሉት፡፡

የተቋሙን ጥረት ካለው የሰው ኃብትና የገንዘብ አቅም ጋር በማጣጣም ተልዕኮዉን ለማሳካትና በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ የተማሪ ቅበላ አቅሙን ወደ 16,500 ከፍ በማድረግ የሚፈለገው ውጤት ላይ ለመድረስ የተጀመረውን ተቋማዊ ጉዞ ውጤታማ በሆነና ወጥነት ባለው መንገድ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ያሉ የመንግስት ተቋማትን አፈጻጸም በአግባቡ ለመመዘንና ለመምራት እንዲያስችል ታስቦ የተመረጠውን የአፈጻጸም አመራር ስርዓት ማለትም የሚዛናዊ ውጤት-ተኮር ስርዓት ሲተገበር የቆየ ሲሆን አሁን ደግሞ ለቀጣዮቹ አምስት ዓመታት ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈልጎታል፡፡

## 3 የዩኒቨርስቲው የባለፉት አምስት ዓመታት ዋና ዋና ተግባራት አፈጻጸም ግምገማና የሁኔታ ትንተና

### 3.1 የአምስት አመታት አፈጻጸም ግምገማ

### 3.1.1.መማር ማስተማር

### 1.ተደራሽነት

ዩኒቨርስቲው የመማር ማስተማር ስራውን የተሻለ በማድረግ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ ተግባራትን ለይቶ በእቅድ በመያዝ ተግባራዊ ያደረገ ሲሆን ትምህርትን ለማህበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ ዩኒቨርስቲው ባለፉት ዓመስት ዓመታ የተጠነከረ ስራ የሰራ ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት8655(ሴ.3250) ተማሪዎችን ተቀብሎ የነበረ ሲሆን በ2011 እና 2012 በጀት ዓመት የመቀበል አቅሙን እስከ 4718 ከፍ በማድረግ ዓመታዊ ጠቅላላ የማስተማር አቅሙን ወደ12003 ከፍ ላማድረግ ችሏል፡፡ በተመሳሳይ መደበኛ ባልሆነው ፕሮግራም/በክረምትና ኤክስቴንሽን/ በ2008 በጀት ዓመት የነበረውን 1942(ሴ.555) በ2012 8420 ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማስተማር ችሏል፡፡ በተመሳሳይ በ2008 በጀት ዓመት 56 የሁለተኛ ድግሪ ተማሪዎችን መደበኛ ባለሆነ ፕሮግራም ማስተማር ጀምሮ በ2012 በጀት ዓመት 36 በመደበኛ፣ 127 በኤክስቴሽንና በክረምት በድምሩ 163 በሁለተኛ ድግሪ ተማሪዎችን ደረጃ ተቀብሎ አስተምሯል፡

ዩኒቨርስቲው በ2006 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ 1799 ተማሪዎችን ያስመረቀ ሲሆን በ2012 ዓ.ም በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት ተማሪዎችን ለማስመረቅ ባይችልም በ2011 ዓ.ም 2627 ተማሪዎችን አስመርቋል፡፡

### 2. የትምህርት ጥራት ማረጋገጥ

የትምህርት ጥራትን ከማስጠበቅ አኳያም ምንም እንኳን የትምህርት ጥራቱ በይበልጥ ሊለካ የሚችለው ተመርቀው የሚወጡ ተማሪዎች በአገሪቱ የልማት እንቅስቃሴ ውስጥ በሚፈለገው ብቃት ደረጃ ተሳትፈው በሚያስመዘግቡት ለውጥ ቢሆንም ይህንን ሊያመጡ በሚችሉ የትምህርት አሰጣጥ ስርዓት፣ የትምህርት ግብአቶችን ከማሟላትና አጠቃላይ ሂደት አንጻር የተከናወኑ ተግባራትን ለመገምገም ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር የትምህርት ጥራትን ከሚከተሉት እይታዎች አንጻር ለመዳሰስ ተሞክሯል፡ የትምህር ጥራትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ግብዓቶችን ማለትም ወርክሾፖችና ላብራቶሪዎችን የማሟላት፣ የመምህራንን አቅም የመገንባት፣ የመማር ማስተማር ስራው ተግባር ተኮር የሆነና ተማሪዎችን ያሳተፈ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችሉ ስራዎችን አከናውኗል፡፡

### 3. ፍትሃዊነት

ዩኒቨርስቲው ዜጎች በእኩል ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መንግስት እየወሰዳቸው ባሉት እርምጃዎች ላይ በመመርኮዝ በዩኒቨርስቲው ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎችና የአካባቢው ማህበረሰብ በጾታ፣ በብሄረሰብ፣ በሐይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና ማህበራዊ እድገታቸው ልዩነት ሳይፈጠር ለማስተናገድ በእቅድ ይዞ ሲንቀሳቀስ ቆይታል፡፡ በዚህም ሁሉም የማህበረሰብ አካላት ያለምንም አድሎ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

ምንም እንኳን የሴት ተማሪዎች ተሳትፍ መጠን የሚወሰነው የትምህርት ሚኒስቴር በሚመድባቸው ተማሪዎቸ ቁጥር ቢሆንም በ2012ዓ.ም አጠቃላይ በመደበኛ የቅድመ ምረቃ ትምህርት የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ 35.4% የደረሰ ሲሆን ይህም ከሃገራዊ ተሳትፎ አንጻር የተሻለ አፈጻጸም ነው፡፡

ሆኖም የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ ፍትሃዊነት የሚረጋገጠው በምንቀባላቸው ሴት ተማሪዎች ቁጥር ብቻ ሳይሆን በትምህርት ቆይታቸው በሚሰጡ ተከታታይ ድጋፎች የመዝለቅ ምጣኔያቸውን ከፍ በማድረግ ጭምር በመሆኑ ዩኒቨርስቲው ይህንኑ ጉዳይ በእቅድ ይዞ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡

በዚህም ለሴት ተማሪዎች ልዩ የቱቶሪያል ፕሮግራሞችን በማዘጋጀትና የትምህርት ድጋፍ በማድረግ፣ በኢኮኖሚ አቅማቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ሴት ተማሪዎች የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ በማደረግ፣15% የሚሆነውን የትምህርት መስክ ምደባ ሴቶች እርስ በርሳቸው በመወዳደር በመረጡት የትምህርት መስክ እንዲመደቡ፣ በስርዓተ-ጾታና በስነ-ተዋልዶ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በስፋት በመስራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል፡፡

### 4. ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች

ዜጎች በትምህርቱ ዘርፍ በፍትሃዊነት እንዲገለገሉና ተመጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ አኳያ በቁርጠኝነት እየሰራ ከሚገኝባቸው አንኳር ተግባራት ውስጥ የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ሲሆን በዚህ ዘርፍ ዩኒቨርስቲው አቅሙ የፈቀደውን በማከናወን ላይ ሲሆን ባለፉት አመታት እየተሻሻለ የመጣ አፈጻጸም አስመዝግቧል፡፡ በዚህም የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች፡-

- የሽንት ቤት መደገፊያ፣

- የንባብ ክፍል በማዘጋጀት የላይበራሪ አቴንዳንቶች መጽሃፍትን የማቅረብ አገልግሎት እንዲሰጧቸው፣
- በመኝታ ቤት ህንጻዎች ላይ በምድር ቤቶች እንዲመደቡ፣
- የኢኮኖሚ ችግር ላለባቸው የአካል ጉዳተኞች የገንዘብ ድጋፍ፣
- የምግብ ቤት የመስተንግዶ አገልግሎት በቅድሚያ እንዲያገኙ የማድረግ ስራዎችን አከናውኗል፡፡

ሆኖም የነባር ህንጻዎች ግንባታ ዲዛይኖች የአካል ጉዳተኞችን ከግምት ውስጥ ያላስገቡ በመሆናቸው በመማሪያ ክፍሎችና በመኝታ ቤቶች አካባቢ ችግር መፍጠራቸው አልቀረበመሆኑም በቀጣይ የእቅድ ዘመን የሚከናወኑ አዳዲስ ግንባታዎች እነዚህን ያገናዘቡ መሆን እንዳለባቸው በመገንዘብ በሚሰሩ ዲዛይኖች ላይ ትኩረት ተሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ከታዳጊ ክልሎች ለመጡ ተማሪዎች በመመሪያው መሰረት በመረጡት የትምህርት መስክ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ በማድረግ መንግስት የሰጠውን ኃላፊነት በመወጣት ላይ ነው፡፡

### 3.1.2 የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት

ዩኒቨርስቲው ከመንግስት ከተቀበላቸው ተልዕኮዎች መካከል ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎችን ማከናወን፣የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖን የማስቻልና ለህብረተሰቡ ችግር ፈቺ የአገልግሎት ስራዎች መስራት ይገኙበታል፡፡ በዚሁ መሰረት የወልድያ ዩኒቨርስቲ ከተቋቋመበት 2004ዓ.ም ጀምሮ እነዚህን ተልኮዎች ለመወጣት በእቅድ ይዞ ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

*ሀ. ምርምር*

ዩኒቨርስቲው በምርምር ዘርፍ የተመራማሪዎችን አቅም በመገንባትና የምርምር ውጤቶቻቸው ለተገልጋዩም ሆነ ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ እንዲሆኑ ለማስቻል ዩኒቨርስቲው ከ2004ዓ.ም ጀምሮ በእቅድ ይዞ የተንቀሳቀሰ ሲሆን በተለይም መምህራኑ ጀማሪ ተመራማሪዎች በመሆናቸው አቅማቸውን በመገንባት ስራ ላይ ትኩረት አድርጎ ሰርቷል፡፡ በየአመቱ በጥናትና ምርምር ላይ የጽነሰ ሃሳብ ስልጠናዎች የተሰጠ ሲሆን የምርምር ስራው የሚፈለገውን ግብ ለማሳካት ያስችል ዘንድም የምርምር ፖሊሲ ወጥቷል፤ በጥናት ላይ የተመሰረተና የአካባቢውን ማህበረሰብ ችግር መሰረት የምርምር የትኩረት መስኮች ተለይተዋል፡፡

በዚህም የምርምር ስራዎች በተናጠልና በጋራ እየተከናወኑ ሲሆን በ2004ዓ.ም 4 የምርምር ስራዎች የተከናወነ ሲሆን በ2012ዓ.ም 53 የጥናት ንድፈ ሃሳቦች ጸድቀው 15ቱ ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ የምርምር ውጤቶቹን ተደራሽነት ለማሳደግም በ2006ዓ.ም የመጀመሪያውን ተቋማዊ ዓመታዊ የምርምር ሲምፖዚየም፤ በ2007ዓ.ም የመጀመሪያውን ሃገር አቀፍ ሲምፖዚየም አዘጋጅቶ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ተችሏል፡፡በሌላ በኩል የምርምር ውጤቶችን በውጪ ሀገርና በሀገር ውስጥ በሚታተሙ ጆርናሎች ላይ ለማሳተም ጥረት የተደረገ ሲሆን 25 ውጤቶች በውጪ ሃገራት ጆርናሎች ላይ ታትመዋል፡፡ ለዩኒቨርስቲው የመጀመሪያ የሆነ የአብስትራክት መጽኃፍ/ፕሮሲዲንግም በ2007ዓ.ም የታተተመ ሲሆን በ2012 በጀት ዓመት በድጋሚ ለማሳተም ተችሏል፡፡

### *ለ. የማህበረሰብ አገልግሎት*

ዩኒቨርሲቲው ይዟቸው ከተነሳቸው ተልዕኮዎች አንዱ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ ችግር ፈቺ አገልግሎቶችን መስጠት ሲሆን ለዚህም የህብረተሰቡን ችግሮች በጥናት በመለየትና ቅደም ተከተል በመስጠት በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችለውን አቅም ለመፍጠር ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

ባለፉት ዓመታት እያደገ የመጣ የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆን ለዚህም የማህበረሰብ አገልግሎት ጭብጦችን ለመለየት የሚስችል የዳሰሳ ጥናት በማካሄድና በውጤቱ ላይ ተመርኩዞ ከሚመለከታቸው የህዝብ ተወካዮችና የአስተዳደር አካላት ጋር በመወያየት ለችግሮቹ ቅደም ተከተል ሰጥቷል፡፡

በዚህ ላይ በመመስረትም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ወሎ እና በዋግኽምራ ብሔረሰብ አስተዳደር ዞኖች በ2012 በጀት ዓመት በማህበረሰብ አገልግሎቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ቁጥር 14,000 ለማድረስ ችሏል፡

ሆኖም በቀጣይ የእቅድ ዘመን ትኩረት ተሰጥቷቸው መሰራት እንዳለባቸው በእጥረት ከተገመገሙት ውስጥ የተሸጋገሩ አዳዲስና የተኮረጁ ቴክኖሎጂዎች ላይ አለመሰራቱ እንዲሁምበማማክር አገልግሎቶች ላይ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት አናሳ መሆናቸውና የምርምር ውጤቶችን ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር ተቆራኝቶ እንዲሄድ የማድረግ  ስራዎች ይገኙበታል፡፡

## 3.2 የውስጣዊና ውጫዊ /ጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚና ስጋት/ ዳሰሳ

### 3.2.1 ውስጣዊ ዳሰሳ

| | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|
| 1.መማር ማስተማር | • ትጉህና ተነሳሽነት ያለው የሰው ኃይል<br>• በቡድን የመስራት ባህል<br>• በአብዛኛዎቹ ት/ክፍሎች የተደራጁ ቤተ-ሙከራዎች መኖር<br>• ተግባር ተኮር የትምህርት አሰጣጥ መኖር<br>• ወጣትና ለለውጥ ዝግጁ የሆነ ሠራተኛ<br>• በየትምህርት ዘርፉ ቤተ-መፃህፍት መደራጀት<br>• በቂ መጻህፍት ያላቸዉ ቤተ-መጻህፍት መኖር<br>• የተደራጀ የተማሪዎች መረጃ አያያዝ ስርዓት መኖር<br>• መዋቅራዊ ለዉጥ መኖር<br>• ተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴ<br>• ጠንካራ የአመራር ምልመላና ምደባ ስርዓት መኖር<br>• ጠንካራ የስርዓተ-ትምህርት ቀረፃና ግምገማ ስርዓት መኖር<br>• ገበያ ተኮርና ችግር ፈች የትምህርት መስኮች መረጣ<br>• ጠንካራ የአገር ዉስጥ የአጭርና የረዥም ጊዜ | • የልምድ ማነስ<br>• የግብዓት አለመሟላት<br>• የተማሪ የማቋረጥ መጠን መጨመር<br>• የዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ ዉስንነት<br>• የትምህርት ጥራትና አግባብነት ቁጥጥር ደካማ መሆን<br>• የደንበኞች እርካታ አለመለካት<br>• መማር ማስተማሩን በቴክኖሎጂ አለመደገፍ<br>• የልህቀት ማዕከል ስነ-ምህዳር አለመፈጠር<br>• ትምህርት ላይ ያሉ መምህራን ላይ ክትትል ማነስ<br>• ተማሪዎችን የማማከር አገልግሎት ደካማ መሆን<br>• በሚፈለገው ዓይነትና ብዛት መምህራንና የቴክኒክ ረዳቶች አለመኖር<br>• ውስን የድህረ-ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞች መኖር<br>• የቅድመ-ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞች በሚፈለገዉ መጠን አለመስፋፋት<br>• ደረጃዉን የጠበቀ የቤተ-ሙከራ ሕንፃ አለመኖር<br>• የመረጃ አያያዝ ስርዓት አለመዘርጋት<br>• የሴት መምህራንና ቴክኒካል ረዳቶች ቁጥር አናሳ መሆን |

| | | |
|---|---|---|
| | ስልጠና መኖር<br>• የመምህራን ብቃትና ተወዳዳሪነት መጨመር<br>• ጠንካራ የተከታታይ ትምህርት ትግበራ መኖር<br>• የቅበላ አቅም ማደግ | • ተመራቂ ተማሪዎች ሊኖራቸዉ የሚገባዉ የስራ ዝግጁነት ክህሎት ስልጠና በቂ አለመሆን<br>• የተመራቂ ተማሪዎች የመቀጠር አቅም ምጣኔ አለመጠናት<br>• የስርዓተ-ትምህርት ክለሳ አለመደረግ<br>• ቤተ-ሙከራዎችን ወደ ስልጠና ማዕከልነት አለማሳደግ<br>• ዲጅታል ቤተ-መጻህፍት አለመኖር |
| 2 ጥናትና ምርምር | • በትምህርት ክፍሎች ዉስጥ በቡድን ምርምር የመስራት ባህል መኖር<br>• ለምርምር ስራ አሳታፊ የሆነ አሰራር መኖር<br>• ለምርምር ስራ ምቹ የሆነ መዋቅር መኖር<br>• ሊያሰራ የሚችል የምርምር መመሪያ መኖር<br>• የግብርና ምርምር ንድፈ-ሃሳቦች ግምገማ በፎረም መደረጉ<br>• የምርምር ንድፈ-ሃሳቦች ግምገማ በየደረጃዉ መደረጉ<br>• የምርምር የትኩረት አቅጣጫዎች የመከለስ ስራ መጀመር<br>• ተከታታይ የሆነ የፕሮሲዲንግ ሕትመት ስራ መሰራት<br>• የአገር በቀል እፅዋት ምርምር ጣቢያ መኖር | • የተመራማሪዎች ልምድ ማነስ<br>• መምህራን ጥናትና ምርምር ለመስራት ያላቸው ተነሳሽነት ማነስ<br>• የጥናትና ምርምር ማዕከል አለመኖር<br>• የሚመደበዉ የምርምር በጀት ማነስ<br>• የምርምር በጀትን በአግባቡ አለመጠቀም<br>• የምርምር ግብዓት አለመሟላት<br>• የስፔስ ሳይንስ ምርምር ማዕከሉን ወደ ስራ አለማስገባት<br>• በፋካልቲዎች መካከል በቡድን ምርምር የመስራት ባህል አለመኖር<br>• የምርምር ስራዎች በተያዘላቸዉ ጊዜ ተጠናቀዉ አለመግባት<br>• የምርምር ዉጤቶች ለማሕበረሰቡ ተደራሽ አለመሆን<br>• የጥናትና ምርምር ዩኒቶች አደረጃጀት አለመኖር<br>• በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሁሉን አሳታፊ የምርምር ግምገማ ሒደት አለመኖር |

| | | |
|---|---|---|
| | | • የምርምር ግምገማ ሒደት መጓተት<br>• የጆርናል ሕትመት አለመጀመር<br>• የተመራማሪዎች የሕተመት ማበረታቻ ስርዓት አለመኖር<br>• ከአጋር አካላት ጋር የሚሰራ የምርምር ፕሮጀክቶች ቁጥር ማነስ<br>• በተቋም ደረጃ በጥምረትና በከፍተኛ ክትትል የሚሰራ የምርምር ስራ አለመኖር |
| 3 የማኅበረሰብ አገልግሎት | • ዘላቂ የማኅበረሰብ አገልግሎት ስራዎች መጀመር<br>• የማሕበረሰብ አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ መኖር<br>• የማህ/አገልግሎት የትኩረት አቅጣጫዎች የመከለስ ስራ መጀመር<br>• በየደረጃዉ የግምገማ ስርዓት መኖር<br>• የሣይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂኔሪንግና ሒሳብ ማዕከል በከፊል መቋቋም<br>• የሣይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂኔሪንግ፣ ሒሳብና እንግሊዝኛ ትምህርት ለአንደኛና ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መሰጠቱ<br>• የምርጥ ዘር ቴክኖሎጂ ሽግግር መሰራቱ<br>• የምርምርና የማሕበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማስተዋወቅ መጀመር | • የማኅበረሰብ አገልግሎትን ፅንሰ-ሃሳብ በማሕበረሰቡ ዘንድ አለማስረፅ<br>• የሕግና የቢዝነስ ማማከር አገልግሎት አለመጠናከር<br>• የማሕበረሰብ አገልግሎት የበጀት ማዕከላዊነት<br>• ዘላቂና የተቀናጀ የማሕበረሰብ አገልግሎት ስራ አለመለየት<br>• መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ያለን ግንኙነት አነስተኛ መሆን<br>• የማሕበረሰብ አገልግሎት ከምርምርና ሌሎች ጽ/ቤቶች ጋር የቅንጅት ማነስ<br>• የመዋቅር ችግር<br>• የስልጠና መስጫ ማዕከል አለመኖር<br>• ሐብት የማፈላለግ ልምድ ማነስ<br>• የሴቶች ተሳትፎ አነስተኛ መሆን<br>• የፕሮጀክት ተፅዕኖ ግምገማ አለመካሄድ |

| | | |
|---|---|---|
| | | • መምህራን የማሕበረሰብ አገልግሎትን የስራቸዉ አካል አድርጎ አለመቁጠር<br>• ተደራሽነቱ አነስተኛ የሆነ የማሕበረሰብ አገልግሎት አሰጣጥ<br>• ተማሪዎችን አሳታፊ ያልሆነ የማሕበረሰብ አገልግሎት አሰጣጥ<br>• የበጀት እጥረት |
| 4 አስተዳደር | • ተቋማዊ ለውጥ ለማምጣት የሚታይ ፍላጎት<br>• ፍትሃዊ የሆነ የቅጥርና የደረጃ ዕድገት የአሰራር ስርዓት መኖር<br>• የተገኙ ተሞክሮዎችን የመተግበር ተነሳሽነት<br>• ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች መቋቋምና ስራ ላይ መዋል<br>• ስራዎችን ለሶስተኛ ወገን መስጠት<br>• የፋይናንስ ግልፀኝነት መኖር<br>• ተግዳሮትን ተቋቁሞ የመስራት ልምድና ባህል መዳበር<br>• ለስራ መደቡ የሚመጥን በቂ የትምህርት ዝግጅትና ልምድ ያለዉ ወጣት ሰራተኛ መኖር<br>• መልካም የእርስበርስ ግንኙነት መኖር<br>• ተልዕኮን ለመቀበል ዝግጁ የሆነ ሰራተኛ መኖር<br>• የራስን አቅም የማጎልበት ተነሳሽነት መኖር<br>• ጥሩ የመሰረተ-ልማት ግንባታ መኖር | • ደካማ የንብረት አስተዳደርና ቁጥጥር መኖር<br>• የኮሚቴ ስራዎች በአግባቡ አለመመራትና የመደበኛ ስራ አካል ተደርገዉ አለመታየት<br>• ወጥ የሆነ የሰራተኛ አፈፃፀም ምዘና ስርዓት አለመኖር<br>• ተደጋጋሚ የአመራር ለዉጥና በቂ የስራ ርክክብ አለመኖር<br>• ደካማ የሕዝብና የውጭ ግንኙነት መኖር<br>• የስራ ኃላፊነትን በሚገባ አለመወጣት<br>• ደካማ የቁጥጥርና የተጠያቂነት ስርዓት መኖር<br>• በዕቅድ አለመመራት<br>• የካይዘን አሰራር ስርዓት አለመተግበር<br>• የአመራር አካላት ልምድ ማነስና የተቋሙን የስራ ባህሪ አለመረዳት<br>• የተደራጀ የመረጃ ስርዓት በየክፍሉ አለመኖር<br>• ክፍሎች በመረጃ ግንኙነት ስርዓት አለመደገፍ<br>• የግዥ አፈፃፀም ችግር/የእቃዎች ጥራትና የግዥው ወቅታዊነት/<br>• የመዋቅር ችግር መኖር<br>• ተቋማዊና የስራ ክፍሎች የዉስጥ አሰራር ስርዓት አለመዘርጋት |

| | | |
|---|---|---|
| | | • ተቋማዊ የለዉጥ ስራዎች በአግባቡ አለመመራት<br>• የተማከለ የአሰራር ስርዓት መኖር<br>• ደካማ የማማከርና ሕግ አገልግሎት<br>• ደካማ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ቁጥጥር<br>• ደካማ የግንባታ ርክክብ፣ ጥገናና ዕድሳት<br>• ደካማ ቅድመ እና ድህረ ግንባታ ግምገማ<br>• የሕንፃዎች ግንባታ ኢንተርኔት መሰረተ-ልማት አለመካተት<br>• የግንባታ ስራዎች በተቀመጠዉ ጊዜ አለመጠናቀቅ<br>• ተቋማዊ የአኔነት ስሜት መዳከምና አለመርካት<br>• ደካማ የሆነ የግቢ ዉበት እንክብካቤ<br>• የይዞታ ማስከበርና ማስፋፋት ችግር<br>• ምቹ የስራ አካባቢ አለመኖር/የሕፃናት ማቆያ፣ የቢሮ ጥበት፣ የካፍቴሪያ አገልግሎት/ |
| 5 **የተማሪዎች አገልግሎት** | • የተማሪዎችና የተማሪ ተወካዮች ንቁ ተሳትፎ<br>• ለተማሪዎች የሚደረጉ ድጋፎች (ለሴት ተማሪዎች፣ የኢኮኖሚ ችግር ላለባቸዉ ተማሪዎችና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች)<br>• የተማሪዎች መሰረታዊ አገልግሎቶች መሟላት<br>• የተማሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መኖር | • በቂ የሆነ የህክምና አገልግሎት አለመኖር<br>• የተማሪዎች የማማከር አገልግሎት አለመኖር<br>• በኤች አይቪ ኤድስና ስነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎት ስራዎች አነስተኛ መሆን<br>• የተማሪዎች የመዝናኛ አገልግሎት አርኪ አለመሆን<br>• በተወሰኑ የተማሪዎች መገልገያ ሕንፃዎች የሽንት ቤትና የሻወር ቤቶች በትክክል አለመስራት<br>• በቂና ጠንካራ ክበባት አለመኖር<br>• ወጭ ቆጣቢ አሰራር አለመከተል |

| | | |
|---|---|---|
| | | • በቂ ክትትልና ቁጥጥር አለመኖር<br>• የካይዘን አሰራር ስርዓት አለመተግበር<br>• የተማሪዎች የመረጃ ስርዓትን በአግባቡ አለመጠቀም<br>• ተማሪ ተኮር የመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት እጥረት |
| 6 **ሐብት ማፈላለግና ማመንጨት** | • የቅድመ-ምረቃ ተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም መጠናከር<br>• የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋም መቻል<br>• በጥምረት የሚሰሩ ፕሮጀክቶችን መሳብ መጀመር<br>• ዲዛይንና ማማከር አገልግሎት መመሪያ መፅደቅ<br>• ለገቢ ማመንጫ ስራ የሚዉሉ ሕንፃዎችና መሬት መኖር | • መዋቅራዊ ችግር /የገቢና ሃብት ማመንጫ ዳይሬክቶሬትና የኢንተርፕራይዝ የስራ ድርሻ መደበላለቅ/<br>• ስትራቴጂያዊ የትኩረት ማነስ<br>• አካባቢያዊ ምቹ ሁኔታዎችን አለመጠቀም<br>• ከውጭ አካላት ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለመኖር<br>• ግልፀኝነት የጎደለዉ የፋይናንስ ስርዓት መኖር<br>• የሐብት ብክነት መኖር<br>• ያሉንን ባለሙያዎች መሰረት ያላደረገ የሐብት ማፈላለግ<br>• ሐብት ማመንጨት የሚችሉ ክፍሎችን ለዚሁ ተግባር አለመጠቀም |

## 3.2.2. ውጫዊ ዳሰሳ

| | መልካም አጋጣሚዎች | ስጋት |
|---|---|---|
| 1 ፖለቲካዊ | • መንግስት የትምህርትን ተደራሽነትና ጥራትን ለማስጠበቅ ያለው ቁርጠኝነት<br>• የከፍተኛ ትምህርትን ለማጎልበት የድጋፍ ፕሮግራሞች በመንግስት መቀመጣቸው<br>• አሳታፊነት<br>• ባለ ዘረፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ ትኩረት መስጠቱ<br>• ሊያሰሩ የሚችሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች መኖር<br>• የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና የህግ ማእቀፍ መዘርጋቱ<br>• የአገሪቱ የአስር ዓመት መሪ እቅድ በየዘርፉ መዘጋጀት<br>• ሁሉን አቀፍ አገራዊ ለዉጥ ለማምጣት ጥረት መጀመሩ<br>• ሉላዊነት እያደገ መምጣቱ<br>• ጠንካራ ዓለም-አቀፋዊ የዲፕሎማሲ ግንኙነት መኖር | • ስር የሰደደ ሙስና<br>• ነባራዊ ሁኔታን ያላገናዘቡ ደንቦች መመሪያዎች መኖራቸው<br>• የትምህርት ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ተቃያያሪ መሆን<br>• የአገሪቱ የፖለቲካ አለመረጋጋት |
| 2 ኢኮኖሚያዊ | • ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት መኖር<br>• አበረታች የሆነ ገበያ መር የኢኮኖሚ ስርዓት መኖር<br>• ብዛት ያለው አምራች የሰው ኃይል መኖር<br>• ሰፊ ለልማት የሚውል መሬት መኖር<br>• የተፈጥሮ ሀብትና ታሪካዊ ቅርሶች መኖር<br>• ዓመታዊ የበጀት እድገት | • አጥጋቢ የደመወዝ እርከንና መጠን አለመኖር<br>• የዋጋ ግሽበት/ የኑሮ ውድነት<br>• የዓለም ኢኮኖሚ አለመረጋጋት<br>• አበረታች የብድር አገልግሎት አለመኖር<br>• የሰው ኃይል ገበያው በሚፈለገው መጠን አለማደግ<br>• በቂ በጀት አለመመደብ<br>• የወልድያ ከተማ ዕድገት ዝቅተኛ መሆን<br>• አካባቢያዊ የኢንዱስተሪና ኢንቨስትመንት ዕድገት አለመኖር |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2 | ማኅበራዊ | • ማኅበረሰቡ ለዩኒቨርሲቲው ያለው ጥሩ አመለካከት<br>• እየጨመረ የመጣው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትስስር<br>• ባህላዊ፣ ታሪካዊና ሐይማኖታዊ እሴቶች መኖራቸው<br>• የአብሮነት ባህል መኖር<br>• በዩኔስኮ የተመዘገቡ ቅርሶች መኖር | • ደካማ የስራና የስራ ፈጠራ ባህል መኖር<br>• ከፍተኛ የህዝብ ቁጥርና ዕድገት መኖር<br>• የከተማዋ ማህበራዊ ዕድገት ዝቅተኛ መሆን<br>• ስራ አጥነት<br>• ከተማዋ ለኤች አይ ቪ ተጋላጭ መሆን<br>• ሱሰኝነት<br>• የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት መጓደል |
| 3 | አካባቢያዊ | • አካባቢው ለግብርና ስራዎች ምቹ መሆኑ<br>• አካባቢዉ ለሕዋ ሣይንስ ምርምር ስራ ምቹ መሆኑ<br>• በአካባቢው የቱሪስት መስህብ የሆኑ ቦታዎች መኖር<br>• የወልድያ ከተማ አካባቢያዊ አቀማመጥ ምቹ መሆን<br>• የባቡር መስመር በአቅራቢያው እየተዘረጋ መሆኑ<br>• የዘመናዊ ስቴድየም መኖር<br>• የከርሰ-ምድር ዉኃ ሃብት መኖር | • መልካምድራዊ አቀማመጡ አካባቢዉን ለማልማት ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ መሆኑ<br>• ዓለም-አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ<br>• ተደጋጋሚ የድርቅ መከሰት<br>• የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት አለመኖር |
| 4 | ቴክኖሎጅ | • የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እያደገ መሄድ<br>• የኮንስትራክሽን ዘርፍ እያደገ መሄድ<br>• የICT በፍጥነት መስፋፋት<br>• የዲጅታል ኢኮኖሚ ስትራቴጂ መነደፍ<br>• የህዋ ምርምር ጣቢያ በአካባቢዉ መኖር<br>• የመስኖ ቴክኖሎጅ መስፋፋት<br>• የቴክኖሎጅ ሽግግር እያደገ መሄድ<br>• መንግስት ለሳይንስና ቴክኖሎጅ የሰጠው ልዩ ትኩረት | • የህብረተሰቡ አዳዲስ የቴክኖሎጅ ውጤቶችን ለመቀበል ያለው አቅምና ባህል አናሳ መሆን<br>• ICTን ለማስፋፋት የሚጠይቀው መዋዕለ-ንዋይ ከፍተኛነት<br>• በቴክኖሎጅው ዘርፍ የብቁ ባለሙያ እጥረትና የአቅም ውስንነት<br>• በአገር ዉስጥ ዉስን የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችና ማሰልጠኛ ተቋማት መኖር<br>• የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎትና ሙያዊ ድጋፍ ዉስንነት |

### 3.2.3. አስቻይ ሁኔታዎች /ጥንካሬ + መልካም አጋጣሚ/

### 2.4.2. ፈታኝ ሁኔታዎች

| ጥንካሬ | መልካም አጋጣሚ |
|---|---|
| • ተነሳሽነት ያለውና ተግዳሮትን ተቋቁሞ የሚሰራ የሰው ኃይል<br>• ጠንካራ የእርስበርስ ግንኙነትና በቡድን የመስራት ባህል<br>• ተማሪ-ተኮርና ተግባር-ተኮር በመርጃ መሳሪያ የተደገፈ የትምህርት አሰጣጥ መኖር<br>• ወጣትና እራሱን ለማብቃት ዝግጁ የሆነ ሠራተኛ<br>• በየትምህርት ዘርፉ የተደራጁና በቂ መጻህፍት ያላቸዉ ቤተ-መፃህፍት መኖር<br>• በአብዛኛዎቹ ት/ክፍሎች የተደራጁ ቤተ-ሙከራዎች መኖር<br>• መዋቅራዊ ለዉጥ መኖር<br>• ገበያ ተኮርና ችግር ፈች የትምህርት መስኮች መረጣ<br>• የመምህራን ብቃትና ተወዳዳሪነት መጨመር<br>• የተማሪዎች መሰረታዊ አገልግሎት መኖር<br>• የተደራጀ የተማሪዎች መረጃ አያያዝ ስርዓት መኖር<br>• በተወሰኑ ዘርፎች ጠንካራ የአሰራር ስርዓት መኖር<br>• ጠንካራ የአገር ዉስጥ የአጭርና የረዥም ጊዜ ስልጠና መኖር<br>• ጠንካራ የመጀመሪያ ዲግሪ ተከታታይ ትምህርት ትግበራ መኖር<br>• የተማሪ ቅበላ አቅም ማደግ | • መንግስት የትምህርትን ተደራሽነትና ጥራትን ለማስጠበቅ ያለው ቁርጠኝነት<br>• የከፍተኛ ትምህርትን ለማጎልበት የድጋፍ ፕሮግራሞች በመንግስት መቀመጣቸው<br>• አሳታፊነት<br>• ባለ ዘረፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ ትኩረት መሰጠቱ<br>• ሊያሰሩ የሚችሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች መኖር<br>• የስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና የህግ ማእቀፍ መዘርጋቱ<br>• የአገሪቱ የአስር ዓመት መሪ እቅድ በየዘርፉ መዘጋጀት<br>• ሁሉን አቀፍ አገራዊ ለዉጥ ለማምጣት ጥረት መጀመሩ<br>• ሉላዊነት እያደገ መምጣቱ<br>• ጠንካራ ዓለም-አቀፋዊ የዲፕሎማሲ ግንኙነት መኖር<br>• ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት መኖር<br>• አበረታች የሆነ ገበያ መር የኢኮኖሚ ስርዓት መኖር<br>• ብዛት ያለው አምራች የሰው ኃይል መኖር<br>• ሰፊ ለልማት የሚውል መሬት መኖር |

| | |
|---|---|
| • የምርምርና የማሕበረሰብ አገልግሎት የትኩረት አቅጣጫዎች መከለስ<br>• የአገር በቀል እፅዋት ምርምር ጣቢያ መኖር<br>• ዘላቂ የማኅበረሰብ አገልግሎት ስራዎች መጀመር<br>• ስራዎችን ለሶስተኛ ወገን መስጠት<br>• የፋይናንስ ግልፀኝነት መኖር<br>• ተቋማዊ ለውጥ ለማምጣት የሚታይ ፍላጎት<br>• የተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ<br>• የገቢ ማመንጫ ኢንተርፕራይዝ ማቋቋም<br>• ለገቢ ማመንጫ ስራ የሚዉሉ ሕንፃዎችና መሬት መኖር<br>• አሳታፊ የሆነ አሰራር መኖር<br>• ተከታታይ የሆነ የፕሮሲዲንግ ሕትመት ስራ መሰራት<br>• የሣይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ኢንጂኔሪንግና ሒሳብ ማዕከል በከፊል መቋቋምና ስራ ላይ መዋል<br>• የምርምርና የማሕበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን ማስተዋወቅ መጀመር<br>• ጥሩ የመሰረተ-ልማት ግንባታ መኖር | • የተፈጥሮ ሀብትና ታሪካዊ ቅርሶች መኖር<br>• ዓመታዊ የበጀት እድገት<br>• ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት መኖር<br>• ማኅበረሰቡ ለዩኒቨርሲቲው ያለው ጥሩ አመለካከት<br>• እየጨመረ የመጣው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትስስር<br>• ባህላዊ፣ ታሪካዊና ሐይማኖታዊ እሴቶች መኖራቸው<br>• የአብሮነት ባህል መኖር<br>• በዩኔስኮ የተመዘገቡ ቅርሶች መኖር<br>• የወልድያ ከተማ ስትራቴጃዊ አቀማመጥ<br>• የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እያደገ መሄድ<br>• የኮንስትራክሽን ዘርፍ እያደገ መሄድ<br>• የICT መስፋፋት<br>• የህዋ ምርምር ጣቢያ በአካባቢዉ መኖር<br>• የመስኖ ቴክኖሎጅ መስፋፋት<br>• የቴክኖሎጅ ሽግግር እያደገ መሄድ<br>• መንግስት ለሳይንስና ቴክኖሎጅ የሰጠው ልዩ ትኩረት |

## ፈታኝ ሁኔታዎች /ድክመት + ስጋት/

| ድክመት | ስጋት |
|---|---|
| • የልምድ ማነስ | • ስር የሰደደ ሙስና |
| • በዕቅድ አለመመራት | • ነባራዊ ሁኔታን ያላገናዘቡ ደንቦች መመሪያዎች መኖራቸው |
| • የመዋቅር ችግር | • የትምህርት ስትራቴጂዎችና ፕሮግራሞች ተቃያያሪ መሆን |
| • ደካማ ቁጥጥርና ተጠያቂነት | • የአገሪቱ የፖለቲካ አለመረጋጋት |
| • የደንበኞች እርካታ አለመለካት | • የደመወዝ እርከንና መጠን ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ አለመሆን |
| • የግብዓት አለመሟላት | • የዋጋ ግሽበት/ የኑሮ ውድነት |
| • የተማሪ የማቋረጥ መጠን መጨመር | • የዓለም ኢኮኖሚ አለመረጋጋት |
| • ተማሪዎችን የማማከር አገልግሎት ደካማ መሆን | • አበረታች የብድር አገልግሎት አለመኖር |
| • የልህቀት ማዕከል ስነ-ምህዳር አለመፈጠር | • የሰው ኃይል ገበያው በሚፈለገው መጠን አለማደግ |
| • መምህራን በሚፈለገው የትምህርት ደረጃና ብዛት አለመኖር | • በቂ በጀት አለመመደብ |
| • ደረጃዉን የጠበቀ የቤተ-ሙከራ ሕንፃ አለመኖር | • የወልድያ ከተማ ዕድገት ዝቅተኛ መሆን |
| • ውስን የድህረ-ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞች መኖር | • አካባቢያዊ የኢንዱስተሪና ኢንቨስትመንት ዕድገት አለመኖር |
| • ተመራቂ ተማሪዎች ሊኖራቸዉ የሚገባዉ የስራ ዝግጁነት ክህሎት ስልጠና በቂ አለመሆን | • ደካማ የስራ ባህልና የስራ ፈጠራ ባህል |
| | • ከፍተኛ የህዝብ ቁጥርና ዕድገት መኖር |
| • የተመራቂ ተማሪዎች የመቀጠር አቅም ምጣኔ አለመጠናት | • ስራ አጥነት |
| • የስርዓተ-ትምህርት ክለሳ አለመደረግ | • ከተማዋ ለኤች አይ ቪ ተጋላጭ መሆን |
| • ቤተ-ሙከራዎችን ወደ ስልጠና ማዕከልነት አለማሳደግ | • የሰብዓዊነትና የማሕበራዊ ዕሴት መዳከም |

| | |
|---|---|
| • የቅድመ-ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞች በሚፈለገዉ መጠን አለመስፋፋት<br>• የሴት ሰራተኞችና አመራሮች ቁጥር አናሳ መሆን<br>• የተደራጀ የመረጃ ስርዓት በየክፍሉ አለመኖር<br>• ተቋማዊ የመረጃ ግንኙነት ስርዓት አለመዘርጋት<br>• የጥናትና ምርምር ማዕከል አለመኖር<br>• የበጀት እጥረት<br>• የማኅበረሰብ አገልግሎትን ፅንሰ-ሃሳብ በማሕበረሰቡ ዘንድ አለማስረፅ<br>• ዘላቂና የተቀናጀ የማሕበረሰብ አገልግሎት ስራ አለመለየት<br>• የምርምር ዉጤቶች ለማሕበረሰቡ ተደራሽ አለመሆን<br>• የጆርናል ማተም ስራ አለመጀመር<br>• ከአጋር አካላት ጋር የሚሰራ የምርምር ፕሮጀክቶች ቁጥር ማነስ<br>• በተቋም ደረጃ በጥምረትና በከፍተኛ ክትትል የሚሰራ የምርምር ስራ አለመኖር<br>• ደካማ የንብረት አስተዳደርና ቁጥጥር<br>• ደካማ የሕዝብና የውጭ ግንኙነት<br>• የግዥ አፈፃፀም ችግር/የእቃዎች ጥራትና የግዥው ወቅታዊነት/<br>• የስራ ክፍሎች የአሰራር ስርዓት ሙሉ ለሙሉ አለመዘርጋት<br>• ተቋማዊ የለዉጥ ስራዎች በአግባቡ አለመመራት | • የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት መጓደል<br>• መልካምድራዊ አቀማመጡ አካባቢዉን ለማልማት ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ መሆኑ<br>• ዓለም-አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ<br>• ተደጋጋሚ የድርቅ መከሰት<br>• የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት አለመኖር<br>• የህብረተሰቡ አዳዲስ የቴክኖሎጅ ውጤቶችን ለመቀበል ያለው አቅምና ባህል አናሳ መሆን<br>• ICTን ለማስፋፋት የሚጠይቀው መዋዕለ-ንዋይ ከፍተኛነት<br>• በቴክኖሎጅው ዘርፍ የብቁ ባለሙያ እጥረትና የአቅም ውስንነት<br>• በአገር ዉስጥ ዉስን የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችና ማሰልጠኛ ተቋማት መኖር<br>• የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎትና ሙያዊ ድጋፍ ዉስንነት |

| | |
|---|---|
| • የተማከለ የአሰራር ስርዓት መኖር<br>• የሕግና የቢዝነስ ማማከር አገልግሎት አለመጠናከር<br>• የስልጠና መስጫ ማዕከል አለመኖር<br>• ሐብት የማፈላለግ ልምድ ማነስ<br>• የፕሮጀክት ተፅዕኖ ግምገማ አለመካሄድ<br>• መምህራን የማሕበረሰብ አገልግሎትን የስራቸዉ አካል አድርጎ አለመቁጠር<br>• ተደራሽነቱ አነስተኛ የሆነ የማሕበረሰብ አገልግሎት አሰጣጥ<br>• ተማሪዎችን አሳታፊ ያልሆነ የማሕበረሰብ አገልግሎት አሰጣጥ<br>• የባለዘርፈ ብዙ ጉዳዮች አገልግሎት አነስተኛ መሆን<br>• በቂና ጠንካራ ክበባት አለመኖር<br>• ወጭ ቆጣቢ አሰራር አለመከተል<br>• የገቢ ማመንጫ ስራዎችና የአሰራር ስርዓት ደካማ መሆን | |

## 3.4 የተወሰዱ እርምጃዎች

ዩኒቨርስቲው ያሉትን መልካም አጋጣሚዎች የበለጠ በማጠናከር ለመጠቀም እንዲሁም ስጋቶቹ በተያዘው እቅድ ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ ያስችል ዘንድ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

- የሰው ሃብት ልማት ፕሮግራምን ተግባራዊ በማድረግ የመምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች እና የአመራር ልማት ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ማድረግ፣
- በተቋማዊ ለውጥ ማሻሻያ ፕሮግራም በጥናት የተደገፉ ፖሊሲዎችን፣ መመሪያዎችንና ደንቦችን የማውጣት፣ የመተግበርና የማሻሻል እንዲሁም የለውጥ ማስተግበሪያ መሳሪያዎች ስራ ላይ ማዋል፣
- የግንባታና መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ስራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል
- የትምህርት ፕሮግራሞችን ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊ በማድረግ የትምህርት ፕሮግራሞች ማስፋፋት፣ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ አመላካቾችን ማሟላት፣ የተመራቂ ተማሪዎች አቅም ማጎልበቻ ስራዎችን መስራትና በኤሌክትሮኒክ የተደገፉ ትምህርቶች ለመስጠት የሚያስችል ስራ መስራት
- የባለዘርፈ- ብዙ ጉዳዮች ማስፈፀምያ ፕሮግራምን ተግባራዊ በማድረግ የስርዓተ ጾታ፣ የተላላፊ በሽታዎች መከላከያና መቆጣጠር እንዲሁም የልዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ላይ ትኩተረት የመስጠት
- የግንኙነትና አጋርነት ለማሳደግ የሚያስችሉ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ግንኙነትን ማስፋፈት፣ የእርስ በእርስ ግንኙነት ክህሎትን የማጎልበቻ ስልጠና የመስጠት እንዲሁም የትብብር መስኮችን የመለየትና ተግባራዊ የማድረግ ስራ መስራት፣
- የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የጥናትና ምርምር እና የቴክኖሎጂ ሽግግርና የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር ስራዎችን መስራት
- ሰላምና ደህንነትን ለማስፈን የሚረዳ በውስጡም የመቻቻል ባህልን የማጎልበት፣ የሰላም ፎረምን የማጠናከር፣ የግጭት አፈታት ስርዓትን የመዘርጋትና የመተግበር፣ ከአካባቢው የጸጥታ ኃይሎችጋር ተቀናጅቶ የመስራት፣ የጥበቃ አገልግሎትን ማጠናከርን እንዲሁም

በአካባቢ የሚገኙ የግጭት መንስኤዎችን መለየትና መፍትሄ የማፈላለግ ተግባራትን በዋናነት ማከናወን።

- የውስጥ ቁጥጥርና የአሰራር ስርዓት መዘርጋትና ተፈጻሚ ማድረግ

## 3.5 የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ ዕሴቶች እና መሪ ቃል

ዩኒቨርሲቲው መንግስት የጣለበትን ኃላፊነት በሚገባ ለመወጣት ያስችለው ዘንድ የተሰጠውን ተልዕኮ የመፈተሸና በልምድ ያልደረጀ ከመሆኑ አንጻር በአምስት ዓመታት ውስጥ ምን መሆን እንደሚፈልግ በግልጽ ማስቀመጥ ያለበት በመሆኑ እንዲሁም በተቋሙ ውስጥ የሰረጹና መስረጽ ያለባቸው እምነቶች፣ አስተሳሰቦችና አመለካከቶች ምን መሆን እንዳለባቸው በጥልቀት በመመልከት ተልዕኮ፤ ራዕይና ዕሴቶቹን አስቀምጧል።

**ተልዕኮ፡-**

ለአገራችን ህዝብ ኑሮ መሻሻልና ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ በዕውቀት፣ በክሎትና በስነ-ምግባር የታነጹ ባለሙያዎችን ማፍራት፣ ችግር ፈቺ ጥናትና ምርመሮችን መስራትና ተደራሽ ማድረግ እንዲሁም ፋይዳ ያለዉና ዘርፈ-ብዙ የማኅበረሰብ አገልግሎት መስጠት።

**ራዕይ፡-**

በ2022 ዓ.ም በኢትዮጵያ ካሉ አምስት ተመራጭ የትምህርት እና የምርምር ተቋማት አንዱ ሆኖ ማየት

**ዕሴቶች፡-**

- ጥራት ያለዉ አገልግሎት መስጠት
- ተገልጋይ-ተኮር አሰራርን መከተል
- በቡድን መስራት
- ተወዳዳሪነት
- የባለቤትነት ስሜት
- አሳታፊ አሰራርን መከተል
- የተገልጋይን ደህንነት መጠበቅ
- ሙያዊነትን መላበስ
- በአንድነት ዉስጥ ያለ ልዩነትን ማክበር
- ፍትሃዊ አሰራርን መከተል
- ተግባርን በቅልጥፍና ማከናወን
- ስራን በትጋት መፈፀም

**የዩኒቨርሲቲው መሪ ቃል**

አዕምሮ ሲከፈት ዓይኖች ማየት ይችላሉ

## 3.6 ተገልጋዮችንና ባለድርሻ አካላትን መለየትና ፍላጎታቸውን መተንተን

### 3.6.1 ተገልጋዮችንና ባለድርሻ አካላትን መለየት

**የውስጥ ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት**

- የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ሰራተኞች
- የወልድያ ዩኒቨርሲቲ አመራር አካላት
- የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ስራ አመራር ቦርድ አባላት

**የውጭ ተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት**

- ተማሪዎች
- ማኅበረሰቡ
- ሣይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
- ገንዘብ ሚኒስቴር
- የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት
- የት/ጥ/አግባብነት ኤጀንሲ
- ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
- የከፍተኛ ት/ት እና የምርምር ተቋማት
- ጤና ሚኒስቴር
- የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሚኒስቴር
- ኢንዱስትሪዎች
- የአማራ ክልል መንግስት
- ቀጣሪ ድርጅቶችና መስሪያ ቤቶች
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
- የትምህርት ስትራቴጅክ ማዕከል

### 3.6.2 የተቋሙና የተገልጋይ/ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት ማነፃፀሪያ

| ተ.ቁ | ተገልጋይ/ባለድርሻ አካል | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው ባህሪያት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከተቋሙ የሚፈልጉት ምርት/አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት በተቋሙ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች | የተፅዕኖው ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **የዉጭ ተገልጋይ /ባለድርሻ አካላት** | | | | |
| 1 | ተማሪዎች | • መልካም ስነ-ምግባር<br>• ተነሳሽነት<br>• ብቃት/ጥሩ ዝግጅት<br>• ንቁ ተሳትፎ<br>• ትጋት<br>• ህጋዊነትና ምክንያታዊነት | • ጥራት ያለው ትምህርት<br>• ፍትሀዊና ቀልጣፋ አገልግሎት<br>• በቂ ግብዓት<br>• ምቹ የትምህርት አካባቢ | • ገፅታ መበላሸት<br>• የእኔነት ስሜት አለመፈጠር<br>• ተልዕኮ አለመሳካት | ከፍተኛ |
| 2 | ማኅበረሰቡ | • ንቁ ተሳትፎ<br>• ቅንነት<br>• ትብብር<br>• የባለቤትነት ስሜት | • አግባብነትና ጥራት ያለው፣ ችግር ፈች የማኅበረሰብ አገልግሎት<br>• የአካባቢውን ባህል ማክበር | • ተልዕኮ አለመሳካት<br>• ገፅታ መበላሸት | ከፍተኛ |
| 3 | ሣይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር | • ያልተማከለ አሰራር<br>• ወቅታዊ መረጃ<br>• በዕቅድ መመራት<br>• ፍትኃዊነት<br>• የአቅም ግንባታ ስራ | • ተልዕኮን ማሳካት<br>• መመሪያና ደንቦችን መፈጸም<br>• መልካም አስተዳደር<br>• ወቅታዊ መረጃ | • ዕምነት ማጣት<br>• የድጋፍ መቀነስ<br>• የአመራር ለውጥ<br>• ትኩረት ማጣት | ከፍተኛ |
| 4 | ገንዘብ ሚኒስቴር | • ያልተማከለ አሰራር<br>• በቂና ወቅታዊ የበጀት ምደባ<br>• ግልፅና ሊያሰሩ የሚችሉ የፋይናንስ መመሪያና ደንቦች<br>• ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ የአሰራር ስርዓት<br>• የአቅም ግንባታ ስራ | • ጥሩ የሀብት አጠቃቀም<br>• ወቅታዊ መረጃ/ሪፖርት<br>• ከሙስና የፀዳ አሰራር<br>• የፋይናንስ መመሪያና ደንቦችን መፈጸምና | • የስራ መስተጓጎል<br>• በጀት ቅነሳ<br>• እምነት ማጣት | ከፍተኛ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት | • ያልተማከለ አሰራር<br>• ወቅታዊ ግብረመልስ<br>• በዕቅድ መመራት<br>• ፍትኃዊነት<br>• የአቅም ግንባታ ስራ | • ተልዕኮን ማሳካት<br>• መመሪያና ደንቦችን መፈጸም<br>• መልካም አስተዳደር<br>• ወቅታዊ መረጃ<br>• አሰራሮችን ማሻሻል | • ዕምነት ማጣት<br>• የድጋፍ መቀነስ<br>• የአመራር ለውጥ<br>• ትኩረት ማጣት | ከፍተኛ |
| 6 | የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ | • ወቅታዊ መረጃ<br>• በዕቅድ መመራት<br>• ፍትኃዊነት<br>• የአቅም ግንባታ ስራ | • ተልዕኮን ማሳካት<br>• መመሪያና ደንቦችን መፈጸም<br>• መልካም አስተዳደር<br>• ወቅታዊ መረጃ | • ዕምነት ማጣት<br>• የድጋፍ መቀነስ<br>• ትኩረት ማጣት | ከፍተኛ |
| 7 | ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | • ነባራዊ ሁኔታን ያገናዘበ የአሰራር ስርዓት<br>• ያልተማከለ አሰራር | • አዋጆች፣ መመሪያዎችና ደንቦችን መተግበር<br>• ብቁና ተወዳዳሪ ምሩቃን<br>• ወቅታዊ መረጃ | • የስራ መስተጓጎል<br>• እምነት ማጣት | መካከለኛ |
| 8 | የከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት | • አጋርነት<br>• መልካም ግንኙነት<br>• ልምድን መጋራት | • አጋርነት<br>• መልካም ግንኙነት<br>• ልምድን መጋራት | • መገለል<br>• ድጋፍ ማጣት<br>• የዕድገት መገታት | መካከለኛ |
| 9 | ጤና ሚኒስቴር | • አግባብነት/ሕጋዊነት<br>• መልካምና ቀልጣፋ አስተዳደር<br>• ተነሳሽነት<br>• የጋራ ግብ | • መልካም አስተዳደር<br>• አጋርነት<br>• ፍትኃዊነት<br>• ቀልጣፋ አሰራር | • የትብብር ማነስ<br>• ገፅታ መበላሸት<br>• አለመታመን<br>• የጋራ ግብ አለመሳካት | መካከለኛ |
| 10 | ቴክኖሎጅና ኢኖቬሽን ሚኒስቴር | • አግባብነት/ሕጋዊነት<br>• መልካምና ቀልጣፋ አስተዳደር<br>• ተነሳሽነት<br>• የጋራ ግብ | • መልካም አስተዳደር<br>• አጋርነት<br>• ፍትኃዊነት<br>• ቀልጣፋ አሰራር | • የትብብር ማነስ<br>• ገፅታ መበላሸት<br>• አለመታመን<br>• የጋራ ግብ አለመሳካት | መካከለኛ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ኢንዱስትሪዎች | • አግባብነት/ሕጋዊነት<br>• መልካምና ቀልጣፋ አስተዳደር<br>• ተነሳሽነት<br>• የጋራ ግብ | • መልካም አስተዳደር<br>• አጋርነት<br>• ፍትኃዊነት<br>• ቀልጣፋ አሰራር | • የትብብር ማነስ<br>• ገፅታ መበላሸት<br>• አለመታመን<br>• የጋራ ግብ አለመሳካት | መካከለኛ |
| 12 | የአማራ ክልል መንግስት | • አጋርነት<br>• ቁርጠኝነት<br>• መልካም አስተዳደር | • ችግር ፈች ጥናትና ምርመርና የማህበረሰብ አገልግሎት<br>• አቅም ግንባታ<br>• አጋርነት | • ድጋፍ ማጣት<br>• መገለል<br>• ገፅታ መበላሸት | መካከለኛ |
| 13 | ቀጣሪ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች | • አጋርነት<br>• ፍትሀዊነት<br>• የመቅጠር አቅም<br>• ገንቢ ግብረ መልስ | • ብቁና ተወዳዳሪ ምሩቃን<br>• ቀልጣፋና ፍትህ አገልግሎት<br>• አጋርነት<br>• ወቅታዊ መረጃ | • ተቀባይነት/ ተመራጭነት ማጣት<br>• ገፅታ መበላሸት | መካከለኛ |
| 14 | መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | • አግባብነት/ሕጋዊነት<br>• መልካምና ቀልጣፋ አስተዳደር<br>• ተነሳሽነት<br>• የጋራ ግብ | • መልካም አስተዳደር<br>• አጋርነት<br>• ፍትኃዊነት<br>• ቀልጣፋ አሰራር | • የትብብር ማነስ<br>• ገፅታ መበላሸት<br>• አለመታመን<br>• የጋራ ግብ አለመሳካት | መካከለኛ |
| 15 | የትምህርት ስትራቴጂክ ማዕከል | • አግባብነት/ሕጋዊነት<br>• መልካምና ቀልጣፋ አስተዳደር<br>• ተነሳሽነት<br>• የጋራ ግብ | • መልካም አስተዳደር<br>• አጋርነት<br>• ፍትኃዊነት<br>• ቀልጣፋ አሰራር | • የትብብር ማነስ<br>• ገፅታ መበላሸት<br>• አለመታመን<br>• የጋራ ግብ አለመሳካት | መካከለኛ |

| ተ.ቁ | ተገልጋይ/ባለድርሻ አካል | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው ባህሪያት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከተቋሙ የሚፈልጉት ምርት/አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት በተቋሙ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩባቸው ጉዳዮች | የተፅዕኖው ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | **የዉስጥ ተገልጋይ / ባለድርሻ አካላት** የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ሠራተኞች | • መልካም ስነ-ምግባር<br>• የስራ ብቃትና ተነሳሽነት<br>• የባለቤትነት ስሜት<br>• በጋራ የመስራት ስሜት | • መልካምና ቀልጣፋ አስተዳደር<br>• ምቹ የስራ አካባቢ<br>• የማትጊያ ስርዓት | • ተልዕኮ አለመሳካት<br>• የሠራተኛ ፍልሰት<br>• ተፈላጊነት ማጣት<br>• ገፅታ መበላሸት<br>• የብልሹ አሰራር መፈጠር | ከፍተኛ |
| 2 | የወልድያ ዩኒቨርሲቲ አመራር አካላት | • መልካም አስተዳደር<br>• ቁርጠኝነት<br>• በዕቅድ መመራት<br>• ድጋፍ መስጠት<br>• ፈጣን ውሳኔ | • ተነሳሽነት<br>• ተልዕኮ መሳካት<br>• ኃላፊነትን መወጣት<br>• የስነ-ምግባር መርሆዎችን ማክበር | • የአመራር ለውጥ<br>• አመኔታ ማጣት<br>• የማትጊያ ስርዓቶችን መቀነስ | ከፍተኛ |
| 3 | የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ስራ አመራር ቦርድ አባላት | • መልካም አስተዳደር<br>• ቁርጠኝነት<br>• በዕቅድ መመራት<br>• ድጋፍ መስጠት<br>• ፈጣን ውሳኔ | • ተነሳሽነት<br>• ተልዕኮ መሳካት<br>• ኃላፊነትን መወጣት<br>• የስነ-ምግባር መርሆዎችን ማክበር | • የአመራር ለውጥ<br>• አመኔታ ማጣት<br>• የማትጊያ ስርዓቶችን መቀነስ | ከፍተኛ |

## 3.6.3. የተገልጋይ/ ባለድርሻ አካላት ፍላጎት ትንተና

| ተ.ቁ | ተገልጋይ/ ባለድርሻ አካላት | አገልግሎት ምርት | የአገልግሎቱ/የምርቱ ባህሪያት | | | | ግንኙነት | የተቋሙ ገጽታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የአገልግሎቱ/የምርቱ ጠቀሜታ | ጥራት | አገ/ለማገኘት የሚወስደው ጊዜ | ለአገልግቱ የሚከፈል ዋጋ | | |
| 1 | **ተገልጋይ** ተማሪ | ትምህርት | • በዕውቀት፣በክህሎትና በአመለካከት መዳበር<br>• ስራ-ፈጣሪነት፣ ተቀጣሪነት፣ ችግር ፈችነት | ዓለም-አቀፍና አገር-አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ያሟላ | ተቀባይነት ያለው የጊዜ ገደብ | ተመጣጣኝና ምክንያታዊ የሆነ ክፍያ | መልካም፣ አሳታፊ | ዕምነት የሚጣልበት |
| | | መሰረታዊ አገልግሎት | • መሰረታዊ ፈላጎቶችን ማሟላት<br>• ለትምህርት የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማዘጋጀት | አገር-አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን የጠበቀ | በቆይታ ጊዜያቸው | ተመጣጣኝና ምክንያታዊ | በውይይት ላይ የተመሰረተ አሳታፊ | ዕምነት የሚጣልበት |
| 2 | ማኅብረሰብ | ቸግር ፈች የማህበረሰብ አገልግሎት | • የኑሮ መሻሻል፣ የአስተሳሰብ ለውጥና የስራ ባህል መዳበር | ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎትና ኅብረተሰቡን ያረካ | እንደየአስፈላጊነቱ | ተቀባይነት ያለው | የሁለትዮሽ | የእኔነት ስሜት |
| 3 | ቀጣሪ ድርጅቶችና መ/ቤቶች | ብቁና ተወዳዳሪ ምሩቅ | • ቀጣሪ ተቋማትን ውጤታማ ማድረግ<br>• ተወዳዳሪነት | አለም-አቀፍና አገር-አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ያሟላ | ሁልጊዜ | ተመጣጣኝ | የሁለትዮሽ | የእኔነት ስሜት |

| ተ.ቁ | ተገልጋይ/ ባለድርሻ አካላት | አገልግሎት ምርት | የአገልግሎቱ/የምርቱ ባህሪያት | | | | ግንኙነት | የተቋሙ ገጽታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የአገልግሎቱ/የምርቱ ጠቀሜታ | | | ለአገልግቱ የሚከፈል ዋጋ | | |
| 1 | **ባለድርሻ አካላት**<br>ሣይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር | ተልዕኮን ማሳካት | • አገራዊ ራዕይን ማሳካት<br>• የትምህርት ፖሊሲዎችን መፈፀም | አለም አቀፍና ሀገር አቀፍ የጥራት ደረጃዎችን ያሟላ | ሁልጊዜ | ወጭ ቆጣቢ | አሳታፊ የመሪና ተመሪ ግንኙነት | እምነት የሚጣልበት |
| 2 | ገንዘብ ሚኒስቴር | ውጤትን መሰረት ያደረገ የበጀት አጠቃቀም | • አገራዊ ራዕይን ማሳካት<br>• የሀብት አጠቃቀምን ማሻሻል | በተቀመጡት ውጤቶች | ሁልጊዜ | ወጭ ቆጣቢ | አሳታፊ የመሪና ተመሪ ግንኙነት | እምነት የሚጣልበት |
| 3 | ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን | ቀልጣፋና ፍትሃዊ የስራ አፈፃፀም | • አገራዊ ራዕይን ማሳካት<br>• መልካም አስተዳደርን ማስፈን | በሚኒስቴሩ የደረጃ መለኪያ መስፈርት | ሁልጊዜ | ተመጣጣኝ፣ አግባብነት ያለው | አሳታፊ የመሪና ተመሪ ግንኙነት | አርአያነት |
| 4 | መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች | ትብብር | • የጋራ ግብን ማሳካት | የጋራ ግብን ያሟላ | አስፈላጊ በሆነ ጊዜ | ተቀባይነት ያለው | የሁለትዮሽ | ተባባሪነት |
| | | የጥናትና ምርምር ውጤቶች | • የማህበረሰቡን ችግር መፍታት<br>• የድጋፍ ምንጭ መሆን | አለም አቀፍና አገር- አቀፍ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ | አስፈላጊ በሆነ ጊዜ | ተቀባይነት ያለው | የሁለትዮሽ | ተባባሪነት |
| 5 | የከፍተኛ ት/ትና የምርምር ተቋማት | ትብብር | • አቅም ማጎልበት<br>• የስራ ውጤታማነትን መገምገም | የጋራ ጥቅምን ያስጠበቀ | አስፈላጊ በሆነ ጊዜ | ተቀባይነት ያለው | የሁለትዮሽ | ተባባሪነት |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | የአማራ ክልል መንግስት | የልማት አጋርነት | • የክልሉን ዕድገት ማፋጠን | የህብረተሰቡን ፍላጎት ያረካ አያደገ የሚሄድ | ሁልጊዜ | ተመጣጣኝ | የሁለትዮሽ | ተባባሪነት፣ ዕምነት የሚጣልበት |
| 7 | የስራ አመራር ቦርድ አባላት | መልካም የስራ አፈፃፀም | • ግብን ማሳካት<br>• ብልሹ አሰራርን ማስወገድ | በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ተቀባይነት ያለው | ሁልጊዜ | ወጭ ቆጣቢ | የመሪና ተመሪ | ዕምነት የሚጣልበት |
| | | ደንበኞችን ያረካ አገልግሎት | • ግብን ማሳካት<br>• ብልሹ አሰራርን ማስወገድ | በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ተቀባይነት ያለው | ሁልጊዜ | ወጭ ቆጣቢ | የመሪና ተመሪ | ዕምነት የሚጣልበት |
| | የወልድያ ዩኒቨርሲቲ አመራር አካላት | መልካም የስራ አፈፃፀም | • ግብን ማሳካት<br>• ብልሹ አሰራርን ማስወገድ | በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ተቀባይነት ያለው | ሁልጊዜ | ወጭ ቆጣቢ | የመሪና ተመሪ | እምነት የሚጣልበት |
| | | ምቹ የስራ አካባቢ | • የስራ ተነሳሽነት መፍጠር<br>• እርካታ | አገራዊ መልካም ስነ-ምግባር ደንቦችን ያሟላ | ሁልጊዜ | ተቀባይነት ያለው | የጋራ ጥቅምን ያስጠበቀ | ተመራጭ |
| | | የአቅም ግንባታ ስራ | • የመፈፀም አቅምን ማሳደግ | አለም አቀፍና አገር አቀፍ የጥራት ደረጃውን ያሟላ | አስፈላጊ በሆነ ጊዜ | ወጭ ቆጣቢ | ›› | ›› |
| | | ማበረታቻና ጥቅማጥቅም | • ተነሳሽነትና የኔነት ስሜት መፍጠር | ያረካ | አስፈላጊ በሆነ ጊዜ | ተቀባይነት ያለው | ›› | ›› |

## 3.7 የትኩረት አቅጣጫ የሚወስንበት አግባብ

ዩኒቨርስቲው በእቅድ የያዛቸው ተግባራ መንግስት ከሰጠው ተልኮ አንጻር በመማር ማስተማር በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ተገቢውን ድርሻ ለመወጣት ይችል ዘንድ፡-

- የአጠቃላይ ዩኒቨርስቲ ከመሆኑ አንጻር በዚህ ምድብ የተመደቡ ዩኒቨርስቲዎች መወጣት የሚገባቸውን ኃላፊነት መሰረት በማድረግ፣
- የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ያስቀመጣቸውን ግቦችና የትኩረት አቅጣጫዎች ታሳቢ መደረጋቸውን በማረጋገጥ
- አገራዊና አካባቢያዊ የሰው ሃብት ልማት ፍላጎቶችና ችግሮችን ከግናዛቤ በማስገባት፣
- የሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ አቅጣጫዎችን በተለይም ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የሚደረገውን መዋቅራዊ ሽግግር ታሳቢ ባደረገ መልኩ፤
- ዩኒቨርስቲው አሁን ያለበት የአፈጻጸም ደረጃ እና ተልዕኮውን ለመወጣት የሚያስችሉ ደረጃዎች

### 3.8 የትኩረት አቅጣጫዎች

የዩኒቨርሲቲው ስትራቴጂክ የትኩረት አቅጣጫዎችን ሲመርጥ ቀደም ሲል የተከናወኑ ስትራቴጂያዊ ትንተና ውጤቶችን መሠረት በማድረግ እና መንግስት የሰጠውን የአጠቃላይ ዩኒቨርስቲ ተልዕኮ ለመወጣትና  ራዕዩን እውን ለማድረግ የሚያስችሉ መሆናቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ሲሆን የትኩረት አቅጣጫዎቹም፡-

1. ብቁና ተወዳዳሪ ምሩቃንን ለማፍራት የሚያስችል የላቀ ትምህርት አሰጣጥ
2. ችግር ፈች ጥናትና ምርምር ስራዎች
3. ፋይዳ ያለዉ የማህበረሰብ አገልግሎት፤
4. የቴክናሎጂ ልማት

እነዚህ የትኩረት አቅጣጫዎች እነዚህን ዝርዝር ጉዳዮች ያካትታሉ

ሀ.ብቁና ተወዳዳሪ ምሩቃንን ለማፍራት የሚያስችል የላቀ ትምህርት አሰጣጥ

ዩኒቨርስቲው ብቁ የሰው ሀይልና በቂ ግብዓት በማሟላት፣ ተፈላጊ የትምህርት መርሃ ግብሮችና ስርዓተ-ትምህርቶችን በመቅረፅ እንዲሁም ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓትና አጋርነትን በመፍጠር ጥራቱን የጠበቀ የመማር ማስተማር ሂደት በማከናዎን ተማሪዎች ተፈላጊውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት እንዲያዳብሩ በማድረግ ብቁ፣ ተወዳዳሪና የፈጠራ ችሎታ ያላቸዉ ምሩቃንን በማፍራት የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮና ራዕይ ማሳካት የሚያስችል ነው፡፡

በዚህም ዩኒቨርሲቲው ለተማሪዎች በሚሰጠው የትምህረት ጥራትና የተማሪዎች አገልግሎት ብቁና ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችላቸውን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት እንዲጨብጡ የማድረግ፣ በቆይታቸውም ምቾታቸውን የጠበቀ አገልግሎት ስእንዲያገኙ የሚያስችሉ ተግባራትን የማከናወን፡፡

ብቁና ተወዳዳሪ ምሩቃንን ለማፍራት የሚያስችሉ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ስረዓትን የመዘርጋትና የትምህርት ጥራት አመላካች መስፈርቶች በሚገባ ስለመፈጸማቸው የማረጋገጥ እንዲሁም የትምህርት ጥራት ቁጥጥርን የማድረግ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ በተጨማሪም በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት መርሃ ግብሮች /በኤክስቴንሽን፣ በክረምትና በርቀት/ ገበያው የሚፈልጋቸውን የትምህርት ክፍሎችና ግቢዎችን መክፈትን፣ ዩኒቨርሲቲዉ በሚሰጣቸዉ አገልግሎቶችና ባለዉ ኃብት ሴቶች፣ ለአደጋ ተጋላጭና ልዩ ትኩረት የሚሹ ወገኖች በእኩል ተጠቃሚ ለማድረግና ፍትኃዊ አሰራርን ለማስፈን የሚደረገዉን ጥረት የሚያካትት ይሆናል፡፡

ከዚህም ባለፈ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማሳለጥ አጋዥ የሆኑ የሕንፃ ግንባታ፣ የመንገድ፣ የመብራት፣ የውሃ፣ የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶችና የተለያዩ ክፍሎችን የማስፋፋትና የመስራት ተግባርን፣ የተመራቂዎችን የተቀጣሪነት መጠን ለማሳደግ የሚያስችሉ የክህሎት ስልጠናዎችን በመስጠትና ከኢንዱስትሪዎች ጋር ትስስር በመፍጠር የምሩቃንን መቀጠር የማረጋገጥና ዩኒቨርሲቲው የመምህራንንና የአስተዳደር ሰራተኞችን አቅም ለማሳደግ የሚያከናውናቸውን የአጭርና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎችና ሌሎች የአቅም መገንቢያ ስልቶችን ተግባራዊነት እንዲሁም የተገልጋዮችን ደህንነት መጠበቅ፣ የመምህራን መኖሪያ ቤት፣ ካፍቴሪያዎች፣ የስፖርት ማዘዉተሪያ ስፍራዎች፣ የግቢ ዉበት፣ የመዝናኛ ስፍራዎችና ግብዓትን ማሟላትን ያስራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው ይከናወናሉ፡፡

### ለ. ችግር ፈች ጥናትና ምርምር ስራዎች

ዩኒቨርሲቲው የማህበረሰቡን ችግሮች በመለየት አሳታፊና የተቀናጀ ተግባራዊና መሠረታዊ ጥናትና ምርምሮችን በማካሄድና ተደራሽ በማድረግ ለሀገራችን እድገትና ብልጽግና የድርሻውን ለመወጣት የተሰጠውን ተልዕኮና ራዕይ ዕውን ለማድረግ የተመረጠ ስትራቴጂያዊ የትኩረት አቅጣጫ ሲሆን በዩኒቨርሲቲውና ከዩኒቨርሲቲዉ ዉጭ የተሰሩ የጥናትና ምርምር ውጤቶች በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጪ በሚታተሙ ጆርናሎች፣ በሲምፖዚየሞች፣ ወደ ፕሮጀክት በመቀየርና በሌሎች ዘዴዎች ለፖሊሲ አውጭዎች፣ ለተመራማሪዎች እና ለማህበረሰቡ መድረሳቸውን የማረጋገጥ ስራዎችን የሚያካትት ነው፡፡

ለዚህም የተመራማሪዉን በቡድንና በግል የጥናትና ምርምር ስራዎችን ለማከናወን የሚያስችሉ የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች፣ የምርምር ሰሚናሮች፣ ወርክሾፖችና ሲምፖዚየሞችን የመስራትና ሌሎች የአቅም ግንባታ ስራዎችን የማከናወን፣ ለጥናትና ምርምር እንዲሁም ለስልጠና ስራ አጋዥ የሆኑ ማዕከላትና ቤተ-ሙከራዎችን ማቋቋም፣ ለስራው የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማሟላት እንዲሁም የማበረታቻ ስርዓት የመዘርጋት እና በለያቸዉ የጥናትና ምርምር የትኩረት መስኮች የሚሰሩ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በቁጥርና በጥራት ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶችን፣ ማበረታቻዎችንና በቂ የሆነ ኃብት የመመደብ ስራ ይሰራል፡፡

በተጨማሪም የሀገር በቀል እውቀትን በመለየትና ምርምሮችን በመስራት እንዲሁም የቴክኖሎጂ አቅርቦት ለማሳደግ የሚያስችሉ የመለየት፣የመቅዳት ወይም የማላመድ፣ የማሻሻል፣ እንዲሁም ቴክኖሎጂን የመፍጠር አቅምን የመገንባት ስራ ይሰራል፡፡ ከዚህም ባለፈ ዩኒቨርሲቲዉ የልሕቀት ምህዳሩን ለመገንባትና የጥናትና ምርምር ስራዎችን በተለያዩ የትኩረት መስኮች ለመስራት የሚያስችሉ ማዕከላትን የማቋቋምና የማደራጀት ስራዎች ይሰራሉ፡፡

ሐ. ፋይዳ ያለዉ የማህበረሰብ አገልግሎት፤

ዩኒቨርስቲው ችግር ፈች የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ተግባራዊነት፣ የረዥምና የአጭር ጊዜ ስልጠናዎችን መስጠት፣ የማማከርና ማህበረሰቡን ያሳተፋና ፍትኃዊ አገልግሎቶችን እንዲሁም አገልግሎቶቹን ለመስጠት የሚፈጠሩ አደረጃጀቶችና የግብዓት ማሟላትን ስራዎችን ለመስራትና የአገልግቶችን ብዛት፣ ተደራሽነትንና የተገልጋዮችን እርካታ በማጥናት ማህበረሰቡን ያሳተፈና ያረካ አገልግሎት በመስጠት የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮና ራዕይ ዕውን ለማድረግ የሚያስችል የትኩረት አቅጣጫ ነው፡፡

በዚህም የማህበረሰብ አገልግሎቶችን በዓይነትና በቁጥር ማሳደግ፣ ህብረተሰቡ ችግሮቹን በራሱ የመፍታት ባህሉን እንዲያዳብር በማድረግና አደረጃጀቶችን በመፍጠር አገልግሎቱ እውን መሆኑን በማረጋገጥ የሚሰጡ የማህበረሰብ አገልግሎቶች ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል ግልጽና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት ስለመዘርጋቱና የፋይዳ ጥናት ይደረጋል፡፡ ዩኒቨርሲቲዉ በለያቸዉ የማህበረሰብ አገልግሎት የትኩረት መስኮች የሚሰጡ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን በቁጥርና በጥራት ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶችን፣ ማበረታቻዎችንና በቂ የሆነ ኃብት የመመደብና የዩኒቨርስቲው ከማህበረሰቡና አጋር አካላት ጋር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ የትብብርና ድጋፍ ስምምነቶችን ለመፈራረም የሚያስችሉ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በመቅረጽና የመተግበር ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

መ- የተሟላ የቴክኖሎጂ አገልግሎት፤

ዩኒቨርሲቲዉ የቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማትን በመዘርጋት፣ ዘመኑ የሚፈልገዉን ግብዓትና በዘርፉ የሰለጠነ የሰዉ ኃይል በማሟላት መማር ማስተማሩን፣ ምርምሩን፣ የማሕበረሰብ አገልግሎቱንና አስተዳደራዊ ስርዓቱን በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ፍትኃዊ፣ ቀልጣፋና ጥራቱን የጠበቀ በማድረግ ዩኒቨርሲቲዉን ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት የሚያግዝ ሲሆን ቴክኖሎጂን በመፍጠር፣ በመቅዳትና በማላመድ አገራዊ በማድረግ በአግባቡ የመጠቀም እንዲሁም ይህንን በተሳካ ሁኔታ ለማካሄድ የሚያስችሉ አጫጭር ስልጠናዎች፣ ወርክሾፖች፣ ኤግዚቢሽኖች በማዘጋጀትና የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር በመፍጠር የሚሰሩ ተግባራትን ያካትታል፡፡

በተጨማሪም ተቋማዊ የመረጃ ልዉዉጥን በዘመናዊ የመረጃ ቋት በመጠቀምና የመረጃ አጠቃቀም ፖሊሲና ደህንነትን የጠበቀ ቅንጅታዊ አሰራር በስራ ክፍሎች የመዘርጋት፣ የስራ

ክፍሎች ከጊዜዉ ጋር የሚሄዱ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጣቸዉን ማዘመን በዚህም ሴቶች፣ ለአደጋ ተጋላጭና ልዩ ትኩረት የሚሹ ወገኖች በእኩል ተጠቃሚ ለማድረግና ፍትኃዊ አሰራርን ለማስፈን ጥረት ይደረጋል፡፡

# 4 የአምስት ዓመታት እቅድ ግቦች፣ ዓላማዎች፣ ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

የዩኒቨርሲቲው የለያቸው የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ በመመስረት እና ስትራቴጂያዊ ትንተና ውጤቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተቋሙ ዋና ዋና ተግባራትን ለሚገልጹትና የትኩረት አቅጣጫውን ለሚያመላክቱ የስኬት አምዶች ራዕዩን እውን ለማድረግ የሚስችሉ የየራሳቸው ዓላማ ያላቸው ግቦችን የቀረጸ ሲሆን የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎችንም ነድፏል፡፡

## 4.1 ስትራቴጂያዊ ግቦች

ዩኒቨርስቲው ከሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ግቦች አንጻር ተወራራሽ የሆኑና የዩኒቨርስቲውን በአጠቃላይ ዩኒቨርስቲነት የተሰጠውን ተልዕኮና በአስር ዓመቱ መሪ እቅድ ያስቀመጠውን ራዕይ ዕውን ለማድርግ የሚያስችሉ ስትራቴጂያዊ ግቦች በማስቀመጥ የሚከተሉትን የአምስት ዓመታት ግቦች አስቀምጧል፡፡

1. የትምህርት ጥራት፣ አግባብነት፣ ተደረሽነትንና ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ
2. የዩኒቨርስቲውን የአፈጻጸም አቅምና ብቃት ማሳደግ፣
3. የማህበረሰብ ተሳትፎና የሳይንስ ባህል ግንባታን ማጠናከር
4. የጥናትና ምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራትን ማጠናከር
5. የዩኒቨርስቲውን መሰረተ-ልማትና ፋሲሊቲ ማሳደግ
6. የክትትልና ግምገማ ስርዓቱን ማጠናከ

## 4.2 የሚጠበቁ ውጤቶች

ዩኒቨርስቲው ይህን የልማት እቅድ ሲያቅድ ከእቅዱ የሚጠበቅ ውጤት ምን እንደሆነ በግልጽ በመለየት ሲሆን የእቅድ አፈጻጸሙን በየጊዜው ሲገመግም እነዚህን ውጤቶች መሰረት በማድረግ ሲሆን ዋና ዋና ውጤቶቹ ከዚህ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

- የዲጅታል ክህሎት ያላቸው ብቁና ተወዳዳሪ ምሩቃን

- በውስጥና በውጭ የምርምር ስራዎች የታገዙ ተደራሽ የማህበረሰብ አገልግሎቶች
- ችግር ፈቺ የጥናትና ምርምር ዉጤቶች
- በእውቀት፣ ክህሎትና አመለካከታቸዉ ያደገ እና የተወዳዳሪነት ብቃት ያላቸው መምህራን ይኖራሉ
- ዩኒቨርሲቲው የተቋቋመበትን ተልዕኮ ከማሳካት አኳያ በቂ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል እውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ያላቸው አስተዳደር ሠራተኞች ይኖራሉ
- ብቃት ያላቸው የከፍተኛ፣ መካከለኛና የታችኛው የአመራር አካላትና ክህሎታቸው ያደገ ተተኪ አመራሮች
- በየስራ ክፍሉ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ክህሎት ያላቸዉ ሠራተኞች እና ቀልጣፋና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ልውውጥ ይፈጠራል
- የተጠናከረ የፋይናንስና የግብዓት አቅም ይኖራል
- የተማሪ ቅበላ አቅም ያድጋል
- ጠንካራ የአገር ውስጥና የውጭ ግንኙነት ይፈጠራል
- ውብ፣ ማራኪና ለስራ የሚያነሳሳ ምቹ የስራ አካባቢ ይኖራል
- የሴቶች ተሳትፎ ያድጋል
- የዩኒቨርሲቲውና የአካባቢው ማህበረሰብ ሰላምና ደህንነት ይጠበቃል

5. የዩኒቨርስቲው ወሳኝ የሆኑ ሰብዓዊና ቁሳዊ ሃብቶች

### ሀ. የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ

በ2004ዓ.ም ስራውን የጀመረው ለዩኒቨርስቲው የአስተዳደር ጽ/ቤት በወልድያ ከተማ አነስተኛ ህንጻ ተከራይቶ ሲሆን የተማሪዎች የመኝታና የትምህርት አገልግሎት የሚሰጠው በመርሳ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ ውስጥ ነበር፡፡ በወቅቱ የዩኒቨርስቲው የአስተዳደር ዘርፍ የስራ መዋቅር በትምህርት ሚኒስቴር ተጠንቶ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የጸደቀ ሲሆን በመዋቅሩ መሰረት 117 ሰራተኞች ነበሩት፡፡

በ2005ዓ.ም ዩኒቨርስቲው በራሱ ግቢ ስራ ሲጀምርና የተማሪዎች ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ የነበረው የሰው ሃይል አደረጃጀት በቂ ስላልነበር የሰው ሃይል መዋቅሩ እንዲጠና ተደረገና ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ቀርቦ እንዲጸድቅ በመደረጉ በአሁኑ ወቅት ዩኒቨርስቲው በአራት ዘርፎች/በምክትል

ፕሬዘዳንቶች የሚመራ/ ሰላሳ ስድስት የስራ ክፍሎች ያሉት ሲሆን የአስተዳደር ሰራተኛውም ቁጥር 958 ደርሷል፡፡ ከዚህ ውስጥ 42% ሴቶች ናቸው፡፡

ከነዚህ በተጨማሪ የግንባታ ሂደቱን ከትምህርት ሚኒስቴርና ከአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የቤቶች ልማት ኤጀንሲ በመረከብ የክትትልና ቁጥጥር ስራውን ለመስራት ይቻል ዘንድ የፕሮጀክት ጽ/ቤት እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን ጽ/ቤቱን በሰው ኃይል የማደራጀት ስራ ተሰርቷል፡፡ ለዚህም 8 ሰራተኞች ተቀጥረው ስራቸውን በማከናወን ላይ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የምግብ፣ የጥበቃና የጽዳት አገልግሎቶችን በከተማ አስተዳደሩ ለተቋቋሙ ማህበራት የሰጠ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ለ983አባላት አሏቸው፡፡ ዩኒቨርስቲው አገልግሎቱን ለማህበራቱ በመስጠቱ ለግለሰቦቹ የስራ እድል ከመፍጠሩ ባሻገር አመራሩ በአቅርቦቱ ጥራት ላይ እንዲያተኩር ከመርዳቱም በላይ ለትራንስፖርትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያወጣውን ወጪ ለመቀነስ ችሏል፡፡

### ለ. መምህራን

ዩኒቨርስቲው በ2004ዓ.ም ስራውን ሲጀምር የነበሩት የመምህራን ቁጥር 115 የነበረ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የሴቶት መምህራን ቁጥር 15/13%/ ነበር፡፡ በ2012ዓ.ም ይህ አሃዝ በአጠቃላይ የመምህራን ቁጥር ወደ 1285 ከፍ ያለ ሲሆን የሴት መምህራን ቁጥር ወደ 160/12%/ ነው፡፡ ይህም በመቶኛ ሲታይ መጀመሪያ ከነበረው ዝቅ ብሏል፡፡ በመሆኑም ከሴት መምህራን ተሳትፎ አንጻር መንግስት ያስቀመጠውን 20% ለማድረስ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት የሴት መምህራን ቁጥር በገበያ ላይ አነስተኛ በመሆኑ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በቀጣዩ የእቅድ ዘመን የሴት መምህራን ቁጥር ማሳደግ አስፈላጊ እንደሆነ ያመላክታል፡፡

በ2012 ዓ.ም ካሉን አጠቃላይ መምህራን በመጀመሪያ፣ በሁለተኛና በሦስተኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ስብጥር በቅደም ተከተል 22፡75፡3 ለማድረስ ተችሏል፡፡

### *ሐ. ሌሎች ግብአቶች*

የዩኒቨርስቲው አመራርና ሰራተኞች ባሳለፉት አራት አመታት ሙሉ አቅማቸውን በማሟጠጥ ጠንክረው ከሰሩባቸው ዘርፎች መካከል ግንባታ ማካሄድን፣ የቢሮ ቁሳቁሶችን፣ የመማሪያ ክፍሎችን፣ ላብራቶሪዎችንና ቤተ-መጽሃፍትን የማሟላትና የማደራጀት ተግባራት ይገኙባቸዋል፡፡
በዚህም የቁሳቁስ ግዢዎች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲከናወኑና ለመማር ማስተማር ስራ በቅድሚያ ሊሟሉ የሚገባቸውን ቅድሚያ በመስጠት እንዲፈጸሙ ተደርጓል፡፡ ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ውርክሾችንንና ላብራቶሪዎች ከሚያስፈልገው 80 በመቶ የሚሆነውን ለማሟላት ችሏል፡፡ የቤተ-መጽሃፍቱን በመጽሃፍት ለማሟላት የግዢና የማባዛት ስራዎችን በስፋት በመስራት በአሁኑ ወቅት 70,00 መጽሃፍት እንዲኖሩት አስችሏል፡፡ የኢንፎርሜሽን ኮሙኑኬሽን/ICT/ ግብአትን በተመለከተም ዩኒቨርስቲው በአሁኑ ወቅት 500 ሜጋ ባይት የኢንተርኔት አገልግሎት በመግዛት እየተጠቀመ የተማሪዎችን መረጃ ለመያዝና ለመለዋወጥ የሚያስችል ሶፍት ዌር /SMIS/ ገዝቶ መጠቀም ጀምሯል፡፡

## 6. የማስፈጸሚያ ተቋማዊ አቅም፣ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች

*አገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂን መቃኘት ዩኒቨርስቲው ለሀገራዊ ልማት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ምሩቃንን ለማፍራት ሊያተኩርባቸው የሚገቡ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ለመወሰንና በገበያ ላይ ተወዳዳሪ ለመሆኑ የሚያስችሉ የትምህርት ክፍሎችን ለመክፈት አይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም ወሳኝ የሆኑ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን እንደሚከተለው ገምግሟል፡፡*

### 6.1 የትምህርትና ስልጠና ፍኖተ ካርታ እና የዘላቂ ልማት ግቦች (SDG)

ትምህርትና ሥልጠና የተሻለ ኑሮ፣ ዕድገትና ብልጽግናን እንዲሁም ልማታዊነትንና ዴሞክራሲያዊነትን ለቀጣዩ ትውልድ ለማሰተላለፍ የሚያስችል ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የግለሰብ እውቀትና ክህሎትን በማሳደግ ምርታማነቱን መጨመር የሚያስችል ጥራት ያለው ትምህርትን በማስፋፋት የሕብረተሰብንና በአጠቃላይ የአገርን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ተቋማዊ የመፈፀም አቅምን ያሳድጋል፡፡

የተመረጡ የትኩረት አቅጣጫዎች፡-

- ትምህርትና ሥልጠናን ከግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ እንዲሁም ከኢንዱስትሪና ከግብርና ለውጥና እድገት ጋር ማስተሳሰር፣

- ለነባራዊ ሁኔታዎች ምላሽ የሚሰጡና ግብርናን ወደ ላቀ ደረጃ በማሻገር ኢኮሚኖሚውን የሚያሳድጉ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆኑ ብቁ ዜጎችን ማፍራት፣
- የሀገሪቱን መልካም ባህል የሚያበለጽጉ፣ የሀገር ፍቅር ያላቸው፣ብዙሃነትን የሚቀበሉ፣ ሰብአዊ መብቶችን የሚያከብሩ፣ለሰው ልጅ ደህንነትና እኩልነት፣ ለፍትሕ፣ ለሠላም ዘብ የሚቆሙ፣ በግብረገብ፣ በሥነምግባርና በዴሞክራሲ ባህል የታነጹ፣ የሀገራቸውን ታሪክ የሚያውቁ፣ ለሀገራቸው አንድነት ዘብ የሚቆሙ፣ ለሕዝብና ለሀገር ፍቅር ያላቸው ሁለንተናዊ ስብእናቸው የተሟላ ዜጎችን ማፍራት፣
- ጥራት ያለው የከፍተኛ ትምህርትን በፍትሃዊነት ለሁሉም ዜጎችና በሁሉም አከባቢዎች ያለ ልዩነት ማዳረስ፣
- በሀገሪቱ የሚሰጡ የከፍተኛ ትምህር ትመርሃ-ግብሮች ከሀገር እና ከዓለም አቀፍ ልማትና እድገት እንዲሁም ከሰው ኃይል ገበያ ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ ጥራትና ተገቢነት ያላቸው እንዲሆኑ ማድረግ፣
- የከፍተኛ ትምህርት መምህራን የሚያስተምሩበት ደረጃ የሚጠይቀውን የሙያ እውቀት፣ አመለካከትና ክህሎት ብቃት ማጎልበት፣
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚካሄዱ ምርምሮች ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር ተጣምረው የማህበረሰብን ሁሉን አቀፍ ለውጥ ማምጣት፣
- የዩኒቨርሲቲ መርሃ-ግብሮችንከ ኢንዱስትሪ ፍላጎት ጋር የሚያጣጥምና ብቃት ያለው የሰው ኃይልን ለማፍራት የሚያስችል እንዲሁም የኢንዱስትሪውን ተወዳዳሪነትና ምርታማነት የሚያሳድግ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር እንዲኖር ማድረግ፣
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተቋቋሙበትን ዓላማ ለማስፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ ብቃት እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- የከፍተኛ ትምህርት ጥራትንና ተገቢነትን ለማስጠበቅና ተደራሽነትን ለማስፋት ዓለም -አቀፋዊነትና አጋርነትን ማሳደግ፣
- ውጤታማ የሆነ፣ ተጠያቂነትን ያሰፈነ እና ሚዛናዊ የሆነ ያልተማከለ የትምህርት ፋይናንስ ሥርዓት መዘርጋት፣

- ትምህርትና ሥልጠናን በጥራት ለመሥጠት፣ ለመደገፍና ለማስፋፋት የሚያስችል ቴክኖሎጂ እንዲጠናከር ማድረግ ሲሆን፣

ወልድያ ዩኒቨርሲቲ ይህን ፖሊሲ ለማስፈፀም የተሰጠዉን አገራዊ ኃላፊነት በአግባቡ በመወጣት በቴክኖሎጂ ዕዉቀትና ክህሎት የበለፀጉ፣ ብቁና ተወዳዳሪ፣የአገር ፍቅር ያለዉ፣ ለአገረ-መንግስት ግንባታ የበኩሉን አስተዋጾ የሚያበረክት የሰው ሀይል ለማፍራት ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከኮሌጆች፣ ከምርምር ተቋማት፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና ከኢንዱስትሪዎች ጋር በመተባበር የሚሰራ ሲሆን የአዳዲስ እውቀቶች ማፍለቂያና ማላመጃ ማዕከል በመሆን የዚህን ቁልፍ ፖሊሲ ተፈፃሚነት እዉን ያደርጋል፡፡

## 6.2. የጤና ፖሊሲ

እንደ አውሮፓውያን ዘመን ቀመር በ1993 የተዘጋጀው የጤና ፖሊሲ በጤና አገልግሎትና በዋና ዋና የጤና ችግሮች ላይ ያተኮረ ተግባራዊ ምርምርን ያበረታታል፡፡ የጤና ባለሙያና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተም የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችንና መካከለኛ ደረጃ ባለሙያዎችን በብዛት በማፍራት በመከላከል ላይ የተመሰረተ የጤና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ትምህርትና እንደሚያስፈልግ አስቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በ2015 የተዘጋጀው የጤና ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የቁጥጥር ስርዓት ማጠናከር ላይ በውጤታማ ስራ አመራርና ተአማኒነት ባለው በመረጃ የተደገፈ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ያተኩራል፡፡ የዘርፉን ስራ ለማዘመንም ቴክኖሎጂ አጠቃቀም የተሟላ ጤና መሰረተ ልማት  እና ፈጠራ የታከለበት የሰው ሀይል አመራር እንደሚያስፈልግ ይገልጻል፡፡

ይህንነኑ መሰረት በማድረግ ዩኒቨርሲቲው በከፈታቸው የጤና ትምህርት ዘርፎችና ሌሎች ተያያዥ መስኮች መስኩ የሚፈልገፈውን የሰው ሃብት ለማፍራት ጥረት የሚያደርግ ሲሆን በዘርፉ የሚሰሩ ሴክተሮችም ይህንን ሊደግፉና ያላቸውን እውቀት የዩኒቨርስቲውን እንቅስቃሴ ለመደገፍ የሚችሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል

## 6.3 የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ

ግብርና ለሀገራችን ኢኮኖሚ ዋነኛ መሠረት ነው፡፡ 83% የሚሆነው የህብረተሰብ ክፍልም ኑሮውን የመሠረተው በዚሁ ዘርፍ ነው ፡፡ ስለሆነም ክፍለ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ የሚረዱ እንደ ካፒታል ጉልበትና መሬት የመሳሰሉትን ግብአቶች በሙሉ አቅምና በቁጠባ በመጠቀም

ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የመሬትን ምርታማነት የሚጨምሩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የመሬት እንክብካቤን በማሳደግና በማሻሻል፣የተሻሻሉና ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ ዝርያዎችን ወደ ህብረተሰቡ በማሰራጨት፣ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በመስራትና ምርምሮችን በማካሄድ አበረታች ውጤት ማስመዝገብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም መንግስት ለአፈፃፀሙ ያመች ዘንድ የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች አስቀምጧል፡፡

- የሰው ኃይል አቅም ግንባታና ጉልበትን በስፋት መጠቀም፣
- ለግብርና የሚውል መሬትን በአግባቡ መጠቀም፣
- ለተለያዩ የግብርና ስነ-ምህዳር ትኩረት መስጠት ፣
- ውጤታማ የግብርና ገበያ ስረዓት መዘርጋት ፣
- ስፔሻላይዜሽንና ዳይቨርሰፊኬሽን ያጣመረ ግብርና ማካሄድ፣
- የተቀናጀ የሰብል ፣እንስሳት፣ የገበያና የተፈጥሮ ሀብት ልማትና የግብርና ምርምሮች ማስፋፋት፣
- የገጠር መሰረት ልማቶችንና አገልግሎቶችን ማስፋፋት፣
- የገጠር የገንዘብ ተቋማትን ማስፋፋት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ስለሆነም ወልድያ ዩኒቨርሲቲ ለግብርናው ዘርፍ ልማት መፋጠን አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ብቁ የግብርና ባለሙያዎችን በማፍራት፣ጥናትና ምርምር በማካሄድ የምርምር ውጤቶችን ተደራሽ በማድረግ እና የማማከር አገልግሎት በመስጠት ለስራው ዳር መድረስ አስተጽኦ ያደርጋል፡፡

## 6.4የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ

የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ዋና ዓላማ ዲጂታል ኢኮኖሚ በመፍጠር ከድህነት የተላቀቀችና መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር ለመገንባት ያስቀመጥነውን ሀገራዊ ራዕይ ለማሳካት የሚያስፈልጉትን ውጤታማ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለማላመድና ለመጠቀም የሚደረጉ ጥረቶችን ማበረታታት፣ መምራት፣ ማስተባበርና መደገፍ የሚያስችል ሀገራዊ ማዕቀፍ ለመፍጠር ነው፡፡

የፖሊሲው አቅጣጫዎችም፡-

- ዲጂታል ኢኮኖሚ፣

- የቴክኖሎጂ ሽግግር፣
- የሰው ሀብት ልማት፣
- የማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተሳትፎ፣
- ምርምር፣
- የፋይናንስ ድጋፍና የማበረታቻ ስርዓት፣
- ብሄራዊ የጥራት መሠረተ ልማት፣
- የዩኒቨርሲቲዎች፣ ምርምር ተቋማት እና ኢንዱስትሪዎች ትስስር፣
- የአእምሯዊ ንብረት ስርዓት፣
- የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ናቸው፡፡

በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማካሄድ፣ አዳዲስ ግኝቶችን በተለያየ መንገድ በማስገባት፣ በማላመድ፣ በመጠቀምና በማሸጋገር እንዲሁም በዋናነት በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂና በኢኖቬሽን ዘርፍ ብቁና ተወዳዳሪ ዜጎችን በማፍራት ለፖሊሲው መሳካት አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

## 6.5 የከተማና ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ

የከተማና ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ በመሰረታዊነት የከተሞችንና የኢንዱስትሪውን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የእድገት አቅጣጫና ተግባራት እንዲሁም የግብርና መር ኢኮኖሚውን ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚጣለውን መሰረት አቅጣጫ የሚያሳይ ነው፡፡

ይህም መንግስት በአሁኑ ሰዓት እየጨመረ የመጣውን የከተሞች የህዝብ ቁጥር ዕድገት ከከተሞቹ ዕድገት ጋር በማመጣጠን የህብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል እንዲረዳ የቀረጸው ፖሊሲ ሲሆን ከተሞችን በተመለከተ ፖሊሲው ያስቀመጣቸው የትኩረት አቅጣጫዎችም፡-

- የከተሞችና የመሰረተ ልማትን ግንባታና አገልግሎት ማስፋፋት
- አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማትን ማደራጀት፣ ማበረታታትና ማሳደግ
- የገጠር- ከተማንና የከተሞች የእርስ በእርሰ ትስስርን ማጠናከር
- ያልተማከለ የከተሞች አስተዳደር ስርዓትን መዘርጋት

- የዝቅተኛ ወጪ ቤቶች ግንባታን በስፋት ማካሄድ የሚሉት ናቸው፡፡

በተለይ ሀገራችን በአሁኑ ሰዓት የምትመራበት የግብርና ኢኮኖሚ ከፍተኛ እድገት እንዲያስመዘግብና በዚሁ ላይ ተመርኩዞ ኢንዱስትሪው የመሪነት ድርሻውን እንዲይዝ መንግስት በኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲው ያስቀመጣቸው አቅጣጫዎች፤

- የአነስተኛ ጥቃቅን ተቋማት ልማት
- የመካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች ልማት
- የኢንዱስትሪ መንደሮች ግንባታ
- የመንግስት ተቋማትን የስራ አመራር ማሳደግና ወደ ግል ማዛወር የሚሉት ሲሆኑ በዋናነት በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ልማት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

ኢንዱስትሪው በዋናነት የግብርና ውጤቶችን በግብዓትነት በመጠቀም ገበያ ተኮር እንዲሆንና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ምርቶችን የሚተኩና ለፈጣን የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚያገለግሉ የሀገሪቱን ፍላጎት የሚያሟሉ ምርቶችን የሚያመርት እንዲሆን ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ከፍተኛ ወጪ ከሚጠይቁ ዘርፎች ይልቅ ያለንን ከፍተኛ የሠው ሀይል መጠቀም በሚያስችሉን ዘርፎች ትኩረት ያደርጋል፡፡

ይህንን ሃገራዊ ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣትም የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ሀይል ለማምረት ከኢንዱስትሪዎች፣ ከምርምር ተቋማትና ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ጋር በመተባበር የሚሰራ ሲሆን የአዳዲስ እውቀቶች ማፍለቂያና ማላመጃ ማዕከል በመሆንም የፖሊሲውን ተፈፃሚነት ይደግፋል፡፡

## 6.6 የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ

የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲ መሠረታዊ አገራዊ ጥቅምን የማስጠበቅና አገራዊ ህልውናን የማረጋገጥ ተልዕኮ ያለው ሲሆን በሀገራችን ልማትና መልካም አስተዳደር ለማስፈን ቁልፍ ሚና ያለው ነው፡፡

የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫዎች፡-

- ዋናው ጉዳይና ትኩረት በአገር ውስጥ የሚሰራው ስራ እንዲሆን ማድረግ፤
- ኢኮኖሚን ማዕከል ያደረገ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ፤

- በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ጥቅሞችን አሟጦ መጠቀም ፤
- በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ አደጋዎችን መቀነስ፤
- ለአደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ፤
- ብቃት ያለው የመከላከል አቅምን መገንባትና
- የማስፈጸም አቅምን መገንባት የሚሉት ናቸው፡፡

ከዚህ በመነሳትም ዩኒቨርሲቲው ሃገራዊ እምነትና አመለካከት በመፍጠር ረገድ ከሚጫወተው ሚና እና ኃላፊነት በተጨማሪ ለፖሊሲው መሳካት አስተዋጽኦ ያላቸው ጥናቶችንና ምርምሮችን በማካሄድ የራሱን ድርሻ ይወጣል፡፡

## 7. የዩኒቨርሲቲው የአምስት ዓመታት ዕቅድ ግቦች፣ የግቦች መግለጫዎች፣ ስትራቴጂክ ዓላማዎችና እና የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

**ግብ 1፡-** የትምህርት ጥራት፣ አግባብነት፣ ተደረሽነትንና ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 1.1 በየዓመቱ ከምናስመርቃቸዉ መደበኛ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የተቀጠሩ ተመራቂዎች መጠን ማሳደግ

**የዓላማው መግለጫ** በየዓመቱ በተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞች ከምናስመርቃቸዉ መደበኛ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ውስጥ በተመረቁበት የትምህርት መስክ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምን ያህሉ እንደተቀጠሩ ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. ለተመራቂዎች የተወዳዳሪነት ብቃትን የሚጨምሩ የክህሎት ስልጠናዎች መስጠት
2. በጥናት ላይ የተመሰረቱና ገበያ ተኮር ስርዓተ-ትምህርቶችን ተግባራዊ ማድረግ
3. ምሩቃን በተግባር የተፈተሸ ክህሎት አዳብረዉ እንዲወጡ ማስቻል
4. በመውጫ ፈተና ውጤታማነትን የማረጋገጥ ስራ መስራት
5. በተመራቂ ተማሪዎች ውጤታማነት የቀጣሪ አካላት እርካታን ማሳደግ
6. የተመራቂ ተማሪዎች መረጃ በተሟላ ሁኔታ መያዝና ክትትል ማደረግ

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 1.2 የትምህርት ክፍሎች ቁጥር ማሳደግ

**የዓላማው መግለጫ** የትምህርት ፖሊሲያችንን መሰረት በማድረግ፣ የአገራችንንና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባትና የዳሰሳ ጥናት በማድረግ አግባብነት ያላቸውና ደረጃቸውን ጠብቀው የተስፋፉ የትምህርት ክፍሎችን ብዛት ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. በትምህርት ክፍል ደረጃ በትኩረት መስክ ላይ የተመሰረተ ካሪኩለም እንዲኖር ማድረግ
2. በፕሮግራምና በካሪኩለም ዝግጅት ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ማሳደግ
3. የተጠናከረ የትምህርት ፋሲሊቲና ግብዓት የማሟላት ተግባራትን ማከናወን
4. የዩኒቨርሲቲው የሰው ሃብት አቅም ማሳደግ
5. ከሌሎች አጋር አካላት ጋር የሚኖረን ግንኙነትን ማጠናከር
6. የዓለም አቀፍ እና የአገር አቀፍ የገበያ ፍላጎት ጥናት ማድረግ

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 1.3 የትምህርት ፕሮግራሞችን ማስፋፋት

**የዓላማው መግለጫ** የትምህርት ፖሊሲያችንን መሰረት በማድረግ፣ የአገራችንንና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባትና የዳሰሳ ጥናት በማድረግ አግባብነት ያላቸውና ደረጃቸውን ጠብቀው የተስፋፉ የትምህርት ፕሮግራሞችን ብዛት ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. የሦስተኛ ዲግሪያላቸው መምህራን ቁጥር መጨመር
2. ወደ ረዳት ፕሮፌሰርነት የትምህርት ማዕረግ የሚያድጉ መምህራን ቁጥር ማሳደግ
3. በቅጥርና በዝዉዉር ረዳት ፕሮፌሰርና ከዛ በላይ የትምህርት ማዕረግ ያላቸዉን መምህራንን ማምጣት
4. የትምህርት ፋሲሊቲዎችና ግብዓቶች ማሟላት

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 1.4 የትምህርት ጥራት አመላካች መስፈርቶች አፈፃፀም የተሻለ ማድረግ

**የዓላማው መግለጫ** የሀገር አቀፍ የትምህርት ጥራትና አግባብነት ማረጋገጫ ኤጀንሲ በሚያወጣቸው የትምህርት ጥራት መስፈርቶች መሰረት የዩኒቨርሲቲያችን የተቋማዊ ጥራትና ቁጥጥር ዳይሬክቶሬት የሚከናወኑ የትምህርት ጥራት ማስጠበቅ ተግባራትን የሚለካበት ነው።

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022 ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. ለትምህርት ስራ አጋዥ የሆኑ ግብአቶች ማሟላት
2. በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የተከታታይ ምዘና ተግባራዊነት አጠናክሮ ማስቀጠል
3. የስርዓተ ትምህርት ክለሳና ሞጁላራይዜሽን ተግባራዊነትን አጠናክሮ ማስቀጠል
4. የትምህርት ጥራት መስፈርትን መሰረት ያደረገ የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 1.5 የተማሪ ብክነትን መቀነስ

**የዓላማው መግለጫ** ጥራት ያለው ትምህርት ለተማሪዎች በመስጠት፣አካባቢውን ለመማር ማስተማር ስራ ምቹ በማድረግና መሰረታዊ አገልግሎቶችን በማሟላት የተማሪ ብክነትን ለመቀነስ የሚደረግ ጥረት ውጤታማነት የሚለካ ነው።

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. የተከታታይ ምዘና ስረዓት ተግባራዊነት ማጠናከር
2. ተግባር ተኮርና ተማሪ ተኮር የሆኑ የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴዎች መተግበር
3. ለሴቶች እና ውጤታቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ተማሪዎች ልዮ እገዛ ማገዝ
4. የተዘረጋውን የተማሪዎች የቡድን አደረጃጀት ስርዓት አጠናክሮ ማስቀጠል

**ስትራቴጂክ ዓላማ 1.6** በቴክኖሎጂ የተደገፉ የመማሪያ ክፍሎች መፍጠር

**የዓላማው መግለጫ፡-** ጥራት በያለው ኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የተደገፉ የመማሪያ ክፍሎችን መፍጠር

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. የኦንላይን ትምህርት መስጠት
2. በጊዜና በቦታ ያልተወሰነ ትምህርት መስጠት
3. የትምህርት መረጃና ግብረ-መልስ ልውውጥ
4. ለተማሪዎች የእርስ በርስ ግንኙነት ዘዴ መፍጠር

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 1.7 በየዓመቱ የምንቀበላቸው የመጀመሪያ ዲግሪ መደበኛ ተማሪዎች ብዛት ማሳደግ

**የዓላማው መግለጫ** በየዓመቱ በተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞች የምንቀበላቸውን የመደበኛ ተማሪዎች ብዛት ለመለካት የተቀመጠ ነው።

**መነሻ ጊዜ** 2012ዓ.ም

የእቅድ ዘመን 2013-2022ዓ.ም

የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

- የትምህርት ፕሮግራሞች የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ
- በተገኘው የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ውጤት መሰረት የሚከፈቱ የትምህርት ፕሮግራሞችን መለየት
- ለሚከፈቱ የትምህርት ፕሮግራሞች የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ ማካሄድ፣ በሴኔት ማፀደቅ እና ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚንስቴር መጠየቅ
- ከአቻ የትምህርት ተቋማት ጋር በመሆን የጋራ የትምህርት ፕሮግራሞችን መክፈት
- የትምህርት ፕሮግራሞች ማስፋፊያ ማዕከላት ማቋቋም

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 1.8 በየዓመቱ የምንቀበላቸው የሁለተኛ ዲግሪ መደበኛ ተማሪዎች ብዛት ማሳድግ

**የዓላማው መግለጫ** በየዓመቱ በተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞች የምንቀበላቸውን የሁለተኛ ድግሪ ተማሪዎች ብዛት ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

የእቅድ ዘመን 2013-2022ዓ.ም

የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

- የሦስተኛ ዲግሪያቸዉን አጠናቀዉ የሚመለሱ መምህራን ቁጥር ማስደግ
- ወደ ረዳት ፕሮፌሰርነት የትምህርት ማዕረግ የሚያድጉ መምህራን እንዲኖሩ ማስቻል
- በቅጥርና በዝዉዉር ረዳት ፕሮፌሰርና ከዛ በላይ የትምህርት ማዕረግ ያላቸዉን መምህራን ማሟላት
- የትምህርት ፋሲሊቲዎችና ግብዓቶች እንዲሟሉ ማድረግ

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 1.9 በየዓመቱ የምንቀበላቸው የሦስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ብዛት ማሳደግ

**የዓላማው መግለጫ** በየዓመቱ በተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞች የምንቀበላቸውን የሦስተኛ ድግሪ ተማሪዎች ብዛት ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. ወደ ተባባሪ ፕሮፌሰርነትና ፕሮፌሰርነት የትምህርት ማዕረግ የሚያድጉ መምህራን ቁጥር ማሳደግ
2. በቅጥርና በዝዉዉር ተባባሪ ፕሮፌሰርነትና ፕሮፌሰርነት የትምህርት ማዕረግ ያላቸዉን መምህራን ማሟላት
3. የትምህርት ፋሲሊቲዎችና ግብዓቶች ማሟላት

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 1.10 በየዓመቱ የምንቀበላቸው መደበኛ ያልሆኑ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ቁጥር ማሳደግ

**የዓላማው መግለጫ** በየዓመቱ በርቀትና በተከታታይ መርሃ ግብር ማለትም በቅዳሜና እሁድ፣ በርቀትና በክረምት የምንቀበላቸውን መደበኛ ያልሆኑ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ብዛት፣ የቅበላ አቅም እድገትን እና ተደራሽነትን ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

1. የሦስተኛ ዲግሪያቸዉን አጠናቀዉ የሚመለሱ መምህራን ቁጥር ማሰደግ
2. ወደ ረዳት ፕሮፌሰርነት የትምህርት ማዕረግ የሚያድጉ መምህራን እንዲኖሩ ማስቻል
3. በቅጥርና በዝዉዉር ረዳት ፕሮፌሰርና ከዛ በላይ የትምህርት ማዕረግ ያላቸዉን መምህራን ማሟላት
4. የትምህርት ፋሲሊቲዎችና ግብዓቶች እንዲሟሉ ማድረግ

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 1.11 በየዓመቱ የምንቀበላቸው የመጀመሪያ ዲግሪ መደበኛ ያልሆኑ ተማሪዎች ብዛት ማሳደግ

**የዓላማው መግለጫ** በየዓመቱ በርቀትና በተከታታይ መርሃ ግብር ማለትም በቅዳሜና እሁድ፣ በርቀትና በክረምት የምንቀበላቸውን መደበኛ ያልሆኑ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች ብዛት፣ የቅበላ አቅም እድገትን እና ተደራሽነትን ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

1. የተማሪዎችን መሰረታዊ አገልግሎት መስጫዎች ማጠናከር
2. የተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞችን ማስፋፈት
3. የሰው ኃብት አቅምን ማሳደግ

4. የትምህርት ፋሲሊቲዎችና ግብዓቶች ማሟላት

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 1.12 የትምህርትን ፍትሃዊነት ማረጋገጥ

**የዓላማው መግለጫ፡-** ዩኒቨርሲቲው በሚሰጣቸው አገልግሎቶችና ባለው ሃብት ሁሉም አካላት ማለትም ሴቶች፣ ለአደጋ ተጋላጭ፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ እንዲሁም ሁሉንም አካላት በእኩል ተጠቃሚ ለማድረግና ፍትሃዊ አሰራር ለማስፈን የሚያደርገውን ጥረት የሚያካትት ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. ለአደጋ ተጋላጭ አካላትን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ
2. ልዩ ትኩረት የሚሹ አካላትን ተጠቃሚ ማድረግ
3. የሴቶችን ተሳትፎ ማረጋገጥ
4. ሰላማዊ መማር ማስተማር እንዲኖር ማድረግ

**ግብ 2፡- የዩኒቨርስቲውን የአፈጻጸም አቅምና ብቃት ማሳደግ፣**

**ስትራቴጂክ ዓላማ 2.1** የመምህራን የትምህርት ደረጃ ስብጥር ማሳደግ

**የዓላማው መግለጫ** የሰዉ ኃብት አቅምን ለማጎልበት በሚሰጡ የረዥም ጊዜ ስልጠናዎች የመምህራን የትምህርት ደረጃ ስብጥር እድገት ለመለካት የተቀመጠ ነዉ፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. በዩኒቨርሲቲዉ በኩል ለመምህራን ልማት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት መስራት
2. በአገር ዉስጥ ዩኒቨርሲቲዎች የድህረ-ምረቃ ትምህርት ፕሮግራም በሰፊው መጠቀም
3. ሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ ያላቸዉ መምህራንን በቅጥርና በዝዉዉር ማሟላት
4. ለሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪ ትምህረት የተላኩ መምህራን ትምህርታቸዉን አጠናቀዉ እንዲመለሱ ክትትል ማድረግ

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 2.2 ብቃትና ተጠያቂነት ያለው አመራር መፍጠር

**የዓላማው መግለጫ** የከፍተኛ፣ መካከለኛና የታችኛው የአመራር አካላትና የተተኪ አመራሮች ክህሎት ያድጋል።
**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

- የስራ አመራር ስልጠና ማዕከል ማቋቋም
- የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት
- የልምድ ቀሰማ ማካሄድ

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 2.3 የሴት መምህራንን ቁጥር ከፍ ማድረግ

**የዓላማው መግለጫ** የሴቶችን ተሳትፎ በማሳደግ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ያመጡ ሴት ተመራቂዎችን መቅጠር
2. በቅጥር ወቅት ለሴቶች የተለየ ድጋፍ ማድረግ
3. የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎችን ማከናወን

ስትራቴጂክ ዓላማ 2.4 የሰራተኛው እርካታ ማረጋገጥ

**የዓላማው መግለጫ** በዩኒቨርሲቲዉ ዉስጥ ያሉ ሰራተኞችና ተማሪዎች በተቋሙ የዉስጥ አገልግሎቶች ያላቸዉን እርካታ ይለካል፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. መሰረተ-ልማቶችን ማሟላት
2. የትምህርት እድሎችን ማመቻቸት
3. የማትጊያ ስርዓት መዘርጋት
4. የመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት ማስፋፋት
5. የስራ አካባቢዉን አመቺ ማድረግ

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 2.5 የገቢ ማስገኛ ምንጮችን ማስፋት

**የዓላማው መግለጫ** ዩኒቨርሲቲው በመንግስት የሚመደብለት የድጎማ በጀት ጥገኝነት በመቀነስ የፋይናንስ አቅሙን ለማጠናከር የሚሰማራባቸውን ልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ምንጮችንና የድጋፍ አይነቶችን እድገት ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. አዋጭ የገበያ መስኮችን በጥናት በመለየት ተግባራዊ ማድረግ
2. በተለያዩ የስራ መስክ ለመሰማራት ሚያስችል የመነሻ ካፒታል መመደብ
3. የመምህራንን ፕሮጀክት የማምጣት አቅም ማሳደግ
4. ግንኙነትና አጋርነት ማሳደግ
5. የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ማእከላትን ማስፋፋት

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 2.6 የገቢ እድገት ማስቀጠል

**የዓላማው መግለጫ** ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የውስጥ ገቢ ማስገኛ ምንጮችን በማስፋፋት እና ከአጋር አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር የሚያገኘውን ገቢ ከአመታዊ መደበኛ በጀት ጋር ያለውን ድርሻ ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. አዋጭ የገበያ መስኮችን በጥናት በመለየት ተግባራዊ ማድረግ
2. በተለያዩ የስራ መስክ ለመሰማራት ሚያስችል የመነሻ ካፒታል መመደብ
3. የመምህራንን ፕሮጀክት የማምጣት አቅም ማሳደግ
4. ግንኙነትና አጋርነት ማሳደግ
5. የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ማእከላትን ማስፋፊት

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 2.7 ዓለም-አቀፍ ግንኙነቶች ዘርፍን ማሳደግ

**የዓላማው መግለጫ** ዩኒቨርስቲው ከዓለም-አቀፍ ተቋማት ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም የመሰረታቸውን ግንኙነቶች ቁጥር መጨመር የሚለካ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. የዓለም-አቀፍ ግንኙነት ዲን ጽ/ቤቱን ማጠናከር
2. የውጭ አገር ግንኙነትና አጋርነትን መመስረትና ማጠናከር
3. የመረጃ ልውውጡ በመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ የታገዘ ስለሚሆን ዩኒቨርሲቲው
4. የትብብር መስኮችን መለየት፣ ዝክረ-ሃሳቦችን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ
5. ተቋማዊ ኢሜይል አጠቃቀምን አጠናክሮ ማስቀጠል

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 2.8 የአህዝቦት ስራን የሚያሳድጉ የመገናኛ ዘዴዎችን ማስፋት

**የዓላማው መግለጫ** ዩኒቨርሲቲው በአገር ውስጥና ከአገር ዉጭ ከሚገኙ ተገልጋዮች፣ ባለድርሻ አካላትና ተቋማት ጋር የሚገናኝባቸዉን ወይም በቋሚነት የመረጃ ልውውጥ የሚያደርግባቸዉን የኤሌክትሮኒክና የህትመት መገናኛ ዘዴዎች ብዛት ይለካል።

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. ብዙሃኑን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ የመገናኛ ዘዴዎችን
2. የኢዲቶሪያል ካውንስልን ወደስራ ማስገባት
3. የግንኙነት ክህሎት ማጎልበቻ ስልጠናዎችን መስጠት
4. የመረጃ ልውውጡ በመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ የታገዘ ማድረግ

**ግብ 3፡- የማህበረሰብ ተሳትፎና የሳይንስ ባህል ግንባታን ማጠናከር**

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 3.1 ወደ ትግበራ የሚገቡ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ቁጥር ማሳደግ

**የዓላማው መግለጫ** በዩንቨርሲቲው ከተሰሩ የጥናትና ምርምር ዉጤቶች ዉስጥ የማህበረሰቡን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ተግባራዊየሆኑና ተጨባጭለውጥ ለማምጣት የተተገበሩት ምን ያህል እንደሆኑለመለካትየተቀመጠነው።

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. የጥናትና ምርምር መስፈርቶችን ያሟሉና ጥራታቸውን ጠብቀው የሚከናወኑ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ቁጥር ማሳደግ

2. የቴክኖሎጅ ሽግግርና የምርምር ማዕከላትን ማስፋፋት
3. የተመራማሪዎች የመመራመር አቅም ማሳደግ
4. የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ተስስር እየጎለበተ እንዲሄድ ማድረግ

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 3.2 የማህበረሰብ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር ማስደግ

**የዓላማው መግለጫ**ዩኒቨርሲቲው ለውጪ ማሕበረሰብ የሚሰጣቸውን የጥናትና ምርምር ዉጤቶች፣ የስልጠና፣ የማማከርና ሌሎችም አገልግሎቶች መጠቀም ከሚገባቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሆኑትን በቁጥር ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. የማህበረሰቡ ችግርና ፍላጎት በዳሰሳ ጥናት መከለስ
2. የሚሰጠው የማህበረሰብ አገልግሎት ችግር-ፈች እንዲሆን ጥረት ማድረግ
3. ለማህበረሰብ አገልግሎት የሚመደበውን በጀት ከፍ ማድረግ
4. የተለያዩ የማህበረሰብ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት መክፈት
5. የመምህራንን ፕሮጀክት የማምጣት አቅም ማሳደግ
6. ተሻጋሪ የምርምር ውጤቶች ማሳደግ
7. ግንኙነትና አጋርነት ማሳደግ

**ስትራቴጂክ ዓላማ 3.3** የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶችን ቁጥር ማሰደግ

**የዓላማው መግለጫ** ዩኒቨረሲቲው ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ የሚሰጣቸውን የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶች ቁጥር ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. የማህበረሰቡ ችግርና ፍላጎት በዳሰሳ ጥናት መለየት
2. ዩኒቨርሲቲው ለማህበረሰብ አገልግሎት የሚመድበው በጀት ከፍ ማድረግ
3. የተለያዩ የማህበረሰብ አገልግሎት መስጫ ማዕከላትን ማስፋፈት
4. የመምህራን ፕሮጀክት የማምጣት አቅም ማሳደግ
5. የምርምር ውጤቶች ወደ ፕሮጀክት እንዲቀየሩ ማድረግ

**ስትራቴጅክ ዓላማ** 3.4 በአካባቢው የሚገኙ አገር በቀል እውቀት መለየት፣ መሰብሰብ፣ ማደራጀትና ለጥቅም የሚውሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

**የዓላማው መግለጫ፡** በአካባቢው በርካታ አገር በቀል ጥበቦች፣ እውቀቶችና ቁሳዊ ሃብቶች ባለቤት ሙኖኑ ቢታወቅም እስከ ዛሬ ብዙም ያልተሰራበትና በሳይንሳዊ መንገድ ተደግፎ ስራ ላይ እንዲውል ማስቻል ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላማው ማስፈጸሚያ ስትራቴጅዎች**

1. ዩኒቨርስቲው በአካባቢው ያሉ አገር በቀል እውቀቶችን ይለያል ፣ ሰብስቦ እንዲያደራጁ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣
2. እውቀቱን የሚያጠና፣ የሚያበለጽግና የሚያደራጅ ክፍል እንዲያቋቋም ያደርጋል፣

**ስትራቴጅክ ዓላማ** 3.5. በስርዓተ ትምህርት ዝግጅት በተለያዩ የትምህርት መስኮች ጠቃሚ የሆኑ አገር በቀል እውቀትን በማካተት ተማሪዎች ትምህርቱ ከአገር በቀል እውቀት ጋር ተሰናስሎ እንዲሰጣቸው፡፡

**የዓላማው ማስፈጸሚያ ስትራቴጅዎች**

1. ከየትምህርት መስኩ ጋር የሚገናኙ አገር በቀል እውቀቶችን መለየት፣ ማዘጋጀትና በስርዐተ ትምህርቱ እንዲካተቱ ማድረግ

2. አገር በቀል እውቀቶችን በሚገባ ከሳይንሳዊ ዘዴ ጋር ማጣጣምና በተገቢ መንገድ ማዋሃድ፣

**ስትራቴጅክ ዓላማ** 3.6 ተመራማሪዎች በምርምርና ጥናቶቻቸው ለአገር በቀል እውቀቶች ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ማድረግ

**የዓላማው መግለጫ፡-** የአገር በቀል እውቀቶች ትኩረት ተነፍጓቸው የቆዩ በመሆኑ ያሉትና ጠቃሚ የሆኑትን በመለየት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ጥናትና ምርምር ማካሄድ

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

የዓላማው ማስፈጸሚያ ስትራቴጅዎች

1. ተመራማሪዎች በምርምር አገር በቀል እውቀት ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ማበረታታት
2. በሚገኙት የምርምር ውጤቶቹ ላይ ምሁራዊ ጥልቅ ውይይት የሚካሄድባቸውን መድረኮች ማዘጋጀት

**ስትራቴጅክ ዓላማ** 3.7 የአገር በቀል እውቀቶችን ማልማት፣ ለተግባር አመቺና ተደራሽ እንዲሆኑ

**የዓላማው መግለጫ** የሀገር በቀል እውቀቶችን በማዘጋጀትና በሚገባ በማደራጀት ለጠቃሚ ተደራሽ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላማው ማስፈጸሚያ ስትራቴጅዎች**

እንደ ባህሪያቸውና መልካቸው በተለያዩ መንገዶች የተሰበሰቡትን የአገር በቀል እውቀቶች በቁስ፣ በጽሑፍ ወይም በዲጂታል አዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ።

## ግብ 4፡- የጥናትና ምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራትን ማጠናከር

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 4.1 የጥናትና ምርምር ማዕከላትን ቁጥር ማሰደግ

**የዓላማው መግለጫ** የጥናትና ምርምር ምህዳርን መሰረት ያደረጉ ችግር ፈች ጥናትና ምርምሮችን ለመስራት የሚያገለግሉ የምርምር ማዕከላትን ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. የመምህራንን የጥናትና ምርምር ክህሎትና ልምድ ማሳደግ
2. የአካባቢው ማህበረሰብ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ግንዛቤ ማሳደግ
3. የቴክኖሎጂ ፕሮጀክቶችን ቁጥር ከፍ ማድረግ
4. የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞችን መስፋፋት
5. የአካባቢው መልክዓ-ምድር አመቺነት መጠቀም
6. ለጥናትና ምርምር የሚመደበውን በጀት ማሳደግ
7. ግንኙነትና አጋርነት ማሳደግ

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 4.2 በአገር ውስጥና በአለም አቀፍ ደረጃ የታተሙ የጥናትና የምርምር ውጤቶች ቁጥር ማሰደግ

**የዓላማው መግለጫ** በዩኒቨርሲቲው ከተሰሩ የጥናትና ምርምር ውጤቶች መካከል የጥናትና ምርምር ጥራት ማረጋገጫ መስፈርትን አሟልተው በዩኒቨርሲቲው፣ በአገር አቀፍ እና በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ባላቸው የምርምር ጆርናል አሳታሚ ድርጅቶች መታተም የቻሉትና በልዩ ልዩ ርዕሰ ጉዳዮች የተዘጋጁና የታተሙ ስራዎችን ብዛት የሚያሳይ መለኪያ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. ተመራማሪዎች በተለያዩ የምርምር ጉባዔዎች እንዲሳተፉና የተሻለ ክህሎት እንዲያዳብሩ ማድረግ
2. ከፍተኛ የትምህርት ማዕረግ ያላቸዉ መምህራን ቁጥር ማሳደግ
3. ለጥናትና ምርምር የሚመደበው በጀት ከፍ ማድረግ
4. በጆርናሎች ለሚያሳትሙ ተመራማሪዎች የማዕረግ እድገትና ማነቃቂያ መስጠት

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 4.3 የዩኒቨርሲቲዉ ተከታታይ ህትመት ዉስጥ የታተሙ የምርምር ውጤቶች ቁጥር ማሳደግ

**የዓላማው መግለጫ** ዩኒቨርሲቲው ከሚያሳትማቸዉ ተከታታይ ህትመት ዉጤቶች ዉስጥ በዩኒቨርሲቲዉ ተመራማሪዎች ተሰርተዉ የቀረቡ የምርምር ዉጤቶች ምን ያህል መሆናቸዉን የሚያሳይ መለኪያ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. ተመራማሪዎች በተለያዩ የምርምር ጉባዔዎች እንዲሳተፉና የተሻለ ክህሎት እንዲያዳብሩ ማድረግ
2. ከፍተኛ የትምህርት ማዕረግ ያላቸዉ መምህራን ቁጥር ማሳደግ
3. ለጥናትና ምርምር የሚመደበው በጀት ከፍ ማድረግ

በጆርናሎች ለሚያሳትሙ ተመራማሪዎች የማዕረግ እድገትና ማነቃቂያ

**ስትራቴጂክ ዓላማ 4.4** የተሸጋገሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች

**የዓላማው መግለጫ** ዩኒቨርሲቲው የሚያሸጋግራቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ብዛት ይለካል

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. ጠንካራ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር መፍጠር
2. የቴክኖሎጂ ሽግግር መስኮች በአግባቡ መለየት
3. የፈጠራ ክህሎት ያላቸውን ሠራተኞች፣ ተማሪዎች እና የአካባቢውን ማህበረሰብ የምርምርና ፈጠራ ችሎታቸውን ለማዳበርና ለመተግበር የሚያነሳሳቸው የማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት
4. ለቴክኖሎጂ ሽግግር የሚረዱ ዘርፈ ብዙ የሆኑ የምርምር ስነ ምህዳር ያላቸው ቤተ ሙከራዎችን ማደራጀት

**ግብ 5፡- የዩኒቨርስቲውን መሰረተ-ልማትና ፋሲሊቲ ማሳደግ**

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 5.1 በቴክኖሎጂ የተደገፉ አገልግሎቶች አይነት ማብዛት

**የዓላማው መግለጫ** ዩኒቨረሲቲው የአሰራር ስርዓቶችን በጠበቀ መልኩ የሚሰጣቸውን በቴክኖሎጂ የተደገፉ የአገልግሎት አይነቶች ቁጥር ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. የስራ ክፍሎችን አገልግቶች  በቴክኖሎጂ የተደገፉ ማድረግ
2. የዳታ ሴንተር ሕንፃ ግንባታውን በግብዓት ማሟላትና የመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት ማስፋፋት
3. የሰዉ ሃብት አቅሙን  ማሳደግ
4. አገራዊ የዲጂታል ኢኮኖሚ ስትራቴጂን መተግበር

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 5.2 ጥቅም ላይ የሚውል የመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ አገልግሎትን ማሳደግ

**የዓላማው መግለጫ** በዩንቨርሲቲው የሚከናወኑ አገልግሎቶችን በፍጥነትና በጥራት ለመስጠት የመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ ምን ያህል ጥቅም ላይ እንደዋለ ለመለካትየተቀመጠነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላማው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. የመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት ማስፋፋት
2. የስራ ክፍሎች አገልግሎት አሰጣጥየመረጃ ግንኙነት ቴክኖሎጂ አገልግሎትን እንዲጠቀሙ ማድረግ
3. የአገልግሎት ሰጭ የሰዉ ኃይል አቅም ማሳደግ
4. የዳታ ሴንተር ሕንፃ ግንባታ በማጠናቀቅ የተሟላ ማድረግ

**ግብ 6፡- የክትትልና ግምገማ ስርዓቱን ማጠናከር**

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 6.1 የክትትልና ግምገማ ስርዓት መዘርጋት

**የዓላማው መግለጫ** ዩኒቨርሲቲው በስትራቴጂክ ዘመኑ ለማከናወን የቀረጻቸው ፕርግራሞችና ፕርጀክቶች የሚፈለገውን የግብ ስኬት ያስገኙ ስለመሆኑ ፣ ተቋሙ በትክክለኛው የእድገትና የአገልግሎት አሰጣጥ አቅጣጫ እየተጓዙ መሆኑንና በሥራ እንቅስቃሴዎቹ ላይ ችግሮች ስለመኖርና አለመኖራቸው ለመረዳት፣ የአሠራር ክፍተቶች በአንድ በተወሰነ ደረጃና ጊዜ ለማረም ፣ በሥራ እንቅስቃሴ ላይ የሚታዩ የዕለት ከዕለት ለውጦችን ለመለካትና አሰራርን በማሻሻል ወደ ስኬት ለመድረስ

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. የበላይ አመራር አካላት እና የእቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት መምራት
2. በየደረጃው የሚገኙ ስራ ክፍሎችም ሰራተኞቻቸውን/መምህራንን ማሳተፍ
3. አፈጻጸምን በመከታተልና በመገምገም የማስተካከያ እርምጃዎችን በየጊዜው መውሰድ

**ስትራቴጂክ ዓላማ** 6.2 የዉስጥ አሰራር መመሪያዎችን ማዘጋጀት

**የዓላማው መግለጫ** በዩኒቨርሲቲው የተዘጋጁና የተከለሱ የውስጥ አሰራር መመሪያዎችን ብዛት ለመለካት የተቀመጠ ነው፡፡

**መነሻ ጊዜ** 2012 ዓ.ም

**የእቅድ ዘመን** 2013-2022ዓ.ም

**የዓላመው ማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች**

1. የዩኒቨርሲቲዉ የስራ ክፍሎች የየራሳቸውን የውስጥ የአሰራር መመሪያ እንዲያዘጋጁ ማድረግ
2. በዩኒቨርሲቲዉ ተጠያቂነትና ፍትኃዊነት የሰፈነበት የአገልግሎት መስጠት

# 1. ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዓላማ፣ አመላካችና ኢላማ ሰንጠረዥ

| ስትራቴጂካዊ ግብ | ስትራቴጂካዊ ዓላማ | አመልካች | መለኪያ | መነሻ | ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| የትምህርት ጥራት፣ አግባብነት፣ ተደራሽነትንና ፍትሃዊነት ማረጋገጥ | በየዓመቱ ከምናስመርቃቸዉ መደበኛ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የተቀጠሩ ተመራቂዎች መጠን ማሳደግ | የብክነት መጠን | በመቶኛ | 7.2 | 6 | 5 | 4 | 3 | 2 |
| | | በአንድ ዓመት ውስጥ የተቀጣሩ ተማሪዎች | በመቶኛ | 85.5 | 86 | 87 | 88 | 89 | 90 |
| | | የቀጣሪዎች እርካታ መጠን | በመቶኛ | - | 80 | 85 | 90 | 95 | 100 |
| | የትምህርት ክፍሎችና ፐሮግራሞች ቁጥር ማሳደግ | ያደጉ የትምህርት ክፍሎች ብዛት | | | | | | | |
| | | የመጀመሪያ ድግሪ | በቁጥር | 44 | 49 | 55 | 59 | 62 | 65 |
| | | የ2ኛ ድግሪ | በቁጥር | 4 | 19 | 25 | 30 | 35 | 40 |
| | | የ3ኛ ድግሪ | በቁጥር | - | - | - | - | 2 | 3 |
| | | በትምህርት ክፍል ደረጃ በትኩረት መስክ ላይ የተመሰረተ ካሪኩለም እንዲኖር ማድረግ | በቁጥር | . | 23 | 55 | 59 | 62 | 65 |
| | | በካሪክለም ዝግጅት የባለድርሻ አካላት ተሳተፍ መጠን | በመቶኛ | - | 50 | 60 | 70 | 80 | 90 |

| ስትራቴጂካዊ ግብ | ስትራቴጂካዊ ዓላማ | አመልካች | መለኪያ | መነሻ | ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| | የትምህርት ጥራት አመላካች መስፈርቶች አፈፃፀም የተሻለ ማድረግ | በቅድመ ምረቃ መምህር ተማሪ ጥምርታ | ምጥጥን | 1:19 | 1:19 | 1:19 | 1:18 | 1:18 | 1:17 |
| | | በድህረ ምረቃ መምህር ተማሪ ጥምርታ | ምጥጥን | - | 1:18 | 1:17 | 1:15 | 1:14 | 1:12 |
| | | መጽሐፍት ተማሪ ጥምርታ (ዋናና ማጣቀሻ) | ምጥጥን | 1:10 | 1:7 | 1:6 | 1:5 | 1:4 | 1:3 |
| | | የተከለሱ ስርዓተ ትምህርቶች | በመቶኛ | - | .- | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | | የተከናወነ ተቋማዊ ኦዲት | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | | የተከናወነ ፕሮግራም ኦዲት | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | | የተከናወነ የክትትል ኦዲት | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | | መውጫ ፈተና /Exit exam/ ተግባራዊ ያደረጉ ፕሮግራሞች | በመቶኛ | | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | | በመውጫ ፈተና የተማሪዎች የማለፍ ምጣኔ | በመቶኛ | 85 | 86 | 87 | 88 | 89 | 90 |
| | | የመጀመሪያ ድግሪ ተማሪዎች ማጠናቀቅ ምጣኔ | በመቶኛ | 84 | 84.5 | 85 | 86 | 87 | 88 |
| | | የሁለተኛ ድግሪ ተማሪዎች ማጠናቀቅ ምጣኔ | በመቶኛ | 92 | 93 | 84 | 85 | 86 | 97 |
| | | የሶስተኛ ድግሪ ተማሪዎች ማጠናቀቅ ምጣኔ | በመቶኛ | - | - | - | - | - | - |
| | | የአለም-አቀፍ ተማሪዎች | በቁጥር | - | - | - | 6 | 8 | 10 |
| | | የአለም-አቀፍ መምህራን ልዉዉጥ | በቁጠር | - | - | 1 | 2 | 3 | 4 |

| ስትራቴጂካዊ ግብ | ስትራቴጂካዊ ዓላማ | አመልካች | መለኪያ | መነሻ | ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| | በየዓመቱ በተለያዩ የትምህርት ፕሮግራሞች የምንቀበላቸውን ተማሪዎች ቁጥር ማሳደግ | የመጀመሪያ ዲግሪ መደበኛ ተማሪዎች | በቁጥር | 11,262 | 12,500 | 1[illegible],800 | 14,[illegible]00 | 15,000 | 16,000 |
| | | የሁለተኛ ዲግሪ መደበኛ ተማሪዎች | በቁጠር | 36 | 200 | 450 | 550 | 650 | 750 |
| | | የሦስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች | በቁጥር | - | - | - | - | 6 | 15 |
| | | መደበኛ ያልሆኑ የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች | በቁጠር | 127 | 127 | 427 | 800 | 1125 | 1300 |
| | | መደበኛ ያልሆኑ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች | በቁጥር | 8420 | 8420 | 9000 | 9500 | 10500 | 12000 |
| | የትምህርትን ፍትሃዊነት ማረጋገጥ | ለአደጋ ተጋላጭ አካላት ተጠቃሚነት መጠን | መቶኛ | 60 | 70 | 75 | 80 | 85 | 90 |
| | | ልዩ ትኩረት የሚሹ አካላት ተጠቃሚነት መጠን | መቶኛ | 10 | 15 | 20 | 25 | 30 | 35 |
| | ድጋፍ የሚሹ ተማሪዎችን መመረቅ ምጣኔን ማሳደግ | በዩኒቨርሲቲ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የማጠናቀቅ ምጣኔ | በመቶኛ | 90 | 92 | 93 | 94 | 95 | 96 |
| | | በዩኒቨርሲቲ የሴቶች የማጠናቀቅ ምጣኔ | በመቶኛ | 78 | 80 | 82 | 84 | 86 | 88 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ተማሪዎች ምረቃ ምጣኔ | በመቶኛ | 91 | 92 | 93 | 94 | 95 | 96 |

| ስትራቴጂካዊ ግብ | ስትራቴጂካዊ ዓላማ | አመልካች | መለኪያ | መነሻ 2012 | ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| | የዩኒቨርስቲውን የትኩረት መስክ መለየት | ፕሮግራሞችና የትምህርት መስክ የተለዩ መሆን | በመቶኛ | - | 20 | 50 | 80 | 90 | 95 |
| | | በትኩረት መስኩ ሊካተቱ የማይችሉትን የትምህርት መስኮች ማስወገድ | በመቶኛ | - | - | 20 | 30 | 40 | 60 |
| | | ከትኩረት መስኮች ውስጥ የልህቀት ማዕከላትን መለየት | በቁጥር | - | 1 | 2 | 3 | - | - |
| | | የተለዩ መስኮችን በመሰረተ ልማት ማሟላት | በመቶኛ | - | 20 | 40 | 60 | 80 | 100 |
| | ሰላመዊ መማር ማስተማር እንዲኖር ማድረግ | ዘላቂ ሰላም የሚያሰፍን ከሃገራዊ ስትራቴጂ የተመነዘረ ዝርዝር መርሀ ግብር ማዘጋጀት | በሰነድ | - | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | | መርሃ ግብሩን ተግባረዊ ለማድረግ የሚረዳ አደረጃጀት መፍጠር | የተፈጠረ አደረጃጀት | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 |

| ስትራቴጂካዊ ግብ | ስትራቴጂካዊ ዓላማ | አመልካች | መለኪያ | መነሻ 2012 | ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| የዩኒቨርስቲውን የአፈጻጸም አቅምና ብቃት ማሳደግ፣ | የመምህራን ልማትን ማስፋፋት | የመምህራን ምጥጥን በትምህርት ደረጃ | ምጣኔ | 22:75:3 | 17:76:7 | 14:77:9 | 10:78:12 | 7:78:15 | 5:79:16 |
| | | የማስተማር ስነ-ዘዴ ስልጠና ያገኙ መምህራን መጠን | በመቶኛ | 60 | 75 | 80 | 85 | 88 | 90 |
| | | በስነ-ምግባር ደንብ የሰለጠኑ ስነ-ምግባር የተላበሱ መምህራን | በመቶኛ | - | 55 | 65 | 75 | 85 | 95 |
| | | የሙያ ማረጋገጫ ያገኙ መምህራን | በመቶኛ | - | 50 | 60 | 75 | 85 | 90 |
| | | በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠና የተሳተፉ መምህራን | በመቶኛ | - | 60 | 75 | 80 | 85 | 90 |
| | | በምርምር የተሳተፉ መምህራን | በመቶኛ | - | 20 | 25 | 30 | 35 | 40 |
| | | በኢንዱስትሪ ገብተው የተግባር ልምምድ ያደረጉ | በመቶኛ | - | 5 | 10 | 15 | 20 | 25 |
| | ብቃትና ተጠያቂነት ያለው አመራር መፍጠር | የአካዳሚክ መካከለኛ ዓመራር ስልጠና ያገኙ አመራሮች መጠን | በመቶኛ | - | 20 | 25 | 30 | 50 | 70 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ስልጠና ያገኙ አመራሮች መጠን | በመቶኛ | - | 20 | 25 | 30 | 50 | 70 |
| | የሴት መምህራን አቅም ማሳደግ | ሴት አመራሮች | መቶኛ | 7.7 | 10 | 13 | 16 | 20 | 25 |
| | | የሴት መምህራን መጠን | መቶኛ | 13 | 15 | 17 | 20 | 22 | 24 |
| | የሰራተኛውንና የተገልጋይ እርካታ ማረጋገጥ | የስተዳደር ሰራተኛው እርካታ መጠን | በመቶኛ | 78 | 80 | 83 | 87 | 90 | 95 |
| | | የመምህራን እርካታ መጠን | መቶኛ | 51 | 60 | 70 | 80 | 85 | 90 |
| | | የተማሪዎች እርካታ መጠን | መቶኛ | 51 | 60 | 70 | 80 | 85 | 90 |

| ስትራቴጂካዊ ግብ | ስትራቴጂካዊ ዓላማ | አመልካች | መለኪያ | መነሻ 2012 | ኢላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| | የገቢ አቅምን ማሳደግ | የቀነሰ የኦዲት ግኝት | በመቶኛ | 8 | 7 | 5 | 3 | 1 | - |
| | | ጥቅም ላይ የዋለ በጀት | መቶኛ | 98 | 98 | 98.5 | 99 | 99.5 | 100 |
| | | የገቢ ማስገኛ ምንጮች ብዛት | በቁጠር | 5 | 11 | 18 | 22 | 28 | 30 |
| | | የገቢ እድገት ከጠቅላላ በጀት አንጻር | በመቶኛ | 3.6 | 4 | 6 | 7 | 8.5 | 10 |
| | ግንኙነቶች ዘርፍን ማሳደግ | በአገር ውስጥ የተመሰረተ ግንኙነት | በቁጥር | 11 | 20 | 24 | 28 | 32 | 35 |
| | | በውጪ አገር የተመሰረተ ግንኙነት | በቁጥረ | 10 | 12 | 14 | 16 | 18 | 20 |
| | የአህዝቦት ስራን የሚያሳድጉ የመገናኛ ዘዴዎችን ማስፋት | የመገናኛ ዘዴዎቸ | ቁጥር | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |

| ስትራቴጂካዊ ግብ | ስትራቴጂካዊ ዓላማ | አመልካች | መለኪያ | መነሻ 2012 | ኢላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| የማህበረሰብ ተሳትፎና የሳይንስ ባህል ግንባታን ማጠናከር | ወደ ትግበራ የሚገቡ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ቁጥር ማሳደግ | ወደ ትግበራ የገቡ የጥናትና ምርምር ውጤቶች | በመቶኛ | 5 | 10 | 12 | 17 | 20 | 25 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የማህበረሰብ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር ማሰደግ | ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች | በቁጥር | 13242 | 14000 | 15000 | 17000 | 20000 | 25000 |
| | | የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክቶች ብዛት | በቁጥር | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| | ሃገር በቀል እውቀትን ማበልጸግ | በተለዩ የሃገር በቀል እውቀቶች ላይ ምርምር ማካሄድ | በመቶኛ | 10 | 12 | 17 | 20 | 25 | 30 |
| | | በምርምር የተገኙ የሃገር በቀል እውቀት ውጤቶችን ለሕ/ሰቡ/እውቀቱ ባለቤቶች ማስተዋወቅ | በመቶኛ | 5 | 6 | 8 | 10 | 13 | 15 |
| | | ለእውቀቱ ባለቤቶች የአተገባበር ስልጠና መስጠት | በቁጥር | 0 | 2 | 3 | 3 | 4 | 5 |

| የወልድያ ዩኒቨርሲቲ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ስትራቴጂካዊ ግብ | ስትራቴጂካዊ ዓላማ | አመልካች | መለኪያ | መነሻ 2012 | ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| የጥናትና ምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራትን ማጠናከር | የጥናትና ምርምር ማዕከላትን ቁጥር ማሰደግ | የጥናትና ምርምር ማዕከላት | ቁጥር | 01 | 02 | 03 | 05 | 07 | 10 |
| | የታተሙ የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ቁጥር ማሳደግ | በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ጆርናሎች የታተሙ የምርምር ውጤቶች | በመቶኛ | 1 | 10 | 20 | 35 | 50 | 65 |
| | | በዩኒቨርሲቲው ተከታታተይ ህትመት የታተሙ የምርምር ውጤቶች | በመቶኛ | 38 | 55 | 55 | 60 | 65 | 70 |
| | ችግር ፈቺ ምርምሮችን ማካሄድ | ፒ-ኤች-ዲ መምህራን ጥናትና ምርምር እንዲያከሂዱ ማድረግ | በቁጥር | 5 | 6 | 8 | 11 | 16 | 21 |
| | | በሴት ተመራማሪዎች በመመራት የተከናወኑ ጥናትና ምርምሮች | በቁጥር | 3 | 5 | 8 | 12 | 17 | 23 |
| | | በዩኒቨርሲቲ ደረጃ መቅረብ ያለበትን የምርምር መሰረተ ልማት አቅርቦትን ማሳደግ | በመቶኛ | 50 | 65 | 77 | 83 | 90 | 95 |
| | | በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በቀረበ የምርምር መሰረተ ልማት አጠቃቀም የመምህራንን እርካታ ማሳደግ | በመቶኛ | 78 | 80 | 83 | 87 | 90 | 95 |
| | የተሸጋገሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች | የቴክኖሎጂ አገልግሎት | በመቶኛ | 10 | 15 | 25 | 40 | 50 | 70 |
| | | የአካባቢ ማሕ/ሰብ ችግር ፈች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የማሸጋገር ምርምር ማካሄድ | በቁጠር | 4 | 8 | 10 | 12 | 14 | 16 |
| | | በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ የተካሄዱ ምርምሮችን ማጠናቀቅ | በቁጥር | 1 | 5 | 7 | 9 | 12 | 15 |
| | | የተሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎች | ቁጥር | 1 | 5 | 7 | 9 | 12 | 15 |

| ስትራቴጂካዊ ግብ | ስትራቴጂካዊ ዓላማ | አመልካች | መለኪያ | መነሻ 2012 | ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| የዩኒቨርስቲውን መሰረተ-ልማትና ፋሲሊቲ ማሳደግ | በቴክኖሎጂ የተደገፉ አገልግሎቶች አይነት ማብዛት | የቴክኖሎጂ አገልግሎት | በመቶኛ | 10 | 15 | 25 | 40 | 50 | 70 |
| | | ስማርት ክፍሎችን ማዘጋጀት | በቁጥር | - | - | 8 | 12 | 16 | 20 |
| | | በስማርት ክፍሎች አጠቃቀም የተማሪ እርካታ ማሳደግ | በመቶኛ | - | - | 80 | 85 | 90 | 95 |
| | ዲጂታል ተጠቃሚነትን ማሳደግ | መምህራን በዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስልጠና መስጠት | በመቶኛ | - | 30 | 50 | 60 | 70 | 80 |
| | | የመምህራንን የዲጂጂታል ተጠቃሚነት ብቃት በተጨባጭ ማሳደግ | በመቶኛ | - | 30 | 50 | 60 | 70 | 80 |
| | የትምህርት ፋሲሊቲ ማሟላት | የላቦራቶሪ ተጠቃሚ ተማሪዎች ቁጥር በስታንዳርዱ መሰረት ማድረግ | በቁጥር | 40 | 38 | 36 | 34 | 32 | 30 |
| | | ላቦራቶሪ ቴክኒሽያኖችን ማሟላት | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| | | በላቦራቶሪ የተማሪ አጠቃቀም እርካታ ማሳደግ | በመቶኛ | - | 70 | 80 | 85 | 90 | 92 |
| | | ከዩኒቨርሲቲ ውጭ ባሉ ላቦራቶሪዎች አጠቃቀም የተማሪዎችን እርካታ ማሳደግ | በመቶኛ | - | 70 | 80 | 85 | 90 | 92 |

| ስትራቴጂካዊ ግብ | ስትራቴጂካዊ ዓላማ | አመልካች | መለኪያ | መነሻ | ዓላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2012 | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| የክትትልና ግምገማ ስርዓቱን ማጠናከር | የክትትልና ግምገማ ስርዓትን ማዳበር | የተዘረጋ የክትትል ስርዓት | በሰነድ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| | የዉስጥ አሰራር መመሪያዎች በማውጣት ስራን ማሳለጥ | የወጡ የውስጥ አሰራር መመሪያዎች | ቁጥር | 17 | 19 | 22 | 26 | 30 | 35 |
| | በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚዘጋጅ የዩኒቨርሲቲዎች ብቃት መለኪያ አማካይ ውጤትን ማሳደግ | አማካይ ውጤት | በመቶኛ | - | 75 | 78 | 80 | 82 | 84 |
| | በግምገማ ሂደቱ አግባብነት የመምህራንን እርካታ ማሳደግ | የእርካታ መጠን | መቶኛ | - | 75 | 78 | 80 | 82 | 88 |
| | በግምገማ ሂደቱ አግባብነት የተማሪዎችን እርካታ ማሳደግ | የእርካታ መጠን | መቶኛ | - | 70 | 72 | 74 | 78 | 80 |
| | በየሴሚስተሩ የተለዩ ዋና ዋና ዋና ማነቆዎችን መፍታት | የተፈቱ ችግሮች | መቶኛ | - | 80 | 82 | 84 | 86 | 90 |

# 9 የአምስት ዓመት የፋይናንስ ፍላጎት

ሺ.ህ

| የወጪ ዓይነት/የገንዘብ ምንጭ | የጊዜ ሰሌዳ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 2013 | 2014 | 2015 | 2016 | 2017 |
| ሀ. የመደበኛ ወጪ | 447,410.00 | 476,213.00 | 502,263.00 | 529,887.00 | 559,031.00 |
| ከመንግስት ግምጃ ቤት | 433,631.00 | 461,607.00 | 486,780.00 | 513,233.00 | 541,599.00 |
| ከውስጥ ገቢ | 13,779.00 | 14,606.00 | 15,483.00 | 16,654.00 | 17,432.00 |
| ለ. የካፒታል ወጪ | 600,000.00 | 630,000.00 | 750,000.00 | 820,000.00 | 890,000.00 |
| ድምር | 1,047,410.00 | 1,106,213.00 | 1,252,263.00 | 1,349,887.00 | 1,449,031.00 |
| ጠ ድምር | | | | | 6,204,804.00 |

## 10. ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች

ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች በተቋሙ የአፈጻጸም መነሻ እና በተቀረጹት ኢላማዎች መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሚቀረጹ አስቻይ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ዋና ዋና ተግባራት ናቸው፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው በእቅድ ዘመኑ ለማሳካት ያቀዳቸውን ግቦች በማስፈጸምስኬታማነቱን ሊያረጋግጡለት የሚችሉ፣ ከስትራቴጂክ ግቡ ጋር ቁርኝት ያላቸውና ወደ ተግባር የሚቀየሩ፣ እና ትርጉም ያለው ተቋማዊ ለውጥ ለማምጣት ሰፊ እድል የሚፈጥሩ 11 ስትራቴጂክ እርምጃዎችን ነድፏል፡፡

| እርምጃ 1፡ የሰው ሃብት ልማት ፕሮግራም | |
|---|---|
| **ወሰን** | ይህ ፕሮግራም የሚከተሉትን ፕሮጀክቶች ያካትታል<br>• የመምህራን ልማት ፕሮጀክት<br>• የአስተዳደር ሠራተኞች ልማት ፕሮጀክት<br>• የአመራር ልማት ፕሮጀክት |
| **ጠቀሜታ** | ይህ እርምጃ የተቋሙን የሰው ሀብት በበቂ ሁኔታ በማሟላት፤ በአመለካከት፣በእውቀትና በክህሎት ያደገ የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ መፍጠር እንዲሁም የአመራር ክህሎትን በማሳደግ ሁሉንም ተቋማዊ ግቦች ለማሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ግቦቹም፡-<br>• እርካታን ማሳደግ<br>• ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የምሩቃንን የተቀጣሪነት መጠን ማሳደግ<br>• ገቢን ማሳደግ<br>• የሀብት አጠቃቀምን ማሻሻል<br>• የአገልግሎት ዘርፎችን ማስፋፋት<br>• ተቋማዊ የአሰራር ስርዓትን ማሻሻል<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ<br>• የእኩል ዕድልና ተጠቃሚነትን ማሳደግ<br>• ግንኙነትና አጋርነትን ማሳደግ<br>• የሰዉ ኃይል አቅምን ማሳደግ<br>• መሰረተ-ልማትን ማስፋፋት |

| | |
|---|---|
| **የሚጠበቁ ውጤቶች** | ይህ እርምጃ በተቋሙ ውስጥ የሚገኙትን የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ስልጠና በመስጠት እና የሰውሀብት በማሟላት የሚከተሉት ውጤቶች እንዲገኙ ይረዳል፤<br>• የመምህራን የማስተማር፣ የምርምርና የማህበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከታቸዉ ያደገ እና የተወዳዳሪነት ብቃት ይኖራቸዋል፡፡<br>• በተለያዩ ዘርፎች የሚገኙ የአስተዳደር ሠራተኞች ዩኒቨርሲቲው የተቋቋመበትን ተልዕኮ ከማሳካት አኳያ በቂ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል እውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ይኖራቸዋል፡፡<br>• የከፍተኛ፣ መካከለኛና የታችኛው የአመራር አካላትና የተተኪ አመራሮች ክህሎት ያድጋል፡፡<br>• በየስራ ክፍሉ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ክህሎት ያላቸዉ ሠራተኞች እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡ |
| **የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት** | • የመምህራን ልማት ፕሮጀክት<br>  ◦ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ<br>  ◦ በቅጥርና በዝውውር የመምህራን ፍላጎት ማሟላት<br>  ◦ የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠና መስጠት<br>  ◦ ልምድ ቀሰማ ማካሄድ<br>• የአስተዳደር ሠራተኞች ልማት ፕሮጀክት<br>  ◦ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ<br>  ◦ መዋቅርን መከለስና ማሟላት<br>  ◦ የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠና መስጠት<br>  ◦ የልምድ ቀሰማ ማካሄድ<br>• የአመራር ልማት ፕሮጀክት<br>  ◦ የስራ አመራር ስልጠና ማዕከል ማቋቋም<br>  ◦ የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት<br>  ◦ የልምድ ቀሰማ ማካሄድ |
| **ማስፈጸሚያ በጀት** | **ብር** 1,427,365,400.00 |
| **የፕሮግራሙ ባለቤት** | • የሰው ሀብት ዳሬክቶሬት<br>• የአቅም ግንባታ ጽ/ቤት |
| **ፈጻሚ አካላት** | • በየደረጃው ያሉ ሁሉም የስራ ክፍሎች |

| እርምጃ 2፡ የተቋማዊ ለውጥ ማሻሻያ ፕሮግራም | |
|---|---|
| **ወሰን** | ይህ ፕሮግራም የሚከተሉትን ፕሮጀክቶች ያካትታል<br>• በጥናት የተደገፉ ፖሊሲዎችን፣ መመሪያዎችንና ደንቦችን የማውጣት፣ የመተግበርና የማሻሻል ፕሮጀክት<br>• የለውጥ ማስተግበሪያ መሳሪያዎች ፕሮጀክት<br>• ተቋማዊ የመረጃ አያያዝና አስተዳደር ፕሮጀክት |
| **ጠቀሜታ** | ይህ እርምጃ የዩኒቨርሲቲዉን የአሰራር ስርዓት በማሻሻል የሚከተሉት ግቦች እንዲሳኩ ይረዳል፡-<br>• እርካታን ማሳደግ<br>• ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የምሩቃንን የተቀጣሪነት መጠን ማሳደግ<br>• ገቢን ማሳደግ<br>• የሀብት አጠቃቀምን ማሻሻል<br>• የአገልግሎት ዘርፎችን ማስፋፋት<br>• ተቋማዊ የአሰራር ስርዓትን ማሻሻል<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ<br>• የእኩል ዕድልና ተጠቃሚነትን ማሳደግ<br>• ግንኙነትና አጋርነትን ማሳደግ<br>• የሰዉ ኃይል አቅምን ማሳደግ<br>• መሰረተ-ልማትን ማስፋፋት |
| **የሚጠበቁ ውጤቶች** | ይህ እርምጃ ሲፈፀም በዩኒቨርሲቲው<br>• መልካም አስተዳደር ይሰፍናል<br>• ሂደት ሳይሆን ውጤት ይለካል<br>• ቀልጣፋና ውጤታማ አገልገሎት ይሰጣል<br>• ተቋሙ ያለበትን የአፈፃፀም ደረጃ ያውቃል<br>• የተቋሙ ገጽታ ይሻሻላል<br>• ቀልጣፋና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ልውውጥ ይኖራል |
| **የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት** | • በጥናት የተደገፉ ፖሊሲዎችን፣ መመሪያዎችንና ደንቦችን የማውጣት፣ የመተግበርና የማሻሻል ፕሮጀክት<br>  ◦ መመሪያዎችን ማዘጋጀት<br>  ◦ መመሪያዎችን መተግበርና መከታተል<br>  ◦ ፖሊሲዎችን መለየትና መንደፍ<br>  ◦ ክፍተት ያለባቸዉን መመሪያዎች መፈተሽና እንዲሻሻሉ ማድረግ<br>  ◦ በአገራዊ መመሪያዎች ላይ የማሻሻያ አስተያየት መስጠት<br>• የለውጥ ማስተግበሪያ ፕሮጀክት<br>  ◦ የለውጥና መልካም አስተዳደር ዳይሬክቶሬትን ማጠናከር<br>  ◦ የለውጥ ማስተግበሪያ መሳሪያዎች የግንዛቤ ማስጨበጫና የማስረፅ ስራ መስራት<br>  ◦ የለውጥ ማስተግበሪያ መሳሪያዎች አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ማድረግ<br>• ተቋማዊ የመረጃ አያያዝና አስተዳደር ፕሮጀክት<br>  ◦ ተቋማዊ የመረጃ ቋት እንዲኖር ማድረግ<br>  ◦ ዘመናዊ የመረጃ አደረጃጀትና አያያዝ ስርዓት መዘርጋት፣ የሰዉ ኃብት አስተዳደር፣ የንብረት አስተዳደር፣ የተማሪዎች አገልግሎት፣ የፋይናንስና ግዥ አስተዳደር፣ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት አሰራር ማዘመኛ እንዲሁም የተማሪዎች የመረጃ አስተዳዳር ስርዓት መዘርጋት፣ የመረጃ ደህንነት መጠበቂያ ስርዓት መዘርጋት፡፡<br>  ◦ መረጃና መዛግብትን ለአጠቃቀም ቀላልና ምቹ ማድረግ |
| **ማስፈጸሚያ በጀት** | ብር 41,421,000.00 |
| **የፕሮግራሙ ባለቤት** | • የለውጥና መልካም አስተዳደር ዳይሬክቶሬት<br>• የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት |
| **ፈጻሚ አካላት** | • በየደረጃው ያሉ ሁሉም የስራ ክፍሎች |

| እርምጃ 3፡ የገቢ ማፈላለግና ማመንጨት ፕሮግራም | |
|---|---|
| **ወሰን** | ይህ ፕሮግራም የሚከተሉትን ፕሮጀክቶች ያካትታል<br>• የቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ ፕሮጀክት<br>• የማማከር፣ የስልጠናና ትምህርት ፕሮጀክት<br>• የምርምር ማዕከላት ፕሮጀክት<br>• የአገልግሎት ማዕከላት ፕሮጀክት<br>• የልማት ፕሮጀክት |
| **ጠቀሜታ** | ይህ እርምጃ የተቋሙን የሀብት አቅም በማጎልበት ሁሉንም ተቋማዊ ግቦች ለማሳካት አስተዋፅኦ አለው፡፡<br>• እርካታን ማሳደግ<br>• ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የምሩቃንን የተቀጣሪነት መጠን ማሳደግ<br>• ገቢ.ን ማሳደግ<br>• የሀብት አጠቃቀምን ማሻሻል<br>• የአገልግሎት ዘርፎችን ማስፋፋት<br>• ተቋማዊ የአሰራር ስርዓትን ማሻሻል<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ<br>• የእኩል ዕድልና ተጠቃሚነትን ማሳደግ<br>• ግንኙነትና አጋርነትን ማሳደግ<br>• የሰዉ ኃይል አቅምን ማሳደግ<br>• መሰረተ-ልማትን ማስፋፋት |
| **የሚጠበቁ ውጤቶች** | • የተጠናከረ የፋይናንስና የግብዓት አቅም እንዲኖር ያደርጋል<br>• የመንግስት በጀት ጥገኝነትን ይቀንሳል<br>• የሰራተኞች ተነሳሽነት ይጨምራል<br>• የተማሪ ቅበላ አቅም ያድጋል<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት ይስፋፋል<br>• የስራ ፈጠራ ባህል ያድጋል<br>• የጥናትና ምርምር ስራ ይጠናከራል<br>• ግንኙነትና አጋርነት ይጠናከራል |
| **የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት** | • **የቢዝነስ ኢንተርፕራይዝ ፕሮጀክት**<br>  • የኮንስትራክሽን ውል አስተዳደርና ፕሮጀክት ማኔጅመንት<br>  • የሲቪል ስራዎች ዲዛይንና ሱፐርቪዥን<br>  • የውሃ ስራዎች ዲዛይንና ሱፐርቪዥን<br>  • የመካኒካል ስራዎች ዲዛይንና ሱፐርቪዥን<br>  • የኤሌክትሪካል ስራዎች ዲዛይንና ሱፐርቪዥን<br>  • የአይሲቲ ስራዎች ዲዛይንና ሱፐርቪዥን<br>  • የቢሮ ማሽኖች እና የኤሌክትሮኒክሶች ጥገና<br>  • የጣውላና ብረታብረት ማምረት ስራዎች<br>  • የሥጋና ወተት ተዋጽኦ<br>  • የከብት ማድለብ ስራዎች<br>  • የዶሮ እርባታ<br>  • የሆቴልና የካፌቴሪያ አገልግሎት ስራዎች<br>  • የተረፈ ምግብ ማቀነባበሪያ |

| | |
|---|---|
| | **የማማከር፣ ስልጠናና ትምህርት ፕሮጀክት**<br>• የማማከርና ስልጠና ማዕከላትን ማቋቋምና ማደራጀት (የቴክኖሎጂ ስራዎች የስልጠና ማዕከል፣ የኢንዱስትሪያል ሰርትፊኬት ትምህርትና ስልጠና ማዕከል፣ የስራ አመራር ስልጠና ማዕከል፣ የጤና አገልግሎቶች ስልጠና ማዕከል፣<br>• ትምህርትና ስልጠና (የመደበኛ፣ የተከታታይና ርቀት ትምህርት፣ የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች)<br>• **የምርምር ማዕከላት ፕሮጀክት**<br>  • የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት<br>  • የተረፈ ምርምር ሽያጭ<br>  • የዘር ብዜት ሽያጭ<br>  • የእንስሳት እርባታና ህክምና<br>• **የአገልግሎት ማዕከላት ፕሮጀክት**<br>  • የመረጃ ቋት እና የክላውድ ኮምፒውቲንግ አገልግሎት<br>  • የአካል ብቃትና የጂምናዚየም አገልግሎት<br>• **የልማት ፕሮጀክት**<br>  • የአገር አቀፍ እና የዓለም አቀፍ ተቋማት ትብብርና ድጋፍ |
| **ማስፈጸሚያ በጀት** | **ብር** 19,000,000 |
| **የፕሮግራሙ ባለቤት** | • የኢንተርፕራይዝ ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤቶች<br>• የገቢና ሀብት ማመንጫ ዳይሬክቶሬት |
| **ፈጻሚ አካላት** | • የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች |

| እርምጃ 4፡ የግንባታና መሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም | |
|---|---|
| **ወሰን** | ይህ ፕሮግራም የሚከተሉትን ፕሮጀክቶች ያካትታል<br>• **የግንባታዎች ማስፈጸምና ማስፋፊያ ፕሮጀክት**<br>• የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ማዕከላት ግንባታና ማስፋፊያ ፕሮጀክት<br>• የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ፕሮጀክት<br>• የግቢ ውበትና ልማት ፕሮጀክት<br>• የፋሲሊቲ ማሟላትና ማደራጀት ፕሮጀክት |
| **ጠቀሜታ** | ይህ እርምጃ የተቋሙን የግንባታና የግንባታ ማስፋፊያ ፕሮጀክት፣ የምርምር ማዕከላት ግንባታና ማስፋፊያ ፕሮጀክት፣ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ፕሮጀክት፣ የግቢ ውበትና ልማት ፕሮጀክት እና የፋሲሊቲ ማሟላትና ማደራጀት ፕሮጀክት የሚያካትት ሲሆን የሚከተሉትን ተቋማዊ ግቦች ለማሳካት አስተዋፅኦ አለው፡፡<br>• እርካታን ማሳደግ<br>• ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የምሩቃንን የተቀጣሪነት መጠን ማሳደግ<br>• ገቢን ማሳደግ<br>• የሀብት አጠቃቀምን ማሻሻል<br>• የአገልግሎት ዘርፎችን ማስፋፋት<br>• ተቋማዊ የአሰራር ስርዓትን ማሻሻል<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ<br>• የእኩል ዕድልና ተጠቃሚነትን ማሳደግ<br>• ግንኙነትና አጋርነትን ማሳደግ<br>• የሰዉ ኃይል አቅምን ማሳደግ<br>• መሰረተ-ልማትን ማስፋፋት |
| **የሚጠበቁ ውጤቶች** | ይህ እርምጃ ተግባራዊ ሲሆን፡-<br>• ፈጣንና ጥራቱን የጠበቀ አገልግሎት<br>• ዘመናዊ፣ ውጤታማና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ልውውጥ<br>• ውብ፣ ማራኪና ለስራ የሚያነሳሳ ግቢ<br>• ምቹ የስራ አካባቢ ይኖራል፡፡ |
| **የሚከናወኑ ዝርዝርተግባራት** | **የግንባታዎች ማስፈጸምና ማስፋፊያ ፕሮጀክት**<br>በወልድያ ዋናው ግቢ<br>• የተማሪዎች የመኖሪያ ህንጻዎች ግንባታ<br>• የመማሪያ ክፍል ህንጻዎች ግንባታ<br>• የመምህራን የመኖሪያ ህንጻዎች ግንባታ<br>• የቤተ ሙከራ ህንጻዎች ግንባታ<br>• የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ<br>• የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች (የኳስ ሜዳ፣ የጂምናዚየም ህንጻ፣ የዋና ገንዳ)<br>• የአስተዳደር ህንጻ ግንባታ<br>• የቴክኖሎጂ ኢኒስቲቲውት ህንጻ<br>• ግቢ አጥር<br>• የክሊኒክ ማስፋፊያ<br>• የመዝናኛ ማዕከል<br>• ጋራዥ እና የጥገና ወርክሾፕ<br>• የጥበቃ ህንጻዎች ማስፋፊያ<br>• ሆስፒታል |

<table>
<tr>
<td>የሚከናወኑ ዝርዝርተግባራት</td>
<td>
<ul>
<li>የማስፋፊያ ጥያቄ</li>
<li>የውሃ ጉድጓድ</li>
<li>የማህበረሰብ ትምህርት ቤት</li>
</ul>
በመርሳ ግቢ
<ul>
<li>የተማሪዎች የመኖሪያ ህንጻዎች ግንባታ</li>
<li>የመማሪያ ክፍል ህንጻዎች ግንባታ</li>
<li>የመምህራን የመኖሪያ ህንጻዎች ግንባታ</li>
<li>የቤተ ሙከራ ህንጻዎች ግንባታ</li>
<li>የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ</li>
<li>የአስተዳደር ህንጻ ግንባታ</li>
<li>ግቢ አጥር</li>
<li>ክሊኒክ</li>
<li>የመዝናኛ ማዕከል</li>
<li>ቤተ-መጻሕፍት</li>
<li>የማስፋፊያ ጥያቄ</li>
</ul>
የቅዱስ ላሊበላ ግቢ
<ul>
<li>የተማሪዎች የመኖሪያ ህንጻዎች</li>
<li>የመማሪያ ክፍል ህንጻዎች ግንባታ</li>
<li>የመምህራን የመኖሪያ ህንጻዎች ግንባታ</li>
<li>የቤተ ሙከራ ህንጻዎች ግንባታ</li>
<li>የአስተዳደር ህንጻ ግንባታ</li>
<li>የቅዱስ ላሊበላ የባህል ሙዚየም</li>
<li>የግቢ አጥር</li>
<li>የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ</li>
<li>ክሊኒክ</li>
<li>የመዝናኛ ማዕከል</li>
<li>ቤተ መጻሕፍት</li>
<li>ሆቴል</li>
</ul>
በአዲስ አበባ
<ul>
<li>የዩኒቨርሲቲው ማስተባበሪያ ቢሮ</li>
</ul>
የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ማዕከላት ግንባታና ማስፋፊያ ፕሮጀክት
<ul>
<li>የቆቦና የጋሸና የምርምር ማዕከላት ግንባታ</li>
<li>የአቡነ ዮሴፍ፣ አባሆይ ጋራና የማሂ ተራራ የህዋ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ማዕከል</li>
<li>የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የምርምር ማዕከላት ህንጻ</li>
<li>የስልጠና፣ የስቲም እና የኢንኩቤሽን ማዕከል ግንባታ</li>
<li>የባዮቴክኖሎጂ ምርምር ማዕከል ማቋቋም</li>
<li>የባህልና ማሕበራዊ ሳይንስ ምርምር ማዕከል ማቋቋም</li>
<li>የህብረተሰብ ጤና እና የባህል ህክምና ምርምር ማዕከል ግንባታ</li>
</ul>
</td>
</tr>
</table>

| | |
|---|---|
| | • የትምህርት ስነ-ዘዴ ምርምር ማዕከል<br>• የአትክልትና ፍራፍሬ ችግኝ ጣቢያና ሰርቶ ማሳያ ማዕከል<br><br>• **የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ፕሮጀክት**<br>• የኢ.ኮ.ቴ የመረጃ ማዕከል (Data Center) መሰረተ ልማት ፕሮጀክት መተግበር<br>• የደህንነት ቴክኖሎጂ መዘርጋት<br>• ተቋማዊ የኢሜል አገልግሎት መስጫ ሰርቨር ማዘጋጀት<br>• የዲጂታል ቤተ መጻሕፍት እና ቪ.ዲ.አይ ቴክኖሎጂ መተግበር<br>• የአገልግሎት አይነቶችን ማስፋፋት (E-Learning, VoIP Phone, IPTV, Digital Signage, Smart Class Room, Video Conference Room, Wireless Internet, Power Solution)<br>• የኢ.ኮ.ቴ የጥገና አገልግሎት ማቋቋም<br>• የመረጃ ደህንነትን መጠበቂያ ስርዓት መዘርጋት<br>• የኔትወርክ ክምችት (Network Storage) ስርዓት መዘርጋት<br>• የስማርት መማሪያ ክፍሎችን መገንባት<br><br>• **የግቢ ውበትና ልማት ፕሮጀክት**<br>• የግቢው ውበትና ልማት ዲዛይን ማሰራት<br>• በዲዛይኑ መሰረት የግቢ ማስዋብና የልማት ስራዎች መስራትና አፈጻጸሙን መከታተል<br>• የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት መዘርጋት<br>• በፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያው የሚጣራውን ውሃ የመልሶ አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋት<br>• የግቢ ውበት እንክብካቤ ስራዎችን መስራት<br><br>• **የፋሲሊቲ ማሟላትና ማደራጀት ፕሮጀክት**<br>• መሰረተ ልማቶችን ማስፋፋት (መንገድ፣ መብራትና ውሃ)<br>• ፋሲሊቲዎችን በቁሳቁስ ማሟላት (ለመማር ማስተማር፣ ለአስተዳደር ቢሮዎች፣ ለመሰረታዊ አገልግሎት መስጫ፣ ለምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት መስጫ ወዘተ ማሟላት) |
| **ማስፈጸሚያ በጀት** | **ብር** 5,562,667,074 |
| **የፕሮግራሙ ባለቤት** | • የተቋማዊ ልማት ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት |
| **ፈጻሚ አካላት** | • የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች |

| እርምጃ 5 የትምህርት ፕሮግራሞችን ማሻሻያ ፕሮግራም | |
|---|---|
| **ወሰን** | ይህ ፕሮግራም ከዚህ በታች ያሉትን ፕሮጀክቶች በስሩ ይይዛል<br>• የትምህርት ፕሮግራሞች ማስፋፊያ ፕሮጀክት<br>• የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና ማሻሽያ ፕሮጀክት<br>• የተመራቂ ተማሪዎች አቅም ማጎልበቻ ፕሮጀክት<br>• በኤሌክትሮኒክ የተደገፉ ትምህርቶች ማሻሻያ ፕሮጀክት |
| **ጠቀሜታ** | ይህ እርምጃ የትምህርት ፕሮግራሞችን በማስፋፋት፤ የትምህርት ጥራትን በማሻሻል፣የምሩቃንን አቅም በማጎልበት እና የኤልክትሮኒክ ትምህርቶችን በመስጠት የትምህርትን ተደራሽነት ከዳር ለማድረስ ከፍተኛ አወንታዊ አስትዋፅኦ ሲኖረው እርምጃው ሲፈጸምም ዩኒቨርሲቲው ላወጣቸው ለሚከተሉት ተቋማዊ ግቦች መሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡<br>እነዚህም፡-<br>• እርካታን ማሳደግ<br>• ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የምሩቃንን የተቀጣሪነት መጠን ማሳደግ<br>• ገቢን ማሳደግ<br>• የሀብት አጠቃቀምን ማሻሻል<br>• የአገልግሎት ዘርፎችን ማስፋፋት<br>• ተቋማዊ የአሰራር ስርዓትን ማሻሻል<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ<br>• የእኩል ዕድልና ተጠቃሚነትን ማሳደግ<br>• ግንኙነትና አጋርነትን ማሳደግ<br>• የሰዉ ኃይል አቅምን ማሳደግ<br>• መሰረተ-ልማትን ማስፋፋት |
| **የሚጠበቁ ውጤቶች** | ይህ እርምጃ በተገቢው መንገድ ሲፈጸም የሚከተሉትን አበይት ውጤቶችን ያስገኛል<br>• ጥራት ያለው ትምህርት<br>• የትምህርት ተደራሽነት<br>• የዲጅታል ክህሎት ያላቸው ምሩቃን<br>• ብቁና ተወዳዳሪ ምሩቃን ይኖራሉ፡፡ |
| **የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት** | **የትምህርት ፕሮግራሞች ማስፋፍያ ፕሮጀክት**<br>• የትምህርት ፕሮግራሞች የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ<br>• በተገኘው የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ውጤት መሰረት የሚከፈቱ የትምህርት ፕሮግራሞችን መለየት<br>• ለሚከፈቱ የትምህርት ፕሮግራሞች የስርዓተ ትምህርት ቀረፃ ማካሄድ፣ በሴኔት ማፀደቅ እና ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚንስቴር መጠየቅ<br>• ከአቻ የትምህርት ተቋማት ጋር በመሆን የጋራ የትምህርት ፕሮግራሞችን መክፈት<br>• የትምህርት ፕሮግራሞች ማስፋፊያ ማዕከላት ማቋቋም<br><br>**የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና ማሻሽያ ፕሮጀክት**<br>• ተቋማዊ ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬትን ማጠናከር<br>• የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ መስፈርቶችን መተግበርና መከታተል<br>• ተግባር ተኮር የመማር ማስተማር ስነዘዴ መተግበር |

| | |
|---|---|
| | • ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማርስነዘዴ መተግበር<br>• የስርዓተ ትምህርት ክለሳ ማካሄድ<br><br>**የተመራቂ ተማሪዎች አቅም ማጎልበቻ ፕሮጀክት**<br>• የኬሪየር ማዕከል ማቋቋም<br>• የኬሪየር ጋይዳንስ እና ካዉንስሊንግ አገልግሎት መስጠት<br>• ተማሪዎችን ስለስራ ማፈላለግ፣ ሲቪ አዘገጃጀትና ቃለ-መጠይቅ አቀራረብ ማሰልጠን<br>• ለተመራቂ ተማሪዎች ሙያ-ተኮር ስልጠና መስጠት<br>• የተመራቂ ተማሪዎች የመቀጠር ምጣኔ ጥናት ማድረግ<br><br>**በኤሌክትሮኒክ የተደገፉ ትምህርቶች (E-Learning) ፕሮጀክት**<br>• የኦንላይን ትምህርት መስጠት<br>• በጊዜና በቦታ ያልተወሰነ ትምህርት መስጠት<br>• የትምህርት መረጃና ግብረ-መልስ ልውውጥ<br>• ለተማሪዎች የእርስ በርስ ግንኙነት ዘዴ መፍጠር |
| **ማስፈጸሚያ በጀት** | **ብር** 9,106,255.00 |
| **የፕሮግራሙ ባለቤት** | • አካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት<br>• ተቋማዊ ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት<br>• አካዳሚክ ፕሮግራሞች ጽ/ቤት<br>• የኢንፎርሚሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት |
| **ፈጻሚ አካላት** | • በየደረጃው ያሉ ሁሉም የስራ ክፍሎች |

| እርምጃ 6 የባለዘርፈ- ብዙ ጉዳዮች ማስፈፀምያ ፕሮግራም | |
|---|---|
| ወሰን | ይህ ፕሮግራም የሚከተሉትን ፕሮጀክቶች ይይዛል<br>• የስርዓተ ጾታ ማስፈፀምያ ፕሮጀክት<br>• የተላላፊ በሽታዎች መከላከያና መቆጣጠርያ ፕሮጀክት<br>• ልዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ፕሮጀክት |
| የሚጠበቁ ውጤቶች | ይህ ፕሮግራም ሲፈጸም የሚከተሉትን ውጤቶች ያስገኛል<br>• የሴቶች ተሳትፎ ይጨምራል<br>• የተላላፊ በሽታዎች ስርጭት ይቀንሳል<br>• እንክብካቤና ድጋፍ የሚያገኙ ቫይረሱ በደማቸው ያለ ወገኖች ቁጥር ይጨምራል<br>• ልዩ ትኩረት የሚሹ አካላት ድጋፍ ይጨምራል |
| ጠቀሜታ | ይህ እርምጃ የባለ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ለማሳካት እና ከዳር ለማድረስ ከፍተኛ አወንታዊ አስተዋፅኦ ሲኖረው ለሚከተሉት ተቋማዊ ግቦች መሳካት ከፍተኛ ድርሻ አለው።<br>እነዚህም፡-<br>• ተገልጋይ/ ባለድርሻ አካላት እርካታን ማሳደግ<br>• የትምህርት ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• እኩል እድልና ተጠቃሚነትን ማሳደግ<br>• የሰው ሃብት አቅምን ማሳደ |
| የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት | **የስርዓተ ጾታ ማስፈፀምያ ፕሮጀክት**<br>• አጋርነትን ማጠናከር<br>• የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት<br>• በሁሉም የስራ ክፍሎች ተካትተው የሚፈፀሙበትን ስርዓት መዘርጋት<br>• የስርዓተ ጾታ ክበባትን ማቋቋም<br>• የሴቶች ልዩ ፍላጎት መሟላቱን መከታተል<br>• በትምህርታቸዉ ተጨማሪ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸዉ ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት<br><br>**የተላላፊ በሽዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ ፕሮጀክት**<br>• የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ክፍሉን ማጠናከር<br>• የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መስራት<br>• የበጎ ፍቃድ አገልግሎትን ማጠናከር<br>• የምርመራና ማማከር ማእከል ማቋቋም<br>• ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸውን የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ክፍሎች መርዳትና መንከባከብ<br>• በሁሉም የስራ ክፍሎች ተካትተው የሚፈፀሙበትን ስርዓት መዘርጋት<br>• ፀረ-ኤድስ ክበባትን ማጠናከር<br>• የስነ-ተዋልዶና ጤና አገልግሎትን ማስፋፋት<br>• የስነ-ተዋልዶና ጤና አገልግሎትን ክበባት ማቋቋም |

| | |
|---|---|
| | • የተላላፊ በሽታዎች መከላከያ፣ መቆጣጠሪያና የግንዛቤ ማስጨበጫ ማዕከል ማቋቋም<br><br>**የልዩ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ፕሮጀክት**<br>• የልዩ ፍላጎት ጉዳዮች ማስፈፀምያ መመሪያ ማዘጋጀት<br>• የትምህርት አካባቢውን ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ማድረግ<br>• የፈጠራና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ማቋቋም<br>• የልዩ ድጋፍ ስርዓትን መተግበር<br>• ክበባት ማቋቋም |
| **ማስፈጸሚያ በጀት** | **ብር 20,970,419.00** |
| **የፕሮግራሙ ባለቤት** | • ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት<br>• የሴቶች፣ ወጣቶችና ሕፃናት ዳይሬክቶሬት<br>• የፈጠራና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል<br>• የኤችአይቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ክፍል |
| **ፈጻሚ አካላት** | • በየደረጃው ያሉ ሁሉም የስራ ክፍሎች |

| እርምጃ 7 የግንኙነትና አጋርነት ፕሮጀክት | |
|---|---|
| **ወሰን** | ይህ ፕሮጀክት የአገር ውስጥና የውጭ አገር ግንኙነትና አጋርነትን የመመስረት፣ የእርስ በእርስ ግንኙኝነት ክህሎትን የማጎልበቻ ስልጠና የመስጠት፣ የትብብር መስኮችን መለየትና ተግባራዊ ማድረግን ያካትታል። |
| **የሚጠበቁ ውጤቶች** | ይህ ፕሮግራም ሲተገበር የሚከተሉትን ውጤቶች ያስገኛል<br>• የዩኒቨርሲቲው መልካም ገፅታ ይገነባል<br>• ፈጣንና ወቅታዊ የመረጃ ልውውጥ ይኖራል<br>• ጠንካራ የአገር ውስጥና የውጭ ግንኙነት ይፈጠራል<br>• የጎለበተ የጋራ ጥቅም ይረጋገጣል<br>• የዉስጥ ገቢ ይዳብራል |
| **ጠቀሜታ** | ይህ እርምጃ የግንኙነትና አጋርነትን ለመፍጠር እና ለማጠናከር ከፍተኛ አውንታዊ አስትዋፅኦ ሲኖረው እርምጃው ሲፈጸምም ዩኒቨርሲቲው ላወጣቸው ተቋማዊ ግቦች ሁሉ መሳካት አስተዋኦ አያደርጋል።<br>እነርሱም፡-<br>• የተገልጋይ/ባለድርሻ አካላትን እርካታ ማሳደግ<br>• የትምህርት ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የጥናትና ምርምር ውጤቶች ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የሀብት አጠቃቀምን ማሻሻል<br>• ገቢን ማሳደግ<br>• ፕሮግራሞችን ማስፋፋት<br>• የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ማሻሻል<br>• ግንኙነትና አጋርነትን ማሳደግ<br>• የዕኩል ዕድልና ተጠቃሚነት ማሳደግ<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ<br>• የስራ አካባቢን ማሻሻል<br>• የሰው ሀይል አቅምን ማሳደግ<br>• የአይሲቲ መሰረተ ልማትን ማስፋፋት |
| **የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት** | • የዓለም-አቀፍ ግንኙነት ዲን ጽ/ቤት፣ የኮሙኒኬሽን ጉዳዩች ዳይሬክቶሬት እና የማሕበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያን ማጠናከር<br>• ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ማካሄድ<br>• የአገር ውስጥና የውጭ አገር ግንኙነትና አጋርነትን መመስረትና ማጠናከር<br>• ከታዋቂ የቴሌቪዥን ጣቢያ የአየር ሰዓት መግዛት<br>• ዩኒቨርሲቲው የሚያስተዋውቃቸውን ጉዳዮች መለየትና ማስተዋወቅ<br>• የትብብር መስኮችን መለየት፣ ዝክረ-ሃሳቦችን ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ<br>• ስለወቅታዊ ጉዳዮች ተከታታይ የአህዝቦት ስራ መስራት<br>• ተቋማዊ ኢሜይል አጠቃቀምን አጠናክሮ ማስቀጠል |
| **ማስፈጸሚያ በጀት** | ብር 20,500,000.00 |
| **የፕሮግራሙ ባለቤት** | • ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት<br>• የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት<br>• የዓለም-አቀፍ ግንኙነት ዲን ጽ/ቤት |
| **ፈጻሚ አካላት** | • በየደረጃው ያሉ ሁሉም የስራ ክፍሎች |

| እርምጃ 8፡ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ማስፋፊያ ፕሮግራም | |
|---|---|
| **ወሰን** | ይህ ፕሮግራም የሚከተሉትን ፕሮጀክቶች ያካትታል፡፡<br>• የጥናትና ምርምር ፕሮጀክት<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክት<br>• የህትመትና ዶክመንቴሽን ፕሮጀክት<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግርና የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር ፕሮጀክት |
| **የሚጠበቅ ውጤት** | ይህ ፕሮግራም ሲፈጸም የሚከተሉት ውጤቶችን ያስገኛል<br>• የጥናትና ምርምር ዉጤቶች ተደራሽነት<br>• የማህበረሰብ አገልግሎቶች ተደራሽነት<br>• የተሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎች ቁጥር ማደግ<br>• በውስጥና በውጭ የምርምር ስራዎች የታገዙ የማህበረሰብ አገልግሎቶች |
| **የሚኖረው ጠቀሜታ** | ይህ ፕሮግራም ሲፈጸም በዩኒቨርሲቲዉ የሚሰጡ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን ለማስፋፋትና በምርምር የታገዙ እንዲሆኑ የሚያደርግ ሲሆን የሚከተሉትን ግቦች ያሳካል፡፡<br>• የተገልጋይ/ባለድርሻ አካላትን እርካታ ማሳደግ<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• ገቢን ማሳደግ<br>• ፕሮግራሞችን ማስፋፋት<br>• ግንኙነትና አጋርነትን ማሳደግ<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ<br>• የሰው ሀይል አቅምን ማሳደግ |
| **የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት** | **የጥናትና ምርምር ፕሮጀክት**<br>• የጥናትና ምርምር ማዕከላትና ሰርቶ ማሳያ ቦታዎችን ማቋቋም፣ ማደራጀትና ማስፋፋት<br>• ቴክኖሎጂን የማላመድና የማሸጋገር ስራ መስራት<br>• የተመራማሪዎችን አቅም መገንባት<br>• የተለያዩ የምርምር ዝክረ-ሐሳቦችን ማዘጋጀትና ድጋፍ ማፋላለግ<br>• የጥናትና ምርምር የትኩረት መስኮችን መከለስ፣ መምረጥና ቅደም-ተከተል መስጠት<br>• በቴክኖሎጂ የታገዘ የጥናትና ምርምር ፅንሰ-ሃሳብ ጥሪ፣ ድጋፍና ክትትል ማድረግ<br>• የጥናትና ምርምር ዉጤቶች የሚቀርቡበትን መድረክ ማመቻቸት<br>• ዓለም-አቀፍና አገር-አቀፍ የምርምር ጉባዔ ማዘጋጀት<br>• የድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ስራ መስራት<br><br>**የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክት**<br>• በቴክኖሎጂ የታገዘ የማህበረሰብ አገልግሎት ፅንሰ-ሃሳብ ጥሪ፣ ድጋፍና ክትትል ማድረግ<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሔድ<br>• በዳሰሳ ጥናቱ መሰረት በተመረጡ የትኩረት መስኮች የማህበረሰብ |

| | |
|---|---|
| | አገልግሎት መስጠት<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት የተፅእኖ እና የፋይዳ ግምገማ ማድረግ<br>• የስልጠና፣ የስቲም እና የኢንኩቤሽን ስራዎችን ማደራጀትና ማስፋፋት<br>• የአገር-በቀል ችግኝ፣ የአትክልትና የፍራፍሬ ችግኞችን ማባዛት፣ መንከባከብና ማሰራጨት<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት ተግባራት የድጋፍ፣ የክትትልና የቁጥጥር ስራ<br><br>**የህትመትና ዶክመንቴሽን ፕሮጀክት**<br>• በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የምርምር ጆርናል ሕትመት ስራ መጀመር<br>• በየአካዳሚክ ዩኒቱ የምርምር ጆርናል ሕትመት ስራ መጀመር<br>• የምርምር ተከታታይ ሕትመት ስራ ማጠናከርና<br>• የምርምር ተከታታይ ሕትመት ስራ ባልተጀመረባቸዉ አካዳሚክ ዩኒቶች የሕትመት ስራ መጀመር<br>• የማሕበረሰብ አገልግሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎችን በመጽሄት ማሳተም<br><br>**የቴክኖሎጂ ሽግግርና የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር ፕሮጀክት**<br>• የዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስርን ማጠናከር<br>• በቴክኖሎጂ የታገዘ የቴክኖሎጂ ሽግግር ፅንሰ-ሃሳብ ጥሪ፣ ድጋፍና ክትትል ማድረግ<br>• የኢንኩቤሽን ስራዎችን ማስፋፋት<br>• የኢንተርንሽፕ እና የኤክስተርንሽፕ ስራዎችን ማጠናከር<br>• ከአገር-አቀፍና ዓለም-አቀፍ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተቋማት ጋር የቴክኖሎጂ ማላመድና ሽግግር ስራ መስራት |
| **ማስፈጸሚያ በጀት** | **ብር 180,101,700.00** |
| **የፕሮግራሙ ባለቤት** | • የምርምርና ዕድገት ጽ/ቤት<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት ጽ/ቤት<br>• የፈጠራና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግር ማስተባበሪያ ጽ/ቤት<br>• የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት<br>• የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ምርምር፣ ማህበረሰብ አገልግሎትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት<br>• የባሕልና ስነ-ጽሁፍ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት |
| **ፈጻሚ አካላት** | • በየደረጃዉ ያሉ ሁሉም የስራ ክፍሎች |

| እርምጃ 9፡ የሰላምና የደህንነት ጉዳይ ፕሮጀክት | |
|---|---|
| **ወሰን** | ይህ ፕሮጀክት በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥም ሆነ ዩኒቨርሲቲው በሚገኝበት አካባቢ ሰላምና ደህንነትን ለማስፈን የሚረዳ ሲሆን በውስጡም የመቻቻል ባህልን የማጎልበት፣ የሰላም ፎረምን የማጠናከር፣ የግጭት አፈታት ስርዓትን የመዘርጋትና የመተግበር፣ ከአካባቢው የጸጥታ ኃይሎችጋር ተቀናጅቶ የመስራት፣ የጥበቃ አገልግሎትን ማጠናከርን እንዲሁም በአካባቢ የሚገኙ የግጭት መንስኤዎችን መለየትና መፍትሄ የማፈላለግ ተግባራትን በዋናነት ያካትታል፡፡ |
| **የሚጠበቅ ውጤት** | ይህ ፕሮጀክት ሲከናወን የሚከተሉትን ውጤቶች ያስገኛል<br>• የዩኒቨርሲቲውና የአካባቢው ማህበረሰብ ሰላምና ደህንነት ይጠበቃል<br>• በዩኒቨርሲቲዉ ዉስጥ ሊፈጠር የሚችል ግጭት ይቀንሳል<br>• የተቀናጀና የዳበረ ችግሮችን የመፍታት ባህል ይፈጠራል |
| **የሚኖረው ጠቀሜታ** | በዩኒቨርሲቲው ውስጥም ሆነ በዩኒቨርሲቲው አካባቢ ሰላማና ደህንነት መፈጠር የሚከተሉትን ግቦች ለማሳካትያግዛል፡፡<br>• የተገልጋይ/ባለድርሻ አካላትን እርካታ ማሳደግ<br>• የትምህርት ተደራሽነት ማሳደግ<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የጥናትናምርምር ውጤቶችን ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የሀብት አጠቃቀም ማሻሻል<br>• ግንኙነትና አጋርነት ማሳደግ<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ<br>• የአገልግሎት አሠጣጥ ጥራትን ማሻሻል<br>• የዕኩል ዕድልና ተጠቃሚነት ማሳደግ<br>• የስራ አካባቢን ማሻሻል |
| **የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት** | • የመቻቻል ባህልን ማጎልበቻ ተግባራት ማከናወን<br>• የሰላም ፎረምን ማጠናከር<br>• የሰላም ጉባኤ ማዘጋጀት<br>• የግጭት አፈታት ስርዓትን መዘርጋትና ተግባራዊ ማድረግ<br>• ከአካባቢው ማህበረሰብና የጸጥታ ኃይሎች ጋር ተቀናጅቶ መስራት<br>• የጥበቃ አገልግሎትን ማጠናከር<br>• የግቢ የደህንነት ካሜራዎች መግጠምና ስራ ላይ ማዋል<br>• የደህንነት ቅድመ-ትንበያ ስርዓት መዘርጋት |
| **ማስፈጸሚያ በጀት** | ብር 9,500,000.00 |
| **የፕሮግራሙ ባለቤት** | • ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት |
| **ፈጻሚ አካላት** | • አስተዳደርና የተማሪዎች አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት<br>• የህዝብና የውጭ ግንኙነት ጽ/ቤት<br>• የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ ጽ/ቤት<br>• የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ<br>• የሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት<br>• በየደረጃዉ ያሉ የስራ ክፍሎች |

| እርምጃ 10፡ የውስጥ ቁጥጥርና የአሰራር ስርዓት ፕሮጀክት | |
|---|---|
| **ወሰን** | ይህ ፕሮጀክት ተቋሙ በአጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴውን ለመቆጣጠር የሚሰራቸውን የውስጥ የአሰራር ስርዓት አተገባበርና የስራ ክፍሎችን አፈጻጸም ክትትል ያካትታል፡፡ |
| **የሚጠበቅ ውጤት** | ይህ ፕሮጀክት ሲፈጸም የሚከተሉትን ውጤቶች ያስገኛል፡፡<br>• የተገልጋዮች እርካታ ያድጋል<br>• የአሰራር ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ይኖራል<br>• ቀልጣፋ አሰራር ይኖራል<br>• ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል<br>• ፍትኃዊነት ይሰፍናል |
| **የሚኖረው ጠቀሜታ** | ይህ እርምጃ ተቋሙ ለሚያከናውናቸው ሁሉም ተግባራት በጣም ከፍተኛ አስተዋጾ የሚኖረው ሲሆን የሚከተሉት ግቦች እንዲሳኩ ያደርጋል፡፡<br>• የተገልጋይ/ ባለድርሻ አካላትንእርካታማሳደግ<br>• የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ማሻሻል<br>• የስራ አካባቢን ማሻሻል<br>• ገቢን ማሳደግ<br>• የሀብት አጠቃቀምን ማሻሻል<br>• የእኩል ዕድልና ተጠቃሚነትን ማሳደግ |
| **የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት** | • የውስጥ ኦዲት፣ የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና፣ የህግ አገልግሎት እና ተቋማዊ ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬቶችን ማጠናከር<br>• ዘመናዊና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣ ድጋፍ ማድረግና ተግባራዊነቱን መቆጣጠር<br>• በኦዲት ግኝቶች መሰረት የማስተካኪያ እርምጃ መውሰድና ግብረ መልስ መስጠት<br>• የንብረት ምዝገባ፣ ክትትልና ቁጥጥር ስራ ማከናወን<br>• የፋይናንስ የማስፈፀም አቅምን ማጠናከር<br>• በህግ የሚያዙ የተቋሙን ጉዳዮች በመከታተል የተቋሙን ጥቅም ማስጠበቅ |
| **ማስፈጸሚያበጀት** | ብር 2,700,000.00 |
| **የፕሮግራሙ ባለቤት** | • ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት<br>• የውስጥ ኦዲት ዳይሬክቶሬት<br>• የስነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ዳይሬክቶሬት<br>• የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት<br>• ተቋማዊ ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት |
| **ፈጻሚ አካላት** | • በየደረጃው ያሉ ሁሉም የስራ ክፍሎች |

| እርምጃ 11፡ የክትትልና ግምገማ ፕሮጀክት | |
|---|---|
| **ወሰን** | ይህ እርምጃ የተቋሙን አጠቃላይ የስራ ክንውን የመከታተል፣ የመገምገም፣ የመቆጣጠርና የማስተካከያ እርምጃዎች መውሰድን ያካትታል፡፡ |
| **የሚጠበቅ ውጤት** | ይህ እርምጃ ሲከናወን የሚከተሉትን ውጤቶች ያስገኛል፡፡<br>• የተግባራት ዉጤታማነት ይጨምራል<br>• መመሪያዎችና ደንቦች በአግባቡ ይተገበራሉ<br>• የተቋሙ ተወዳዳሪነት ይጨምራል<br>• የሰራተኞች የመፈፀም ብቃት ያድጋል |

| | |
|---|---|
| **የሚኖረው ጠቀሜታ** | ያስቀመጥናቸውን ግቦች በእስትራቴጂክ ዘመኑ መጨረሻ ለማሳካት በተዘረዘሩት እስትራቴጂያዊ እርምጃዎች ስር ያሉትን ተግባራት በታቀደላቸው አግባብ እየተከናወኑ መሆናቸውን ለመገምገምና ለመከታተል የሚያስችል ሲሆን የዚህ እርምጃ መተግበር ሁሉንም ግቦች ለማሳካት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።<br>• የተገልጋይ/ባለድርሻ አካላትን እርካታ ማሳደግ<br>• የትምህርት ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የጥናትና ምርምር ውጤቶችን ተደራሽነትን ማሳደግ<br>• የሀብት አጠቃቀምን ማሻሻል<br>• ገቢን ማሳደግ<br>• ፕሮግራሞችን ማስፋፋት<br>• የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ማሻሻል<br>• ግንኙነትና አጋርነትን ማሳደግ<br>• የዕኩል ዕድልና ተጠቃሚነት ማሳደግ<br>• የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ<br>• የስራ አካባቢን ማሻሻል<br>• የሰው ሀይል አቅምን ማሳደግ<br>• የአይሲቲ መሰረተ ልማትን ማስፋፋት |
| **የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራት** | • የክትትል፣ ግምገማና ቁጥጥር ስርዓቱን ማሻሻል<br>• የክትትል፣ ግምገማና ቁጥጥር ክህሎትን ማሳደግ<br>• ወቅታዊ የክትትል፣ ግምገማና ቁጥጥር ስራ መስራት<br>• የክትትል፣ ግምገማና ቁጥጥር ስርዓቱን በኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ ማድረግ<br>• በክትትል፣ ግምገማና ቁጥጥር ውጤት ተመርኩዞ ግብረ መልስ መስጠትና የማስተካኪያ እርጃዎችን መውሰድ |
| **ማስፈጸሚያ በጀት** | ብር 19,350,100.00 |
| **የፕሮግራሙ ባለቤት** | • ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት<br>• የእቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት |
| **ፈጻሚ አካላት** | • በየደረጃው ያሉ ሁሉም የስራ ክፍሎች |

# 9. የክትትልና ግምገማ ስርዓት

ዩኒቨርሲቲው በስትራቴጂክ ዘመኑ ለማከናወን የቀረጻቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሚፈለገውን የግብ ስኬት ያስገኙ ስለመሆኑ ፣ ተቋሙ በትክክለኛው የእድገትና የአገልግሎት አሰጣጥ አቅጣጫ እየተጓዙ መሆኑንና በሥራ እንቅስቃሴዎቹ ላይ ችግሮች ስለመኖርና አለመኖራቸው ለመረዳት ፣ የአሠራር ክፍተቶች በአንድ በተወሰነ ደረጃና ጊዜ ለማረም ፣ በሥራ እንቅስቃሴ ላይ የሚታዩ የዕለት ከዕለት ለውጦችን ለመለካትና አሰራርን በማሻሻል ወደ ስኬት ለመድረስ ውጤትን መሠረት ያደረገ የክትትል፣ ግምገማ ስርዓት መዘርጋት ወሳኝ ነው፡፡

ይህ ተግባር ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ደግሞ በዩኒቨርሲቲው የስራ ክፍሎች መካከል የጠበቀ ትስስር ሲፈጠርና በሁሉም ዘንድ የባለቤትነት ስሜት ሲጎለብት በመሆኑ ተግባሩን የበላይ አመራር አካላት እና የእቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት በበላይነት የሚመሩት ቢሆንም በየደረጃው የሚገኙ ስራ ክፍሎችም ሰራተኞቻቸውን/መምህራንን ባሳተፈ መልኩ አፈጻጸማቸውን በመከታተልና በመገምገም የማስተካከያ እርምጃዎችን በየጊዜው መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ይህ የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ስርዓት ተዘጋጅቷል፡፡

## 9.1 የክትትል ስርዓት

የዩኒቨርሲቲው የስራ ክፍሎች ከአምስት አመቱ ስትራቴጂክ እቅድ የተቀዳ ዓመታዊ እቅዳቸውን የክፍሉን ሰራተኞች/መምህራን በማሳተፍ ማዘጋጀት የሚጠበቅባቸው ሲሆን ወደ መንፈቅ ዓመት፣ ሩብ ዓመት፣ ወርሃዊና ሳምንታዊ እቅዶች በመመንዘር ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ የአፈጻጸም ሪፖርታቸውንም በየወቅቱ ለእቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በዚሁ መሰረት በዩኒቨርሲቲው፡-

- ተቋማዊ
- የስራ ክፍሎች
- የስራ ቡድኖች/ ዲፓርትመንቶች እና

- የፈጻሚዎች አፈጻጸም ሪፖርቶች ይዘጋጃሉ፡፡

ሪፖርቶቹ በሚዘጋጁበት ወቅት ገላጭ የሆኑና የእቅድ አፈጻጸምን በንጽጽር የሚያሳዩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

በየክፍሉ ከሚቀርቡ ወቅታዊ ሪፖርቶች በተጨማሪ የእቅድ አፈጻጸሙን /በተለይ ከለውጥ ፕሮግራሞች አፈጻጸምና ከውስጥ ቁጥጥር አንጻር/ ለመከታተል የሚያስችሉ አዳጊ አመላካች ነጥቦች / በማዘጋጀት በግንባር ክትትል ይደረጋል፡፡

## 9.2 የሪፖርት ፍሰትና ወቅት

የስትራቴጂክ እቅዱን አፈጻጸም በአግባቡ ለመከታተል ያስችል ዘንድ በየደረጃው የሚገኙ የስራ ክፍሎች፣ መምህራንና ሰራተኞች ለቅርብ ኃላፊዎቻቸው በአፈጻጸም ወቅት የታዩ ጥንካሬዎችን፣ ድክመቶችን፣ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችንና የተሰጡ መፍትሄዎችን በግልጽ የሚያሳይ ሪፖረት ማቅረብ የሚኖርባቸው ሲሆን ፡-

- በግለሰብ ደረጃ ፈጻሚዎች ከቅርብ ኃላፊዎቻቸው ጋር በየቀኑ አፈጻጸማቸውን የተመለከተ የቃል መረጃ ልውውጥ ያደርጋሉ፣ በእለት ስራ መመዝገቢያም ላይ ያሰፍራሉ፤
- ፈጻሚው በሳምንቱ የመጨረሻ ቀን ሳምንታዊ አፈጻጸሙን የተመለከተ የጽሁፍ ሪፖርት ለቅርብ ኃላፊው ያቀርባል፤
- የትምህርት ክፍሎችና ሌሎች ንኡሳን የስራ ክፍሎች በየ15 ቀኑ ከሚመለከታቸው የክፍሉ መምህራን/ሰራተኞች ጋር የስራ አፈጻጸማቸውን በመገምገም የጽሁፍ ሪፖርት ለቅርብ ተጠሪያቸው ያቀርባሉ፤
- ፋኩሊቲዎች/ዳይሬክቶሬቶች/ጽ/ቤቶች በየወሩ ከሚመለከታቸው የክፍሉ መምህራን/ሰራተኞች ጋር አፈጻጸማቸውን በመገምገም ወርሃዊ የጽሁፍ ሪፖርት ለቅርብ ተጠሪያቸው ያቀርባሉ፤
- የምክትል ፕሬዜዳንት ጽ/ቤቶችና ተጠሪነታቸው ለፕሬዛዳንቱ የሆኑ ዳይሬክቶሬቶችና ጽ/ቤቶች በየሩብ አመቱ ከሚመለከታቸው የክፍሉ መምህራን/ሰራተኞች ጋር አፈጻጸማቸውን በመገምገም የሩብ ዓመት

የጽሁፍ ሪፖርት ለፕሬዜዳንት ጽ/ቤት እና ለእቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ያቀርባሉ፤

- የእቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ ዳይሬክቶሬት ከየስራ ዘርፉ የተቀበላቸውን የሩብ ዓመት የእቅድ ክንውን ሪፖርቶች በማጠቃለልና በዩኒቨርሲቲው የማኔጅመንት ካውንስል በማስገምገም የጽሁፍ ሪፖርት ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፣ ለዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ቦርድም ቀርቦ እንዲገመገም ያደርጋል፡፡
- በየስድስት ወሩ የዩኒቨርሲቲው የእቅድ ክንውን በዩኒቨርሲቲው መምህራንና ሰራተኞች በጋራ የሚገመገም ሲሆን ለዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ቦርድም ቀርቦ አቅጣጫ እንዲሰጥበት ይደረጋል፡፡

## 9.3 የሪፖርትና ግብረ-መልስ የጊዜ ሰሌዳ

የስትራቴጂክ እቅዱን በተደራጀና በተጠናከረ መንገድ በመምራትና አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የሚጠበቀውን ውጤት ለማምጣት ይቻል ዘንድ በዩኒቨርሲቲው ወጥ የሆነ የሪፖርት ግንኙነት የጊዜ ሰሌዳ እንዲኖር ማድረግ የሚያስፈግ ሲሆን በዚህ መሰረት፡-

- የግለሰብ ፈጻሚዎች ሳምንታዊ የጽሁፍ ሪፖርት በየሳምንቱ አርብ ለቅርብ ኃላፊያቸው መድረስ የሚኖርበት ሲሆን በቀጣዩ ሰኞ የቅርብ ኃላፊው ግብረ-መልስ መስጠት ይኖርበታል፡፡
- የ15 ቀን ሪፖርቶች ወር በገባ ከ14 እስከ 16 እና ከ28-30 ለቅርብ ኃላፊ መድረስ ይኖርባቸዋል፤ ግብረ-መልሱም በ3 ቀናት ውስጥ ለሚመለከታቸው እንዲደርስ ይደረጋል፡፡
- ወርሃዊ ሪፖርቶች በቀጣዩ ወር በገባ 25 እስከ 28 ለሚመለከተው አካል መድረስ የሚኖርባቸው ሲሆን ግብረ-መልስ ሪፖርቱ በ4 ቀናት ውስጥ መሰጠት ይኖርበታል፡፡
- የሩብ ዓመት ሪፖርቶች በመስከረም፣ በታህሳስ፣ በመጋቢት እንዲሁም በሰኔ ወራት ከ25 እስከ 30 ባሉት ቀናት ውስጥ ለሚመለከታቸው አካላት መድረስ የሚኖርባቸው ሲሆን በደረሱ 7 ቀናት ውስጥም ግብረ-መልስ መሰጠት ይኖርበታል፡፡

## 9.4 ግምገማ

በስትራቴጂክ ዘመኑ ለማከናወን በእቅድ የተያዙ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና አንኳር ተግባራትን በላቀ ሁኔታ ለመፈጸምና የሚጠበቀው የግብ ስኬት ላይ ለመድረስ አፈጻጸምን መገምገምና ያለበትን ደረጃ ማወቅ የግድ ይላል።

በመሆኑም ዩኒቨርስቲው በግለሰብ፣ በቡድንና በተቋም ደረጃ ሊኖር የሚችለውን የአፈጻጸም ደረጃ በየጊዜው በመለካት ለሚመለከታቸው አካላት ግልጽ ያደርጋል። በዚህም መሰረት፡-

1. ከአራቱ እይታዎች አንጻር አፈጻጸሙ የሚኖረው ክብደት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

| እይታ | ክብደት በመቶኛ |
|---|---|
| ተገልጋይ/ባለድርሻ አካል | 20 |
| ፋይናንስ | 15 |
| የውስጥ አሰራር | 30 |
| መማማርና እድገት | 35 |

2. በየእይታዎቹ የተቀመጡ ግቦች የራሳቸው የክብደት ነጥብ ይሰጣቸዋል። የተቋሙ፣ ለስራ ዘርፎችና ለፈጻሚዎች የሚወርዱ ግቦችና ግብ ተኮር ተግባራትም ይህንኑ መሰረት ያደረገ ክብደት ይኖራቸዋል።

| የአፈጻጸም ደረጃ | ነጥብ | አፈጻጸም በመቶኛ | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| በጣም ከፍተኛ | 5 | ከ95 አስከ 100 | አፈጻጸምን በእቅድ ከተያዘው |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | አንጻር በመቶኛ በማስላት |
| ከፍተኛ | 4 | ከ80 እስከ 94 | ‹‹ ‹‹ |
| መካከለኛ | 3 | ከ60 እስከ 79 | ‹‹ ‹‹ |
| ዝቅተኛ | 2 | ከ50 እስከ 59 | ‹‹ ‹‹ |
| በጣም ዝቅተኛ | 1 | ከ50 በታች | ‹‹ ‹‹ |

በዚህም ላይ በመመስረት የአፈጻጸም ደረጃ የሚለይ ሲሆን አምስት የአፈጻጸም ደረጃዎች ይኖራሉ፡-

- የስድስት ወር የአፈጻጸም ሪፖርትን መሰረት በማድረግ የተቋሙ የአፈጻጸም ደረጃ በአመት ሁለት ግዜ እንዲለይ ይደረጋል፤
- የስራ ክፍሎችና ቡድኖች የአፈጻጸም ደረጃ በየሩብ አመቱ በአፈጻጸም ሪፖርቶቻቸው ላይ በመመስረት ይለያል፤
- የአስተዳደር ሰራተኞች የስራ አፈጻጸም በሲቪል ሰርቪስ መመሪያ መሰረት በታህሳስና በሰኔ መጨረሻ በዓመት ሁለት ጊዜ በቅርብ ኃላፊዎቻቸው፣ በስራ ባልደረቦቻቸውና በራሳቸው የግምገማ ውጤት እንዲሞላ በማድረግ ደረጃቸው ይለያል፤
- የመምህራን የስራ አፈጻጸም ግምገማ በየሴሚስተሩ መጨረሻ በዓመት ሁለት ጊዜ ይከናወናል፤

የግምገማ ውጤቶች በየጊዜው በማስታወቂያ ሰሌዳዎችና በተለያዩ መንገዶች ይፋ ይደረጋሉ፡፡

በተጨማሪም በየስድስት ወሩ የስትራቴጂክ እቅዱ የአፈጻጸም ደረጃ፣ የተገኙ መልካም ተሞክሮዎች፣ ጥንካሬዎችና ተግዳሮቶች ይፋ ይደረጋሉ፡፡

## 9.5 የውድድርና የሽልማት አፈጻጸም

የዩኒቨርስቲውን የተግባራት አፈጻጸም በቀጣይነት ለማሻሻል ይረዳ ዘንድ በተግባሮች አፈጻጸም ላይ የተመሰረተ የውድድርና የሽልማት ስረዓት የሚኖር ሲሆን በዚህም

የተሻሉ የስራ ክፍሎች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች ተለይተው በየዓመቱ መጨረሻ ይሸለማሉ፡፡ ለዚህም ዩኒቨርሲቲው ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## 9.6 ስትራቴጂ ፍተሻና ማስተካከያ

በየጊዜው ከሚከናወኑ ተከታታይና አመታዊ ግምገማዎች በመነሳት ስትራቴጂውን እንደገና መፈተሸና ማስተካከል ባስፈለገበት ማናቸውም ወቅት እንዲስተካከል የሚደረግ ሲሆን የተወሰዱ ማስተካከያዎችን የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች፣ ቡድኖችና ግለሰቦች እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

## 9.7 የቅሬታ አቀራረብ

ማንኛውም የዩኒቨርሲቲው አመራር ወይም ፈጻሚ በስራ አፈፃፀም ግምገማ ውጤቱ ላይ ቅሬታ ካለው በማንኛውም ጊዜ ለሚመለከተው ኃላፊ ወይም የቅሬታ ሰሚ አካል አቅርቦ መልስ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ዩኒቨርሲቲው የቅሬታ ማስተናገጃ ሥረዓት በመዘርጋት የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል፡፡